አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ

ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርኃ ግብር

# የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ

በ

ድርብወርቅ ብፁ

ሰኔ፣ 2007

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ

ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርኃ ግብር

# የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ

በ

ድርብወርቅ ብፁ

በአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ስንቅነሽ አጣለ /ዶ/ር/

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ

ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርኃ ግብር

# የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ

በ

ድርብወርቅ ብፁ

2007 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ፊርማ

_____________ _____________

የፈታኝ ስም

_____________ _____________

_____________ _____________

# ማስታወሻነቱ

**ይህ ጥናት በቤተሰባችን ውስጥ ሁሌም ህያው ሆና**

**ለምትኖረው  እህቴ ተናኘ ብፁ ይሁንልኝ**!!!!!!!

# ምስጋና

ነጻ የትምህርት እድል ለሰጠኝ እና ለጥናቱ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናየ ከፍ ያለ ነው።

ከጅምሩ፤ርእስ ከመምረጥ ጀምሮ እያንዳንዷን ሃሳብ እና ቃል ያለመታከት በማረም እና በማስተካከል ይህ ጥናት እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍና እገዛ ላደረገችልኝ አማካሪዬ ዶ/ር ስንቅነሽ አጣለ ከ "አመሰግናለሁ" ውጭ ምን እላለሁ! አመሰግናለሁ።

ዶ/ር ዋልተንጉስ መኮነን እንደ ሁለተኛ አማካሪ በመሆን ማግኘት የማልችላቸውን መጣጥፎች እና መጽሓፍት ከማዋስ ጀምሮ ያደረክልኝ የሃሳብ ድጋፍ ከፍተኛ ስለነበር ምስጋናዬ ይድረስህ። ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው እና ዶ/ር ሙሉሰው አስራቴ (ከብሄረሰቡ አንጻር) የምን ላይ ደረስሽ ጥያቄያችሁ እና በፈለኩት ሰአት ቢሯችሁን ክፍት በማድረግ በነጻነት ለስራዬ የሚሆኑ ሃሳቦቻችሁን ወስጃለሁና አመሰግናለሁ። አቶ የወንድወሰን አውላቸው እና ሌሎችም ስማችሁን ያልጠቀስኳችሁ ነገር ግን በሃሳብ ፣መጽሓፍትን በማዋስ ያገዛችሁኝን እንዲሁም በክፍል ውስጥ የሰጣችሁኝ እውቀት በዚህ ስራ ላይ አሻራው አለና ምስጋናየ ይድረሳችሁ።

በሕይወቴ ሁሉ ስኬቴን ለማየት በምታሳዩኝ ጉጉት ገፍታችሁ እዚህ ላደረሳችሁኝ ቤተሰቦቼ፤ ለእናቴ ሰውነት በላቸው፣ ለታላቋ! እህቴ ሃረግነሽ ብፁ፣ ለወንድሞቼ መስረት እና ኤሊያስ ብፁ እንዲሁም ለአብዩ እንግዳ እና አስረሳች ፈጣሪ ዕድሜ እና ጤና አብዝቶ ይስጥልኝ።

በመጨረሻ መረጃ ለመሰብሰብ መስክ በወጣሁበት ጊዜ በቤታችሁ ውዬ አድሬ፤ ተስተናግጄ በነጻነት መረጃ እንድሰበስብ ለረዳችሁኝ ኤሊኝታ እና ሳሉ ፣የመስክ እረዳቶቼ እንዲሁም ሌሎች መረጃ አቀባዮቼ እና ጓደኞቼ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልል በሚገኘው የጉምዝ ብሔረሰብ በሚፈፀሙ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓቶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በብሔረሰቡ በዋናነት የሚፈፀሙ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓቶችን በማሳየት ከሚከወኑባቸው አውዶች አንፃር የሚኖራቸውን ማሕበራዊ ፋይዳ መለየት፣ መግለፅ እና መተርጐም ነው፡፡

በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ሥር ካሉ ሦስት ዞኖች ውስጥ አንዱ በሆነው በመተከል ዞን የሚገኘው የማንዱራ ወረዳ የተመረጠው ቦታ ሲሆን ከወረዳውም አምስት ቀበሌዎች ተመርጠዋል፡፡ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከተመረጡት ቀበሌዎች አራት ያህል ሥርዓቶችን በመመልከት መረጃ የሰበሰብኩ ሲሆን 22 ሰዎች የተሳተፉባቸው ሦስት የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በአጠቃላይ 37 ሰዎች በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ተሳትፈዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 15ቱ ሴቶች ሲሆኑ 22ቱ ወንዶች ናቸው፡፡

በመረጃዎቹ መሰረት በብሔረሰቡ ውስጥ በዋናነት የሚካሄዱት የሕይወት ዘመን ዑደቶች ወይም የሽግግር ሥርዓቶች አራት ሲሆኑ እነሱም የውልደት፣ የመጀመሪያ የወር አበባ እና የወንድ ልጅ ግርዛት፣ የጋብቻ እና የሰርግ ሥርዓት እንዲሁም የሀዘን እና የተስካር ሥርዓቶች ናቸው፡፡ እነዚህን መረጃዎች ለመተንተን እና ለመተርጐም ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በጥናቱ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት ላይ በሚከወኑ ልማዳዊ ሥርዓቶች ውስጥ መስዋእት ማቅረብ፣ መቆሸሽና መንጻት ፣ዘር ማስቀጠል፣ ጸጉር መላጨት እና ጉድጓድ ውስጥ መቅበር የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦች ተተንትነዋል፡፡ በመጨረሻም የሚከተሉትን ግኝቶች አስገኝተዋል፡፡ ሥርዓቶቹ የብሔረሰቡን አመለካከት የሚያሳዩ መሆናቸውን፣ ማሕበረሰቡ የተገነባበትን መዋቅር ማስጠበቂያ ሆነው የሚያገለግሉ መሆናቸውን፣ በማሕበረሰቡ ውስጥ ማሕበራዊ ትስስር መፍጠሪያ እና ማጠናከሪያ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ መተጋገዝን የሚፈጥሩ መሆናቸውን እና ሁሉም ሥርዓቶች የቡድኑን አባላት ሥነ ልቦናዊ እርካታ የሚጨምሩ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል፡፡

## ሙዳየ ቃላት

| አማርኛ | ጉምዘኛ |
|---|---|
| ወፍጮ | ግህሻ |
| በወር አበባ ጊዜ የሚያገለግል ሞዴስ መሰል ነገር | ምጫ |
| አምላክ | ሙሳ |
| ባህላዊ ጠላ | ክያ |
| አረቄ | ፀልኛ |
| የመጀመሪያ የወር አበባ ጭፈራ | ግዲደስ ግህዥ |
| መውለድ | ምኘቋ |
| የመጀመሪያው የወር አበባ ጠላ | ክይ ግህዣ |
| ግርዛት | ሽፓ |
| ተስካር | ከይምሻ |
| ሞት | ምሻ |
| ባህላዊ ሀኪም | ጋፍያ |
| መተት | ግጨሀ |
| ባህላዊ አስተዳደር | ሲያ አጒ |
| ሀብታም | ጢሳ |

ማውጫ

ገጽ

1.መግቢያ ..... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 2
1.2. የጥናቱ አካባቢ ዳራ ..... 3
1.2.1. መልክአምድራዊ ገለጻ ..... 3
1.2.2. ታሪካዊ ዳራ ..... 4
1.2.3. ባሕላዊ አስተዳደር ..... 5
1.2.4. የአምልኮ ሥርዓት ..... 6
1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 7
1.4. የጥናቱ አላማዎች ..... 8
1.5. የምርምር ጥያቄዎች ..... 8
1. 6. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 8
1.7. የጥናቱ ወሰን ..... 9
1.8. የጥናቱ ዘዴ ..... 9
1.8.1. የናሙና አመራረጥ ..... 9
1.8.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..... 10
1.8.2.1. ምልከታ ..... 10
1.8.2.2. ቃለ መጠይቅ ..... 11
1.8.2.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት ..... 12
1.8.3. የመስክ ስነ ምግባሮች ..... 12
1.8.4. የመረጃ ትንተና ዘዴ ..... 13
1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ..... 13

1.10. የመስክ ተሞክሮ ........ 14

2. የንድፈ ሃሳብና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ........ 18

2.1. የንድፈ ሃሳብ ቅኝት ........ 18

2.1.1. የከበራ (ritual) ምንነት ........ 18

2.1.2. የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ምዕራፎች ........ 20

2.1.2.1. መለየት (separation) ........ 21

2.1.2.2. መሸጋገር (transition or liminality) ........ 21

2.1.2.3. መዋሃድ (Re incorporation) ........ 22

2.1.3. የአውድ ተኮር ጥናት መሰረቶች ........ 22

2.1.4. የተግባራዊ መዋቅራዊ ንድፈ ሃሳብ ምንነት ........ 24

2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 25

2.2.1. በአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተደረጉ ጥናቶች ........ 25

2.2.2. ከትምህርት ክፍሉ ውጭ የተደረጉ ጥናቶችና ሌሎች ጽሑፎች ........ 26

3. የማንዱራ ወረዳ የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት ከሚከወኑባቸው ዐውዶች አንፃር ........ 30

3.1. የውልደት ሥርዓት (ምፐቋ) ........ 30

3.2. የመጀመሪያ የወር አበባ እና የወንድ ልጅ ግርዛት ........ 36

3.2.1. የመጀመሪያ የወር አበባ ሥርዓት (ግዲድስ ግኸዣ) ........ 36

3.2.2. የወንድ ልጅ ግርዛት (ሸፓ) ........ 39

3.3. የጋብቻ እና የሰርግ ሥርዓት ........ 40

3.3.1. የለውጥ ጋብቻ (ማንጅልማ) ........ 40

3.3.2. የጠለፋ ጋብቻ (ማንጉዣ) ........ 45

3.2.3. የጥሎሽ ጋብቻ (ቢዣ) ........ 48

3.3.4. የውርስ ጋብቻ (ቻምብ ድዋ) ........ 49

3.3.5. የማደጎ ጋብቻ (ምዳንቋ)................................................................................................... 50

3.4. የሀዘንና የተስካር ሥርዓት ...................................................................................................... 50

3.4.1. የሃዘን ሥርዓት ..................................................................................................................... 50

3.4.2. የተስካር ሥርዓት ................................................................................................................... 55

4.ትንታኔ ......................................................................................................................................... 63

4.1. በሥርዓቶቹ የሚከወኑ ልማዳዊ ድርጊቶችና ትዕምርትነታቸው .................................... 63

4.1.1. መፅዳት እና መቆሸሽ ........................................................................................................ 63

4.1.2. መስዋእት ማቅረብ ................................................................................................................ 65

4.1.3. ደም ....................................................................................................................................... 66

4.1.4. ዘር መተካት ......................................................................................................................... 66

4.1.5. ፀጉር መላጨት ..................................................................................................................... 67

4.1.6. መቅበር ................................................................................................................................. 68

4.2. የሽግግርሥርዓቶች እናበሥርዓቶቹየሚከወኑልማዶች ለማሕበረሰቡ ያላቸውፋይዳ..........
…………………………………………………………………………………………….68

4.2.1. ማሕበራዊ ፋይዳ ................................................................................................................. 68

4.2.1.1. ማሕበራዊ መዋቅሩን ማስጠበቅ ................................................................................... 69

4.3.1.2. ማሕበራዊ ትስስር መፍጠር........................................................................................... 72

4.2.1.3. ማሕበራዊ ደረጃን ማሳወቅ ማስቻል ........................................................................... 73

5.ማጠቃለያ ................................................................................................................................... 75

አባሪዎች

# 1.መግቢያ

የጉምዝ ብሔረሰብ የሚኖረው በአብዛኛው በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በከማሽ እና መተከል ዞን ሲሆን በአማራ ክልል በሰሜን ጐንደር ዞን በመተማ ወረዳም በጥቂቱ ይገኛል። ይህ ጥናት የተካሄደው በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ካሉ ሦስት ዞኖች አንዱ በሆነው የመተከል ዞን በማንዱራ ወረዳ በሚገኙ የብሔረሰቡ አባላት ላይ ነው። በማንዱራ ወረዳ የሚገኙ የብሔረሰቡ አባላት የሰው ልጅ ተወልዶ እስኪሞት ድረስ ባለው የሕይወት ጉዞ የሚያልፍባቸውን ደረጃዎች የሚቀበሉባቸው እና የሚሸኙባቸው ስርአቶች አሏቸው። ከነዚህ ደረጃዎች ውስጥ ውልደት፣ ለአቅመ ሄዋን እና ለአቅመ አዳም መድረስ፣ ማግባት እና መሞት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በእነዚህ የሕይወት እርከኖች ላይ የሚከናወኑ የሽግግር ሥርአቶች ለማሕበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ መለየት፣ መግለፅና መተርጐም የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ነው።

ጥናቱ አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ እና ስለ አካባቢውና ስለብሔረሰቡ ገለፃ የተደረገበት አካባቢያዊ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ ምርምሩ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን እና የጥናቱ ዘዴ የቀረቡበት ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን በሚል አብይ ርዕስ ስር የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት እና የንድፈ ሃሳብ ዳራ ቀርቧል፡፡ በሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች መዋቅር አንጻር ተደራጅተው አውዳዊ ገለጻ ተካሂዶባቸዋል፡፡ በአራተኛው ምዕራፍ መረጃዎች ተተንትነው እና ተተርጉመው ቀርበዋል፡፡ በአምስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ የቀረበ ሲሆን፣ ዋቢ መጻሕፍት እናአባሪዎች ማጠቃለያውን ተከትለው ተደርድረዋል።

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

የየትኛውም ብሔረሰብ አባልበሕይወት ሲኖር የሚያልፍባቸው በርካታ ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህ ደረጃዎች ከሕጻንነት ወደ ወጣትነት ሲሸጋገር፣ ከወጣትነት ወደ ጉልምስና ሲሸጋገር፣ከጎልማሳነት ወደ እርጅና ሲሸጋገር፣ ከአንድ ቡድን ተነጥሎ ወደ ሌላ ቡድን ሲቀላቀል እና ከአንድ ማሕበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ማሕበራዊ ደረጃ ሲሸጋገር የሚያገኛቸው ናቸው፡፡ ከሽግግሮቹ ውስጥም ልደት፣ ጋብቻ እና ሞት ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡በማንኛውም ማሕበረሰብ ያለ ግለሰብ በሕይወት ሲኖር በተከታታይ የሚያካሒደው የዕድሜ፣ የሥራ፣ የአካል፣ የማሕበራዊ ደረጃ፣ የመኖሪያ ቦታን ለውጥ ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ሥነ ሥርዓቶች ሁሉ የሕይወት ዘመን ዑደትሽግግር ናቸው (Gennep, 1960:2-3)፡፡

ብዙ ጊዜ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓት ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን በተከተለ መንገድ የማሕበረሰቡን ባሕላዊ ደንብና ሥርዓት ተከትሎ ይከናወናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Bellእንደሚከተለው ብለዋል፡፡

> የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ልደትን፣ ለአቅመ ሄዋን መድረስን ጋብቻና ሞትን ምክንያት በማድረግ በጋራ የሚከወኑ ሥነ ሥርአቶች ሲሆኑ ሰዎችን ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደሌላ ያሸጋግራሉ፡፡ እነዚህ ሥነ ሥርአቶች አንዳንዴ የሕይወትዑደትበሚል የሚጠሩ ሲሆን ከሰዎች ተፈጥሮአዊ እድገት ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ውልደትን፣ጉርምስናን እና ሞትን መነሻ በማድረግ በማህበረሰቡ ባህላዊ ደንቦች መሰረት የተለያዩ ከበራዎች ይፈፅማሉ፡፡
>
> Rites of passage are ceremonies that accompany and dramatize such major events as birth, coming of age may be loosely linked to biological changes like parturition and puberty. Initiations for boys and girls, marriage, and death; they culturally mark a persons transition from one stage of social life to another. While these rites may be loosely linked to biological changes like parturition and puberty (Bell, 1997:94).

ዋና ዋና ከምንላቸው የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች በተጨማሪ እንደ ማሕበረሰቡ እምነት፣ ባሕልና የሕይወት ፍልስፍና ሌሎች ተጨማሪ ሥርዓቶች ይኖራሉ፡፡

በሕይወት ዘመን ሽግግር ከበራዎች ሦስት አበይት ምዕራፎች አሉ፡፡ መለየት (separation)፣ መሸጋገር (transition) እና መዋሃድ (incorporation) ናቸው(Gennp, 1960:11)፡፡በእነዚህ ምዕራፎች ሰዎች ሲወለዱ ከናታቸው ማህፀን ተለይተው ወደ ምድር ይመጣሉ፤ ተሸጋገሩ

ይባላል፡፡ በሥርዓቱ የሙሉ ሰውነትን ማንነት በማግኘትም ወደ ማሕበራዊ ሕይወት ይዋሃዳሉ፡፡ በመጨረሻም የተዋሃዱትን ማሕበረሰብ በሞት ይለያሉ፡፡ እነዚህ የመለየት፣ የመሸጋገር እና የመዋሀድ ምዕራፎች በሰው ሕይወት አንድ ጊዜ ብቻ የሚያልፉ ሳይሆኑ እየተደጋገሙ የሚመጡ ክስተቶች ናቸው፡፡(Gennep,1960:11)፡፡ሰዎች ሲያገቡ ልጅነታቸው ያበቃል፤ ከቡድናቸው ይለያሉ፡፡ ለባለትዳርነት ግን ይወለዱና አዲስ የማንነት ውህደት ይፈጥራሉ፡፡ ሲወልዱ ለእናትነት ወይም ለአባትነት ይበቃሉ፡፡ ይህ ከአንዱ ቡድን መውጣት እና ወደ ሌላው ቡድን መቀላቀል በከበራና በሥነ ሥርዓት ይታጀባል፡፡

እነዚህ የሕይወት ዘመን ዑደት የሽግግር ከበራዎች የተለያዩ ቡድኖች የየቡድናቸውን እምነት፣ አስተሳሰብና የሕይወት አተያይ ለሌላው ማሕበረሰብ የሚያሳዩባቸው አጋጣሚዎች ናቸው(Sims and Stephens, 2005፡125)::የጉምዝብሔረሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከውናቸው በርካታ ሥርዓቶች እና ፎክሎራዊ ጉዳዮች አሉት፡፡ጥናቱ የሚያተኩረው ግን በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት ላይ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አካባቢ ዳራ

በዚህ ርዕስ ስር ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢ መልካምድር፣ የብሔረሰቡ ታሪክ፣ ባሕላዊ አስተዳደር እና የአምልኮ ሥርዓት በአጭሩ ቀርበውበታል፡፡

### 1.2.1.መልክአምድራዊ ገለጻ

የማንዱራ ወረዳ በ17 የገጠር እና በ2 የከተማ ቀበሌዎች የተዋቀረ ነው፡፡የወረዳው ዋና ከተማ ግልገል በለስ ስትሆን ከተማዋ የዞኑም ዋና ከተማ ናት፡፡ የማንዱራ ወረዳ የሚገኝበት የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በምዕራብ ሱዳን፣ በስተሰሜን የአማራ ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ የኦሮሚያ ክልል እና በስተደቡብ የጋምቤላ ክልል ያዋስኑታል፡፡ወረዳው ከአዲስ አበባ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ 550 ኪ.ሜ ላይ ሲገኝ ከክልሉ ዋና ከተማ አሶሳ 340 ኪ.ሜ ይርቃል፡፡ ወረዳው ሙሉ ለሙሉ(100%) ቆላማ ሲሆን የሙቀት መጠኑም ከ25°c-39°c ይደርሳል፡፡የወረዳው የሕዝብ ቁጥር 36,568 እንደሚደርስ ይገመታል፡፡የወረዳው ነዋሪ 80% የጉምዝ ብሔረሰብ ሲሆንቀሪው20% አማራ፣ አገው፣ ኦሮሞ እና ሽናሻ ናቸው፡፡ከወረዳው ሕዝብ 75% የኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣15% የሃገረሰባዊ እምነት፣ 5% የፕሮቴስታንት እና 5% የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡የወረዳው ሕዝብ  በዋናነት የሚተዳደረውም በእርሻ፣

በእንስሳት እርባታ፣ በንብ ማነብ እና በአሳ ማጥመድ ስራ ነው (World Vision Ethiopia 2011 Assessment Report,2011:4)፡፡

የብሔረሰቡ ቋንቋ ጉምዝኛ ሲሆን ቋንቋውም "እንግሽ ብጋ" ይባላል፡፡ "ብጋ" ማለት ጉምዞች እራሳቸውን የሚጠሩበት ቃል ሲሆን ጉምዝ ያልሆኑትን "ሸዋ" በማለት ይጠራሉ፡፡ ጉምዞች ከጉምዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ አገውኛ፣ አማርኛ እና ኦሮምኛ ይናገራሉ፡፡

### 1.2.2. ታሪካዊ ዳራ

ጉምዝ የሚለው መጠሪያ "ጉምዛ" ከሚለው የጉምዝኛ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "ነበዝ"፣ "ጀግና" ማለት ነው፡፡ ብሔረሰቡ ጉምዝ በሚለው መጠሪያ ከመጠራቱ በፊት በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራ ነበር፡፡ ከነዚህም ውስጥ "ሳየ ሳየ"፣ "ሲ ሲ"፣ "ብጋ"እና "ሻንቅላ" ይገኙበታል(Tsega, 2006:16)፡፡ በኢትዮጵያ የዘር ግንድ አመዳደብ የጉምዝ ሕዝብ በናይሎ ሰሐራ የዘር ግንድ እንደሚመደብ ይታመናል (Bender, 1978:20)፡፡

ጉምዞች እንዳሁኑ በመተከል እና ከማሽ ቆላማ አካባቢዎችላይ ከመስፈራቸው በፊት የጎጃም ደጋማ አከባቢዎችን ይዘው እንደነበር ይነገራል፡፡ይህ ቦታም ጣና ሐይቅን ጨምሮ አገው ምድር የሚባለው አካባቢ እንደሆነ፣ በአካባቢው በነበረ አለመግባባት እና ግጭት አከባቢውን ለቀው ገሚሶቹ አባይን ተሻግረው ወደ ወለጋ በመሄድ በደዴሳ ቆላማ አካባቢዎች እና አሁን ከማሽ ዞን በምንለው ቦታ ሲሰፍሩ የቀሩትም ወደ ጎጃም ቆላማ አከባቢዎች በመሄድ በመተከል አካባቢ መስፈራቸው ይነገራል (Tsega, 2006:15;Wolde-selassie, 2002:61)፡፡

ጉምዞች ከደጋማ አካባቢዎች የለቀቁበትምክንያት ባለመግባባቶችና ግጭቶች እንደሆነ ይገለጻል፡፡ Wolde-selassie, Cerull'ን በመጥቀስ እንደገለጹት ከሆነ ግን አለመግባባቱ ከላስታ ከመጡ አገዎች ጋር ሲሆን አገዎቹ ጉምዞችን አስለቅቀው እራሳቸው በመስፈራቸው መሆኑን አመልክተዋል (Wolde-selassie, 2002:64)፡፡

የብሔረሰቡ አባላት ከየት መጣነታቸውን ወይም ታሪካቸውን የሚነግሩበት የራሳቸው ተረክ እንዳላቸው Wolde-selassie ስለብሔረሰቡ በጻፉት ጽሑፍ ላይ የብሔሩ ተወላጆች እንደተረኩላቸው በመግለጽ አስፍረዋል (Wolde-selassie, 2002:64) ይህን ተረክ በማንዱራ

ወረዳ ቁጥር ሁለት ቀበሌ የሃገር ሽማግሌ የሆኑት ቡዚያ ድቢያ የነገሩኝ ሲሆን እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ ።

> የጥንትአያታችን "ሽዋ" ጉምዝካልሆኑትጋርመንትያሆነውተወለዱ።መንትያዎቹካደጉበኋላጥንካሬያቸውንለማወቅየ ልብስ እጥበት ተወዳደሩ። ጉምዙ ልብሱን በድንጋይ ፊትጎ ሲያበላሸው ጉምዝ ያልሆነው ልብሱ ሳይጎዳ አጠበ እና አሸነፈው። ከውድድሩ በኋላ የመኖሪያ አካባቢ እና የአመጋገብ ምርጫ መጣ። መኖሪያ ቦታ ጉምዙ ቆላማ ቦታ ሲመርጥ ጉምዝ ያልሆነው ደጋማ ቦታ መረጠ። ምግብም ጉምዙ "ፓንጻ" ሲመርጥ ጉምዝ ያልሆነው እንጀራ መረጠ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ በቦታ እና በአመጋገብ ተለያየን (ቃለመጠይቅ፣ 10/8/2007)።

ይህተረክ በWolde-selassie ጽሑፍ ከሰፈረው የሚለየው መወዳደሪያውየፈረስግልቢያመሆኑ ብቻ ነው።

## 1.2.3.ባሕላዊ አስተዳደር

የጉምዝ ብሔረሰብ ሦስት ዋና ዋና ጎሳዎች አሉት። እነሱም "ዲምዛ"፣ "ዳንጉዛ" እና "ዲካሪያ" በመባል የሚታወቁ ሲሆን በውስጣቸውም በርካታ የዘር ሐረጎችን አቅፈዋል።እነዚህ የዘር ሐረጎች ወይንም ንዑሳን ጎሳዎች እስከ ሁለት መቶ እንደሚደርሱ ይገለጻል(ዝክረ ህዳር፣ 2007፡53)።ብሔረሰቡ የጠበቀ ጎሳዊ አደረጃጀት አለው። የአንድ ጎሳ አባላት በአንድ አካባቢ ሲኖሩ የአንድ ዘር ሐረግ አባላት በአንድ መንደር ይሰባሰባሉ።ብዙ ጊዜ የአካባቢውን መጠሪያም በጎሳዎቹ ስም ይሰይማሉ።በአንድ ተሰባስበው የሚኖሩ የጎሳ አባላት የውስጥ ሰላምና መረጋጋታቸውን የሚያስጠብቁበት፣ ባሕልና ህልውናቸውን የሚያስቀጥሉበት እንዲሁም እራሳቸውን ከውጭ ጠላት የሚጠብቁበትባሕላዊ አስተዳደር አላቸው።ይህ ባሕላዊ አስተዳደር በጥንት ጊዜ በስፋት ይጠቀሙበት ነበር።በባሕላዊ አስተዳደሩ የሚሾሙ መሪዎች በሁሉም ሕዝብ ተሳትፎ እና ይሁንታ ይመረጣሉ። የምርጫውን ሒደትም የሀገር ሽማግሌዎች፣ የጎሳ መሪዎች፣ የታወቁ አዳኞች እና ጀግኖች ተሰብስበው ያስፈጽሙታል።በዚህ መልክ የተመረጡ ሰዎች የራሳቸው የሆነ ኃላፊነት ሲኖራቸው አንድ ጊዜ ከተመረጡ በኋላ ለአራት ዓመት ያስተዳድራሉ።ይህ የአስተዳደር ሥርዓትም"ሲያአኚ" ይባላል(ዝክረ ህዳር, 2007፡54)።

በዚህ ሥርዓት የመጀመሪያው ሰው "ጢሳ" በመባል ይጠራል።የ"ሲያአኚ" አስተዳደር ከ"ጢሳ" በመቀጠል ሁለተኛው ሰው "ጋንጥቅ ጢሳ" ሲሆን ይህ ሰው "ጢሳ"ው በሌለበት እሱን የመወከል ሥልጣን አለው።ከሁለቱ ሰዎች በተጨማሪ የአካባቢውን ሰላም የማስጠበቅ ሃላፊነት የሚሰጣቸው ሰዎች ይመረጣሉ። አካባቢውን ለማስተዳደር ይሔዱ የነበሩ ነገሥታትና

ወኪሎቻቸው ይህን ሥርዓት ለአገዛዛቸው መጠቀም ሲጀምሩ ሥርዓቱ እየላላ መምጣቱ ይገለጻል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዘመናዊ አስተዳደር በአካባቢው እየተስፋፋ ሲመጣ የባሕላዊ አስተዳደሩ ድርሻ እየቀነሰ መጣ ሲሉ የሃገር ሽማግሌው ይናገራሉ(ቡዚያ ድቢያ፣ ቃለመጠይቅ፣10/8/2007)፡፡

## 1.2.4. የአምልኮ ሥርዓት

የጉምዝ ሕዝብ የራሱ የሆነ ልዕለሃያል ወይም ፈጣሪ ብሎ የሚጠራው አምላክ አለው፡፡ይህ የጉምዞች አምላክ "ሙሳ" በመባል ይጠራል፡፡ ጉምዞች በአንድ አምላክ የሚያምኑ ቢሆንም ሁሉም ነገር የራሱ አምላክ "ሙሳ" አለው፡፡ የውሃ አምላክ "ሙስ[1] አያ"፣ የእህል አምላክ "ሙስ ታንቃ"፣ የመሬት አምላክ "ሙስ እንድያ"፣ የዛፍ አምላክ "ሙስ ጃ"፣ የሰማይ አምላክ "ሙስ ጋአጉና"፣ የጥጥ አምላክ "ሙስ ጋባ"፣ የዝናብ አምላክ "ሙስ ድማ"፣ የእሳት አምላክ "ሙስ ማንጃ" ፣የሳር አምላክ "ሙስ ግዝያ"…. የሚሉት ለሁሉም ነገር የራሱ የሆነ አምላክ አላቸው፡፡አንድን ሰው ውሃ ቢወስደው የውሃ አምላክ ተጣልቶት ነው ይባላል፤ ለዚህም መስዋእት በማድረግ ይቅርታውን ይለማመናሉ፡፡ከዛፍ ቢወድቅና ቢሰበርም እንደዛው የዛፍ አምላክ ተቆጥቶ ነው ተብሎ ይታመናል ( ዋኪ ጋንድር፣ ቃለመጠይቅ፣ 10/8/2007)፡፡

የጉምዝ ብሔረሰብ በየዓመቱ መስዋእት በማድረግ ከብት፣እህልና ሰውን በሰላም ለሚያኖረው አምላክ "ሙሳ" ምስጋና እና መስዋእት ያቀርባል፡፡ ይህ መስዋእት በክረምት ወቅት በአንድ አካባቢ ያሉ ሰዎች በመሰባሰብ የሚያቀርቡት ነው፡፡ የመስዋእት ሥርዓቱን የሚያስተባብረው እና ሥርዓቱ የሚፈጸምበትን ቀን ለማሕበረሰቡ የሚገልጸው ሰው "ሙስ ግድያ" በመባል ይታወቃል፡፡

ሌላው የብሔረሰቡ የአምልኮ ሥርዓት አካል የሆነው የ"ጋፍያ" ሥርዓት ነው፡፡"ጋፍያ" በመባል የሚታወቁት ሰዎች በብዛት ሴቶች ሲሆኑ በብሔረሰቡ እና በአምላክ(ሙሳ) መካከል ያሉ አስታራቂ፣ ምህረት አምጪና የሚመጣውን የሚተነብዩ ተደርገው ይታመናሉ፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድም ከፍ ያለ ቦታ አላቸው፡፡ ከአምላክ በተሰጣቸው ኃይል የታመሙትን መፈውስ፣ አሟሟታቸው ሳይታወቅ የሞቱ ሰዎችን የሞት ምክንያት ማሳወቅ፣

[1] "ሙሳ" ማለት አምላክ ማለት ሲሆን "ሙስ" ሲሆን "የ" የሚለውን የአማርኛ ቅጥያ ይይዛል፡፡ ለምሳሌ የእንጨት አምላክ ለማለት "ሙስ ጃ" ይላሉ፡፡

ንብረት ለጠፋባቸው የወሰደባቸውን ማሳወቅ፣ መሃን ሴትን እንድትወልድ ማድረግ፣ ህልም መፍታት፣ የሰብል ምርት እንዲጨምር ማድረግ እና አዳኞች የተሳካላቸው አዳኝ እንዲሆኑ ማድረግና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን መፈጸም እንደሚችሉ በብሔረሰቡ ይታመናል(ምናለ፣ ቃለመጠይቅ፣ 10/8/2007)፡፡

## 1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት እንዳደርግ ያነሳሱኝ ዋናዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው በአደኩበት አካባቢ(ማንዱራ ወረዳ) የሚኖሩ የጉምዝ ብሔረሰብ አባላት በወሊድ ጊዜ፣ ሴት ልጅ የመጀመሪያዋን የወር አበባ ስታይ እና በሞት ወቅት የሚፈፅሟቸው ሥርዓቶች በአካባቢው ካሉት ሌሎች ብሔረሰቦች የተለዩ መሆናቸው ትኩረቴን ስለሳበው ነው፡፡

የብሔረሰቡ አባላት የሰርግ ሥነ ሥርዓታቸውን በሚፈፅሙበት ጊዜ ሙሽራዋን ሴት ዘመዶቿና ጉረቤቶቿ አጅበዋት ሙሽራው ቤት የሚያድርሱበት ሥርዓት አለ፡፡በዚህ ሥርዓት ላይ ሙሽራዋን እንዴት ሴት ብቻ ያጅባታል? ዘመዶቿ ብቻስ ለምን ያደርሷታል? ሴቶቹስ ሲመለሱ የያዙትን ቅጠል ለምን በየመንገዱ ይጥላሉ? የሚሉ ጥያቄዎች በውስጤ ይመላለሱ ነበሩ፡፡ በክፍለ ትምህርቱ ቆይታዬ እኒህ ቀደምት ጥያቄዎች ከፎክሎር አንጻር ምላሽ እንደሚያገኙ ተረዳሁ፡፡ለጥያቄዎቹምላሽማበጀት መፈለጌምሌላኛው ምክንያት ሆነ፡፡

ከፍ ሲል ከጠቀስኳቸው የግል ምክንያቶች በተጨማሪ “Seminar in Ethiopian folklore” ኮርስ ስማር የኮርስ ማሟያ ለሚሆን ሥራ በክልሉ ባሉ 5 ብሔረሰቦች የተሰሩ ጥናቶችን ዳሰሳ አካሂጄ ነበር፡፡ በአማርኛ ሥነጽሑፍና ፎክሎርትምህርት ክፍል ድሕረ ምረቃ መርሃ ግብር በብሔረሰቡ ዙሪያ የተሰራ አንድም ጥናት አላገኘሁም ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳትስለ ብሔረሰቡ ባሕል ያለ አንዳች ክፍተት ስለሚኖር ይህን መሙላት አለብኝ የሚል ፍላጐት ስለአደረብኝ በዚህ ርእስ ላይ ለማጥናት ተነሳስቻለሁ፡፡

## 1.4. የጥናቱ አላማዎች

የጥናቱ ዋና አላማ በጉምዝ ብሔረሰብ የሚከወኑ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓትን በማሳየት ከሚከወኑባቸው አውድ አንፃር የሚኖራቸውን ፋይዳ መለየት፣ መግለፅና መተርጐም ሲሆን፤ የሚከተሉት ደግሞ ዝርዝር አላማዎቹ ናቸው፡፡

➢ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችንእና የሚፈፀሙባቸውን አውዶች መግለፅእና መተርጐም፣

➢ በብሔረሰቡ በሚከበሩ ዋናዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት አማካይነት ብሔረሰቡ ስለሕይወት ያለውን አመለካከት ማሳየት፣

➢ ብሔረሰቡ በዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓቶች ውስጥ የሚፈጽማቸውን ልማዶችና ያላቸውን ፋይዳ መግለጽ፣

➢ የእያንዳንዱ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓት የመከበር ምክንያት መግለጽ፡፡

## 1.5.የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. በጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?
2. በብሔረሰቡ የሚፈጸሙ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት የመፈጸማቸው ምክንያት ምንድን ነው?
3. የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት እንዴት ይፈፀማሉ?

## 1. 6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

1. በብሔረሰቡ የሚከናወኑ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ምንነት እና ሥርዓት በማሳየት የብሔረሰቡን ባሕል የማስተዋወቅ ጠቀሚታ አለው፡፡
2. በጉምዝ ብሔረሰብ ባሕል ዙሪያ እንዲሁም ጥናቱ በሚያነሳው ርዕስ ጉዳይ  በትምህርት መስኩ በቂ ጥናት ባለመካሄዱ የተፈጠረውን የዕውቀት ክፍተት በማጥበብ የሚሰጠው ጠቀሜታ ይኖራል፡፡

3. በመስኩ ተጨማሪ ምርምር ለሚያድርጉ ምሁራንም እንደመነሻ ያገለግላል፡፡
4. የዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓትና አከባበር በብሔረሰቡ ማሕበራዊና ባሕላዊ መዋቅር ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ያሳውቃል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በመተከል ዞን በሚገኘው የማንዱራ ወረዳ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ በክልሉ ካሉ ብሔረሰቦች ጉምዝን ከአካባቢም የማንዱራ ወረዳን የመረጥኩበት ምክንያት ያደኩት በዚህ አካባቢ በመሆኑቋንቋውን፣ ባሕሉንና አካባቢውን ስለማውቅ የተሻለ ሥራ መስራት እንደምችል ስላመንኩ ነው፡፡በርዕሰ ጉዳይም በብሔረሰቡ ከሚከናወኑ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ውስጥ ዋና ዋና የሆኑትን፣ የወሊድ፣ የመጀመሪያ የወር አበባ እና የወንድ ልጅ ግርዛት፣ የሠርግ እና የጋብቻ ሥርዓት እንዲሁም የሞትና የተስካር ሥርዓት ተመርጠዋል፡፡ ምክንያቱም የቀሩትን በተመረጡት ውስጥ ማየት ስለሚቻል ነው፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ሥርዓቶች ምን እንደሚመስሉ በመግለፅ ትንታኔ የተካሄደባቸው ሲሆን በሥርአቶቹ የሚታዩ ልማዳዊ ክንዋኔዎችም ትርጓሜ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ከተጠቀሱት ውጭ ያሉትን ሌሎች ባሕላዊ ሥርዓቶች ጥናቱ የማይመለከት ሲሆን በሥርዓቶቹ ውስጥ ያሉ ቃልግጥሞችን እና ቁሳዊ ባሕሎችን በዋናነት አያካትትም::

## 1.8. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭና ተንታኝ ዘዴን ተከትለው የተተነተኑ መረጃዎች የቀረቡበት ሲሆን መረጃዎችን ለመተንተንም ተግባራዊ መዋቅራዊ ንድፈሃሳብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 1.8.1. የናሙና አመራረጥ

የተመረጡት ቀበሌዎችም ሆነ መረጃ ሰጪዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡ ናቸው፡፡ በወረዳው ከሌሎች በተሻለ የብሔረሰቡ አባላት በስፋት የሚኖሩባቸው አምስት ቀበሌዎች በዋናነት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ አምስት ቀበሌዎችም ጀግዳ ፣ ቁጥር ሁለት፣ ደፈሌ፣ ዳቡሀ እና የኢሲሳ ጉጥ ያለበት ገነተ ማርያም ቀበሌ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከተመረጡት ቀበሌዎች ውስጥ ሦስቱ ለመጀመሪያ ዲግሪ መመረቂያ ወረቀት ለመስራት በብሔረሰቡ ባህላዊ ህክምና ዙሪያ መረጃ የሰበሰብኩባቸው ስለነበሩ አሁንም በድጋሚ ልመርጣቸው ችያለሁ፡፡

በመስክ ቆይታዬ ጊዜ በአውዳቸው ተገኝቼ የታደምኩባቸው ሥርዓቶች ስድስት ሲሆኑ ሁለት ተስካር በጂግዳ ቀበሌ እና በኤሲሳ ጎጥ፣ አንድ የሀዘን (የቀብር) ስርዓት በቁጥር ሁለት ቀበሌ የባላንባራስ ጎጥ፣ አንድ የሰርግ ሥርዓት በዳፊሊ ቀበሌ፣ አንድ የልጃገረዶች የመጀመሪያ የወር አበባ ሥርዓት እና ሁለት የውልደት ሥርዓት በዳቡህ ቀበሌ ናቸው፡፡

## 1.8.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለአንድ ጥናታዊ ስራ የሚሆኑ መረጃዎች ቀዳማይ መረጃዎች ከመስክ እና ካልአይ መረጃዎች ከቤተ መፅሐፍት ይሰበሰባሉ፡፡ በዚህ ጥናትም የተዛማጅ ስራዎች ፣የንድፈ ሃሳብ ዳራ እና የአካባቢያዊ ዳራ መረጃዎች ከቤተ መፅሐፍት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ለጥናቱ መሠረት የሆኑት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተሰበሰቡት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው፡፡

### 1.8.2.1. ምልከታ

ምልከታ አጥኚው በሚያጠናበት ቦታ በመገኘት የሚያጠናውን ጉዳይ በማየት፣ በማሽተትና በመዳሰስ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡

በዚህ ጥናትም ምልከታ አንዱና ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ የተመረጠበት ምክንያት የአንድን ብሔረሰብ ባሕል ለመረዳትና ከማሕበረሰቡ ማሕበረ ባሕላዊ አውድ አንፃር ለመተንተን የሚያስችል ወሳኝ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡ በምልከታ አማካኝነት በጉምዝ ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ምንነት፣ ሥርዓቱ እንዴት እንደሚፈፀም እንዲሁም የብሔረሰቡን ባሕላዊ ማሕበራዊ መዋቅር እንዴት ማስጠበቅ እንደሚችል መመልከት ስለሚያስችል ተመርጧል፡፡

ምልከታ እንደሚጠናው ጉዳይ መለያየት እና አጥኝው ከሚያጠናው ባሕል ባለቤት ጋር እንዳለው ቅርበት በሁለት መንገድ ይካሄዳል፡፡ በተሳትፎአዊ ምልከታ እና በኢ- ተሳትፎአዊ ምልከታ፡፡ ተሳትፎአዊ ምልከታ ክዋኔውን ከሚያካሄደው ቡድን ጋር በመቀላቀልና ክዋኔውን በመከወን መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ሲሆን ኢ-ተሳትፎአዊው ምልከታ አጥኝው ዳር ሆኖ በመመልከት መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው (Sims and Stephens, 2005፡220)፡፡ እኔም

መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ቦታው በሄድኩበት ጊዜ ሁለቱንም የምልከታ አይነቶች ተጠቅሚያለሁ፡፡ በተሳትፎአዊ ምልከታ የተስካር እና የመጀመሪያ የወር አበባ ሥርዓትን ተመልክቻለሁ፡፡

በምግብ እና መጠጥ ፣በጭፍራ ሥርዓት እንዲሁም ለሥርዓቱ የድርሻየን በማድረግ በሥርዓቶቹ ላይ ተሳትፊያለሁ፡፡ በተጨማሪም ወላድ አራሶችን በአካባቢው ያሉ ሰዎች አራስ ሴት በሚጠይቁበት መንገድ የጥየቃ ተሳትፎ አካሂጃለሁ፡፡ በኢ-ተሳትፎአዊ ምልከታም የሃዘን ሥርዓቱን እና አንድ ሌላ የተስካር ሥርዓት ተመልክቻለሁ፡፡

በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች ሦስት ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡ የመጀመሪያው መረጃው በአግባቡ ከተሰበሰበ ዐድሎአዊ ከሆነ ግለሰባዊ አስተያየት ይወጣል፡፡ ሁለተኛው የሚሰበሰበው መረጃም ምልከታው በተካሄደበት ጊዜ ያለ መሆኑ ነው፡፡ የመጨረሻው ከመጠይቅ በተሻለ የመረጃ አቀባዩን መልካም ፈቃድ የማይጠበቅበት መሆኑ ነው (Kothrin, 2004:96)፡፡ በሁለቱ የምልከታ ዘዴዎች ለማግኘት ያልቻልኋቸውን መረጃዎች እንዲሁም ከምልከታ በተጨማሪ የማሕበረሰቡን (የከዋኙን) ማብራሪያ የሚሹ ጉዳዮችን በቃለ መጠይቅ ሰብስቢያለሁ፡፡

### 1.8.2.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለመጠይቅ በዚህ ጥናት ውስጥ ከተጠቀምኩባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት መረጃዎችን ስሰበስብ በምልከታ ማግኘት ያልቻልኳቸውንመረጃዎች፣ ግልፅ ያልሆኑልኝን ድርጊቶችና ስሜቶች፣ እንዲሁም የአንዳንድ ክንውኖችን ባሕላዊ ትርጉም ለማወቅ የቃለ መጠይቅ ዘዴ ተጠቅሜያለሁ፡፡

በቃለ መጠይቅ ወቅት ለመረጃ አቀባዮች የምናቀርበው የጥያቄ አይነት መረጃ በምንሰበስብበት አውድና በምንሰበስበው የመረጃ አይነት ላይ የተመሰረተ ነው (Sims and Stephens, 2005:208)፡፡ተመራማሪው በቃለ መጠይቅ ያገኛቸውን መረጃዎች በተለያየ ጊዜ በሚፈጠሩ ተመሳሳይ አውዶች ውስጥ መመርመር አለበት፡፡ አንድ ጉዳይ በተለያዩ መረጃ አቀባዮች ምን ገፅታ እንዳለው መፈተሽ አለበት፡፡ መረጃን ለመመዘን፣ ቅደም ተከተል ለማስያዝ፣ የተደጋገሙ ምላሾች ትኩረት የሳቡ መሆናቸውን ለመረዳት እንዲሁም ተመሳሳይ መረጃዎችን በማጤን የጥያቄዎቹን መልስ ለማዳበር ያስችላል፡፡ በተጨማሪም አንድ ጉዳይ የሚያወሩ የተለያዩ ቃለ መጠይቆችን ለተመሳሳይ መረጃ አቀባዮች በመጠየቅ ምን ምላሽ እንደሚሰጡባቸው ለመለየትና

በማሕበራዊ አውድ መለያየት ምክንያት ሊገኝ የሚችለውን የተለያየ መረጃ ለመረዳትና ለመተርጐም ያስችላል (Goldsteine, 1964:114)፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ በምልከታ የሚታዩ እናትዕምርትነት ያላቸውን ጉዳዮች አውዳዊ ፍቺ ለማግኘት ቃለ መጠይቅ አካሄጃለሁ፡፡

በዚህ ጥናት ብሔረሰቡ ለዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች የሚሰጠውን ፍች ለመረዳት ቃለ መጠይቅ አይነተኛ ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት ቃለመጠይቅን አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች 22 ሲሆኑ ከጾታ ስብጥር አንጻር 8 ሴቶች እና 14 ወንዶች ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል 8ቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ ሰዎቹ የተመረጡት ባላቸው ማህበራዊ ደረጃ እንዲሁም ሥርዓቱ የሚፈጸምላቸውና ሥርዓቱን የሚፈጽሙት ሰዎች የተለዩ በመሆናቸው በክዋኔው ላይ ባላችው ቅርበት ወይም ባለቤትነት ሲሆን፤ ከዕድሜ አኳያም ከ19 እስከ 90 ዓመት ያሉ ሰዎች ተካተዋል፡፡ በተለይም ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በብሔረሰቡ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸውና ስለ ባሕሉ ያላቸው እውቀት  የተመሰከረላቸው ናቸው፡፡

### 1.8.2.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

በዚህ ጥናት ሁለት አይነት የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ አንደኛው መደበኛ በሆነ መልኩ ሰዎችን በቡድኑ ውስጥ ባላቸው ማህበራዊ ደረጃ፣ የጾታ እና የዕድሜ ድርሻ በመምረጥ የተካሄደ ውይይት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ መረጃን በተፈጥሮአዊ መቸት ለመሰብሰብ በተገኘሁባቸው ቦታዎች ተሳታፊዎቹ በጉዳዩ ላይ የሚያደርጉት ውይይት ነው፡፡ ሁለቱንም የተጠቀምኩ ሲሆን ሦስት መደበኛ ውይይቶችን አካሄጃለሁ፡፡ በውይይቶቹም  በሁለቱ ሰባት ሰባት ሰዎች፤ በአንዱ ስምንት ሰዎች በድምሩ ሃያ ሁለት ያህል ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ ይህ ዘዴ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ያልተሟሉ መረጃዎችን ለማሟላት  አግዞኛል፡፡

ባጠቃላይ በምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና በቡድን ውይይት የተገኙት መረጃዎች በመቅረፀ ድምፅ፣ በፎቶ ከሜራና ቪዲዮ ካሜራ ተቀርፀው እንዲሁም በማስታወሻ ደብተር ተጽፈው ተሰብስበዋል፡፡

## 1.8.3. የመስክ ስነ ምግባሮች

አንድ ተመራማሪ የምርምር ስራ ሲሰራ ሊኖረው የሚገባ ሥነ ምግባር አለ፡፡ ይህ ሥነምግባር መረጃ ለመሰብሰብ መስክ በሚወጣበት ጊዜ ጥብቅ መመሪያው ሊሆን ይገባል፡፡ እኔም ይህንን ጥናት ለማካሄድ ወደ ሚጠናው ብሔረሰብ በሄድኩበት ጊዜ በጥብቅ የተመራሁባቸው የሥነ ምግባር መርሆዎች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የጥናቱን ዓላማ በግልጽ ለማሕበረሰቡም ሆነ ለመስክ ረዳቶቼ እንዲሁም ለመረጃ አቀባዮቼ ማስረዳት አንዱ ነው፡፡ ሌላው ሁሉም መረጃ አቀባዮቼ አምነውበት እና ፈቅደው የሰጡኝ መሆኑ ነው፡፡ በጥናቱላይ የቀረቡ ሁሉም መረጃዎች ትክክለኛ እና እውነተኛ ናቸው፡፡ በመጨረሻም በብሔረሰቡ ባሕል መሰረት ተወዳጅ የሆነውን ባሕላዊ መጠጥ አረቄ በመጋበዝ እና በምርቃን ሥርአት ከመረጃ ሰጪዎች ጋር የነበረኝ ቆይታ ተጠናቋል፡፡

## 1.8.4. የመረጃ ትንተና ዘዴ

መረጃዎች አውዳዊ ንድፈ ሃሳብን መሰረት በማድረግ የተሰበሰቡ ሲሆኑ ገላጭ እናተንታኝ ዘዴን በመጠቀም ተገልጸው እና ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በዋናነት መረጃዎችን ለመተንተንና ለመተርጎም መዋቅራዊ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብን (structural functional approach) ጥቅምላይውሏል፡፡ ይህ ንድፈ ሃሳብ ማንኛውም ማሕበረሰብ የሚከውናቸው ፎክሎራዊ ቅንጣቶች ለሚከውነው ማሕበረሰብ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ እንዳላቸው ያወሳል፡፡ በተጨማሪም ማሕበረሰቡ እንደ ማሕበረሰብ እንዲቀጥል የሚያስችሉ መዋቅራዊ ፋይዳዎች ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ ጥናትም በጉምዝ ብሔረሰብ ውስጥ የሚከወኑ የዕድሜ ዘመን ሽግግር ደረጃዎች የማሕበረሰቡን ማህበራዊ መዋቅር ከማስጠበቅ አንፃር የሚኖራቸውን ፋይዳ ከመዋቅራዊ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ አንፃር ተዳሰዋል፡፡

## 1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በመረጃ ስብሰባ ወቅት የገጠሙኝ ችግሮች ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው አንዳንድ የሽግግር ሥርዐቶች (የወሊድ ሥርዓት እና የለውጥ ጋብቻ) "ጎጂ ልማድ" ናቸው በመባል እንዳይፈፅሟቸው ስለሚከለከሉ ለክልከላ የሄድኩ እየመሰላቸው ስጋት ነበረባቸው፡፡ በተለይ የጋብቻ ሥርዓቱን በተመለከተ በወረዳው በብዛት ይፈጸም የነበረው የለውጥ ጋብቻ ነው፡፡ ይህ የጋብቻ አይነት መቅረት አለበት ስለሚባል "ሰርግ ቀርቷል" የሚሉ ሰዎች ብዙ ነበሩ:: ነገር ግን የኔ ዓላማ የነሱን ባሕላዊ አምነት እና አመለካከት "ጎጂ" ብሎ ለመፈረጅ ሳይሆን ሥርዓቶቹን በማጥናት ለትምህርት ግብአትነት ለመጠቀም መሆኑን እየገለፅኩ ለማሳመን እና መረጃዎችን ለማግኘት

ችያለሁ። በተጨማሪ ከዚህ በተያያዘ የገጠመኝ ችግር በዳቡህ ቀበሌ በባሕላዊ መንገድ የወለደችው ሴት ውጭ መውለዷ “ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት ፈጽመሻል” እባላለሁ የሚል ስጋት ስለነበረባት በግልፅነት ላለመናገር ወስና ነበር። ነገር ግን የመጣሁበትን ዓላማ በሚገባ በማስረዳት መረጃውን ለማግኘት ችያለሁ።

ሁለተኛው ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተያያዘ የገጠመኝ ችግር ነው። የመጀመሪያ የወር አበባ ሥርዓት በምመለከትበት ጊዜ ሥርዓቱ የሚፈጸመው በምሽት ነበር። የያዝነው ባትሪ ጨለማውን ማሸነፍ ስላልቻለ ቀረጻ ለማካሄድ ተቸግሬን ነበር። ነገር ግን ከሚነደው እሳት ሳር በመጨመር ለመቅረጽ ተችሏል። በአጠቃላይ አንዳንድ የአከባበር ሥርዓቶች ረዥም ጊዜ የሚወስዱ መሆናቸው እና ሥርዓቶቹ በአንድ ጊዜ የተለያየ ቦታ መከወናቸው ያጋጠሙኝ ችግሮች ነበሩ። ነገር ግን በተቻለ መጠን ሥርዓቱን የሚፈፅሙ ሰዎችን ስለ ጥናቱ ዓላማ በማስረዳትና በምልከታ ማግኘት ያልቻልኳቸውን መረጃዎች በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት በመሰብሰብ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ተሞክሯል።

በመጨረሻ ኤሲሳ በተካሄደው የተስካር ሥርዓት ከወረዳው የመጣው አፈ ጉባኤ የመረጃ መሰብሰብ ስራዬን አቋርጦኝ ነበር። ነገር ግን ከወረዳ አስተዳደር የተፃፈልኝ የህጋዊነት ደብዳቤ በእጄ ስለነበር በማሳየት መግባባት እና ስራዬን መቀጠል ችያለሁ። የህጋዊነት ደብዳቤው በእጄ መኖሩ በመግባባት ችግሩን ፈትቶ ስራውን ለመቀጠል አስችሎኛል።

## 1.10. የመስክ ተሞክሮ

የጥናቴን ዋና መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ቦታው የሄድኩት በ23/05/2007 ዓ.ም ነበር። ከዚህ ቀን በፊት ግን በ18/05/2007 ዓ.ም ከትምህርት ክፍላችን ለዞኑ እና የወረዳ አስተዳደሩ የድጋፍ ደብዳቤ አስጽፌ ነበር። በ25/5/2007 ዓ.ም የማንዱራ ወረዳ አስተዳደር ዘንድ በመቅረብ ደብዳቤውን አስገባሁ። ነገር ግን ከወረዳው አስተዳደር የምፈልገው ደብዳቤ ከመፃፉ በፊት በ25/05/2007ዓ.ም በዳፊሊ ቀበሌ በምሽት የሚፈፀም ሰርግ (የለውጥ ጋብቻ) ሥርዓት መኖሩን በቀበሌው ያሉ ሰዎች ገለፁልኝ። በዚህ ቀን ከመስክ እረዳቴ ጋር በመሆን ከወረዳው ዋና ከተማ ግልገል በለስ ወደ ማንዱራ ከተማ በመሄድ ወደ ዳፊሊ ቀበሌ በእግር ጉዞ ጀመርን። በቦታው ስንደርስም ሥርዓቱ በድብቅ እየተፈጸመ ነበር። በቀበሌው ያሉ ዘመዶቼን በመያዝ ሰዎቹን

ስለማንነቴ እና ዓላማዬ በማስረዳት ሥርዓቱን እንድከታተል ከብዙ ጥረት በኋላ አሳመንኳቸው፡፡ ነገር ግን በሥርዓቱ ላይ ድምጽ መቅዳትም ሆነ ፎቶ ማንሳት እንዲሁም በጹሑፉ ላይ ስማቸውን መጥቀስ እንደማልችል አስጠንቅቀውኝ ተስማምቼ በመመልከት ብቻ መረጃ ሰብስቤ ተመለስኩ፡፡

በ28/05/07ዓ.ም ከወረዳው አስተዳደር የህጋዊነት እና የድጋፍ ደብዳቤ አስፃፍኩ፡፡ ለመስክ እረዳትነት የመረጥኩት በዛው ወረዳ ተወልዶ ያደገ፣ ቋንቋ እና ባሕሉን የሚያውቅ እንዲሁም በማሕበረሰብ ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪውን ተመርቆ በዞኑ አስተዳደር እና ፀጥታ መምሪያ የሚሰራ ሰው ነው፡፡

ምልከታ የተካሄደባቸው ሥርዓቶች ላይ ለመገኘት የተደረጉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው በተመረጡ ቀበሌዎች አንድ ዙር ጉዞ ማድረግ፡፡ በጉዞዬ እራሴን ለሰዎች ለማስተዋወቅ፣ አካባቢውን በደንብ ለማወቅ እንዲሁም ሥርዓቶቹ በቅርቡ የሚፈፀሙ ከሆነም መረጃ ለማግኘት ረድቶኛል፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉኝ መሳሪያዎች ማለትም መቅረጸ ድምጽ፣ ፎቶ እና ቪዲዮ መቅረጽ የሚችል መሳሪያ እንዲሁም መረጃዎችን ማደራጃ ላፕቶፕ ኮምፒውተር መስራታቸውን በማረጋገጥ አዘጋጀሁ፡፡

የሁለተኛው ጉዞዬ በ7/06/2007ዓ.ም ጂግዳ ቀበሌ ነበር፡፡ በዚህ ቀበሌ ዱቡንካ ጎጥ የሚካሄድ የተስካር ሥርዓት ነበር፡፡ በዚህ ሥርዓት ላይ ለመገኘት በዋዜማው ቀን የደረስኩ ሲሆን በሥርዓቱም በጭፈራና በምግብ ሥርዓቱ ተስተፍአዊ ምልከታ አካሄጃለሁ፡፡ የመስክ እረዳቴ በቦታው ካሉ የሥርዓቱ ባለቤቶች ጋር ቅድመ ትውውቅ ስለነበረው ጥሩ ጊዜ እንዳሳልፍ እና መረጃዎችን በአግባቡ እንዳገኝ እረድቶኛል፡፡

ሦስተኛው ጉዞዬ ወደ ዳቡህ ቀበሌ ነበር፡፡ ይህ ቀበሌ ለመጀመሪያ ዲግሪ መረጃ የሰበሰብኩበት ቦታ ነበር፡፡ በዚህ ቀበሌ ሰለሞን እና ኤሊኝታ የተባሉ ግለሰቦች በዚህ ጊዜ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ስለነበሩ መልካም አቀባበል አድርገውልኛል፡፡ በዚህ ቀበሌ የተመለከትኩት ሁለት የወሊድ ሥርዓት እና አንድ የመጀመሪያ የወር አበባ ሥርዓት ነው፡፡ ወላዶቹን ለማየት ወደ ቦታው ስሄድ በአካባቤው ያሉ ሰዎች በሚያደርጉት ሥርዓት መሰረት አረቂ እና የገላ ሳሙና

በመያዝ “እንኳን ማርያም ማረችሽ” እንደሚባለው ወላዶችን የእንኳን ደስ አላችሁ ስሜቴን ገልጬ ነበር የተቀላቀልኩት፡፡

በአራተኛነት የታደምኩት የተስካር ሥርዓት ነው፡፡ ሥርዓቱ በኤሲሳ ጎጥ የተካሄደ ሲሆን ከጅግዳው የተስካር ሥርዓት የሚለይበት መንገድም ነበረው፡፡ ሟች በለጋ ዕድሜዋ ስለሆነ የሞተችው በሥርኣቱ ምንም አይነት የጭፈራ ሥርዓት አልነበረም፡፡ በተቃራኒው ፀጥታ የሰፈነበት እና የሀዘን ድባብ ያጠላበት ነበር፡፡ ተስካሩን ለሚያወጣው ሰው የአካባቢው ሰው እንደሚያደርገው ገንዘብ በሚጣልበት ቦታ ገንዘብ በማስቀመጥ የሃዘናቸው ተካፋይ መሆኔን በመግለፅ ወደ ሥርዓቱ ተቀላቀልኩ፡፡

በዚህ ሥርዓት የወረዳው የፀጥታ ሰዎች ወደ ቦታው ሲመጡ የሀዘን ድባቡ ወደ ግርግር ተቀየረ፡፡ ምክንያቱም በቁጥር ሁለት ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት የሀብታሙ ሂስ ድንገት መሞት ነበር፡፡ የሟች ቤተሰቦች እና ዘመዶች የተስካሩ ሥርዓት ሳይጠናቀቅ ፈጥነው ወደ አካባቢያቸው ተመለሱ፡፡ የሞት መልካም ባይኖረውም ለኔ ግን መልካም አጋጣሚ ነበር፡፡ በነጋታው 15/06/2007 ዓ.ም ከመስክ ረዳቴ ጋር ወደ ሀዘኑ ቤት አቀናን፡፡

የቁጥር ሁለቱ የሃዘን ሥርዓት አምስተኛው ጉዞ ማለት ነው፡፡ ከ30 ደቂቃ የእግር ጉዞ በኋላ ወደ ቦታው ስንደርስ የቀበሌው አስተዳዳሪ እና ፖሊስ ወደ እነሱ አስጠሩን፡፡ የሀዘን ቦታው የሚያስፈራ ድባብ ነበረው፡፡ የመንግስት አካላት ካስጠሩን በኋላ የመጣንበትን ምክንያት ሲጠይቁን አስረዳናቸው፡፡ ነገር ግን ዓላማዬን ቢረዱትም የሟችን ሞት ምክንያት ተከትሎ ችግር እንዳለ ገለፁልን፡፡ ሟች ታሞ ውሎ ሳያድር በድንገት ነበር የሞተው፡፡ አሟሟቱያጠራጠራቸው ቤተሰቦቹ ወደ “ጋፍያ” “አዋቂ” ቤት በመሄድ የሞቱን ምክንያት ሲጠይቁ ካሁን በፊት የነበሩት ጠበኞች ደግምት “ግጭህ”አስደርገውበት መሆኑ ተነገራቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች ገድለዋል በተባሉ ቤተሰቦች ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ስጋት ነበረባቸው፡፡ መጨረሻ ላይ ይህን ድባብም ማየት ግድ እንደሆነ እና እንደምፈልግ ስገልፅላቸው የሟችን ወንድም አስጠሩልኝ፡፡ በዚህ ጊዜ የሟች ወንድም ሞቅ ያለ ሰላምታ ሰጠኝ፡፡ የምፈልገውን ነገር ሥርዓቱን መመልከት እንደሆነ ሰዎቹም እኔም ተራ በተራ አስረዳነው፡፡ ምላሹ ግን ያልጠበኩት ነበር፡፡ የሟች ወንድም አያና ባሮ እንደሚያውቀኝና እስከ 6ተኛ ክፍል አብረን እንደተማርን ነገሮኝ እንዳስታውሰው ጠየቀኝ፡፡ ሟችን ማስታወስ ባልችልም

አያናን ግን ከነሱ ቀበሌ ወደ ማንዱራ ወረዳ ትምህርት ቤት ሲመጡ ያመጡልን ስለነበረው የእንኮይ ፍሬ ሲያስታውሰኝ የተወሰነ ለማስታወስ ችያለሁ፡፡ ይህ አጋጣሚ በሟች ቤተሰቦች እና ገድለዋል በተባሉት ወገኖች ችግር ተፈጥሮ አደጋ ይደርስባታል የሚለውን ስጋት ስለቀነሰው ከአያና ጋር ወደ ለቅሶው ቤት አቀናን፡፡ በዚህ ሁኔታ ሥርዓቱን በመመልከት መረጃዎቹን ሰብስቤ ተመልሻለሁ፡፡

ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ቦታው የሄድኩት በ28/07/2007ዓ.ም ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ መረጃዎችን መተንተን ጀምሬ ስለነበር ብዥታ የፈጠሩብኝን ጉዳዮች በቃለ መጠይቅ ያገኘሁበት ነበር፡፡ በ12/08/2007 ዓ.ም ባጠቃላይ ከአባባቢው መረጃ የማሰባሰብ ስራ አጠናቅቄ ተመልሻለሁ፡፡

በመስክ ተሞክሮ ማጠቃለያ ላይ ማስፈር የምፈልጋቸውና ሌሎች አጥኚዎች ልብ ቢሏቸው መልካም ነው ብዬ የማስባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው የጥናት ርእስ ከመመረጡ በፊት ጥናት ሊደረግባቸው ወደ ታሰቡ ቦታዎቸ በመሄድ ቅኝት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሁለተኛው ከሚመለከታቸው አካላት የተጻፉ የድጋፍ ደብዳቢዎች በመስክ ስምሪት ላይ ሁሉ ከአጥኚው ጋር መለየት የሌለባቸው መሆኑን አስተውያለሁ፡፡ በመጨረሻ የፎክሎር አጥኚ ለጥናት የሚያውቀውን ባህል እና ቋንቋ፤ የሚያውቀውን አካባቢ ቢመርጥ ስራው የተሻለ እንደሚሆን መረዳት ችያለሁ፡፡[2]

---

[2]ይህን ሃሳብ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ field method የተባለውን ኮርስ ሲያስተምሩ የገለፁልን ሃሳብ ቢሆንም በመስክ ቆይታዬ አካባቢውን የማላውቀው ቢሆን ኖሮ ምን ያህል እንደሚያስቸግረኝ በመገመት ሃሳቡን ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

# 2. የንድፈ ሃሳብና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

## 2.1. የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

በዚህ ክፍል ስር ከጥናቱ ጋር የተያያዙ ከበራ እና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦች ቀርበውበታል፡፡ መረጃዎች የተሰበሰቡባቸው እና የተተነተኑባቸው ንድፈ ሃሳቦችም ተዳሰዋል፡፡

### 2.1.1. የከበራ (ritual) ምንነት

ሰዎች በሚኖርበት አካባቢ በሚፈጥሩት መስተጋብር ማሕበራዊና ባሕላዊ ድንበር ያበጃሉ፡፡ በዚህ ድንበር ውስጥም የኔ፣ የኛ የሚያሰኛቸውን ቡድን ይመሰርታሉ፡፡ በቡድኑ ውስጥ የሚኖራቸው ሓይማኖታዊ፣ ተፈጥሮአዊና ሌሎችም ክስተቶች ምክንያት በማድረግ በባሕላዊ ሥርዓቱ መሰረት ከበራ ያዘጋጃሉ፡፡ከበራ የምንለውን ሃሳብ ብዙዎች ከሓይማኖታዊ ሥርዓት ጋር እንደሚያገናኙት በመግለፅ ስለምንነቱ "ከበራ በአንድ መዋቅር ውስጥ የተለያዩ ገፅታዎችና ባህሪያትን በያዘ መልኩ አንዱ ከአንዱ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ነው" (Rappaport, 1992:249) ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ከበራዎች በሰዎች ሕይወት ሲወለድ ጀምሮ እስኪሞት ድረስ (ከሞት በኋላም በተሰካር ይመጣል) የሚኖሩ፤ ከመደጋገማቸው የተነሳ እንዳንድ የሕይወት ገጽታ የሚቆጠሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ብዙ ጊዜ ከበራ በአንድ ቡድን ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከወን ልማድ ሲሆን የተደራጀና በቡድኑ ውስጥ የራሱ የሆነ ተግባር ያለው ነው፡፡ ለሚከውኑት ሰዎችም የቡድን አባልነታቸውን ለቡድኑ አባላትም ሆነ ለውጭ ተመልካቾች የሚያሳውቁበት እና የማንነት መገለጫቸው ነው (Sims and Stephens, 2005: 95)፡፡

ከበራ ሰዎች በእለት ተእለት የህይወት ገጠመኝ እና በረጅም ጊዜ የህይወት ልምድ ያካበቷቸው አስተሳሳቦች፣ አመለካከቶች፣ እምነቶች እና የእሴቶቻቸው ውጤቶች ይፋ የሚሆኑበት ነው፡፡ በብዛት ቡድኑን የሚያሳትፍ በቃልም ሆነ በአካል እንቅስቃሴ የሚገለፅ ልማዳዊ ሥርዓት ነው፡፡ "ማሕበረሰቡ የሚከውነው ከበራ ነው ካልን እንዲከውኑት የሚያሳምን እና የሚገፋፋ፤ ሁሉም አባላት የሚጋሩት እምነት እና እሴት ሊኖር ይገባል"ብለዋል፡፡ "In order for here to be a

ritual, then there must be a set of beliefs and values that members of a group accept and want to have reinforced" (Sims and Stephens, 2005:95).

በአንድ ክበራ አንድን ግለሰብ የየትኛው ቡድን ቋንቋ ተናጋሪ እንደሆነ፣ ማሕበራዊ ደረጃውን እንዲሁም ውስጣዊ ማንነቱን መናገር እንችላለን፡፡ በክበራ ወቅት ይህ የሚሆንበት ምክንያት አንድ ሰው ከፍ ሲል የተገለፁትን ማንነቶች በሙሉ በክበራ ጊዜ ሊያወጣቸው፣ ሊገልፃቸው ስለሚችል ነው፡፡

በአጠቃላይ ግን የሰው ልጅ አጠቃላይ ውስጣዊ (ሞራል፣ እሴት፣ እውቀት፣ እምነት) ማንነት በክበራዎች ሥርዓት ላይ ይንፀባረቃል፡፡ የተለያዩ ምሁራን ክበራን በተለያየ መንገድ ይከፍሉታል፡፡

ክበራዎች ከሚከወኑባቸው አውዶች አንፃር በሁለት ይመድባሉ፡፡ የከፍተኛ አውድ ክበራ (high context) እና የዝቅተኛ አውድ ክበራ (low context)፣ የከፍተኛ አውድ በተደራጀና በታቀደ መልኩ የሚከወን ሲሆን የዝቅተኛ አውድ ባልተደራጀና ባልታቀደ መልኩ እንዲሁ የሚካሄድ ነው (Sims and Stephens, 2005: 98-99)፡፡

አንድማሕበረሰበለሚከውነውክበራአመጣጥመነሻእናፋይዳየሚሰጠውማብራሪያእናምክንያትግልፅነት ናግልጽአለመሆንክበራዎችንሓይማኖታዊናሓይማኖታዊያልሆኑበማለትለመክፈልእንደሚያስችለንH omans Malinowskiንበመጥቀስያስረዳሉ (Homans, 1941:165)::ከዚህበተያያዘበክበራዎችላይድንበርአበጅቶመለየትእጅግአዳጋችነው፡፡ሰዎችለአንዳንዶቹ ለምንእናእንዴትእንደሚያከብሯቸውሲገልፁሌሎቹንልማድስለሆነእንደሚፈፅሟቸውይናገራሉ (Homans, 1941:167)፡፡

Bell ክበራን በስድስት ዋና ዋና ዘርፎች መድበውታል (Bell, 1997:94-123)፡፡

1. የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር (the rites of passage) ይህ የክበራ አይነት የሰው ልጅ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ሲሸጋገር የሚፈፀመው ክበራ ነው፡፡
2. ዓመታዊ ክበራዎች (calenderical rites) ማሕበራዊ ቡድኑ በጋራ የሚያከበረው ሲሆን የጊዜያትን፣ ወራትንና አመታትን መቀያየር ምክንያት በማድረግ የሚከበር ነው፡፡

3. ለመስዋእት ማቅረቢያ የሚከበር (rites of exchange and communion) ይህ የከበራ አይነት ለሓይማኖታዊ ከበራ ጥሩ ምሳሌ ነው። ሰዎች ምላሽ ጠብቀው ለአምላካቸው የሚያደርጉት ሥርዓት ነው።
4. ከበሽታ ለመፈወስ የሚከወኑ (rites of afflicton) ሰዎች የሚገጥማቸውን ህመም ከመለኮታዊ ኃይል ጋር ያያይዙታል። ምህረት ለማግኘትም ከበራዎችን ያካሄደሉ።
5. ጾምን ተከትለው የሚፈጸሙ (feasing, fasting and festivals) በፆም ወቅት ሰዎች የተወሰኑ የምግብ አይነቶችን ከመብላትና ካለመብላት ይገደባሉ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚከወኑ ሥርዓቶችን የሚያካትት ነው።
6. ፖለቲካዊ ከበራዎች (political) ከፖለቲካ መሪዎች እና የፖለቲካ አስተሳሰቦች ጋር በተያያዘ የሚከበሩ ናቸው።

ከተገለጹት ስድስት የከበራ አይነቶች ይህ ጥናት የሚያተኩረው በህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር (the rites of passage) ላይ ይሆናል።

## 2.1.2. የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ምዕራፎች

አንድ ሰው በምድር ሲኖር ተፈጥሮአዊ ዑደትን ተከትለው በየጊዜው የሚመጡ ለውጦች አሉት። ለውጦቹ የአካል፣ የስነልቦና፣ የአስተሳሰብ፣ የማሕበራዊ ደረጃና የባህሪ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህን ለውጦች ሰዎች ትእምርታዊና ምስል ከሳች በሆኑ ሥርዓቶች ይከውኗቸዋል። አንድ ሰው በማሕበረሰቡ ውስጥ ሲኖር ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ከአንድ የዕድሜ ዑደት ደረጃ ወደ ሌላ ሲሸጋገር ከማሕበረሰቡ እውቀት እና ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል። ተፈጥሮአዊ ለውጡ በሕህላዊ ሥርዓት ማሕበራዊ ተቀባይነት ማግኘት ይኖርበታል። ስለዚህ ሃሳብ ምሁራን ከጻፉት ውስጥየሚከተለውን ላቅርብ። “በአካል መወለድ አንድ ጉዳይ ሲሆን ማንነቱ በሚገባ ተለይቶ፤ በማሕበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት አግኝቶ እንደ አንድ አባል መቆጠር ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው” “Physical birth is one thing; being properly identified and accepted as a member of the social group is another”(Bell,1997:94)። አንድ ሰው ማሕበረሰቡ በጊዜው እውቅናና ተቀባይነት ካልሰጠውበስተቀር በአካላዊ አቋም፣ በፊት ገጽታ እና በጸጉር ብቻ በማሕበረሰቡ የትልቅ ሰውነት ደረጃ አያገኝም።

በማነኛውም ማሕበረሰብ ውስጥ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሓይማኖታዊ እና ተፈጥሮአዊ ደረጃዎች ይኖራሉ። በዛ ማሕበረስብ ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦችም በተለያዩ ጊዜያት

በነዚህ ደረጃዎች ያልፋሉ። የሰው ልጅ ከሚያልፍባቸው ዋና ዋና ሽግግሮች ውስጥ መወለድ፣ ለአቅመ ሔዋንና ለአቅመ አዳም መድረስ፣ ማግባት እና መሞት ይጠቀሳሉ (Bell,1997; 94)። ከሚኖሩበት ሃገር ወደሌላ ሃገር መቀየር፣ ከኮሌጅ ወይም የከፍተኛ ትምህርት ቤት ትምህርት ማጠናቀቅ፣ በሓይማኖት ትምህርት ማእረግ ማገኘት እና የመሳሰሉ በማሐበረሰቡ ውስጥ የሚና እና የማሕበራዊ ደረጃ ለውጥ የሚያስከትሉ ለውጦች የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ናቸው ማለት እንችላለን። ከዚህ ተያይዞ ለሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር በሚፈጸሙ ከበራዎች የግለሰቦችን ማንነት መቅረጽ፣ ማሕበራዊ መዋቅሩን ማስጠበቅና ባሕላዊ እሴቶችን ማስከበር እንደሚያስችል (Bell, 1997:94) ይገልጻሉ።

በማንኛውም የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች የሚኖሩ ሦስት ምዕራፎች አሉ። መለየት (separation)፣ መሸጋገር (transition) እና መዋሃድ (incorporation) ናቸው (Gennep,1960:11)። (Gennep,1960:viii) አክለውም እነዚህ ምዕራፎች በሁሉም ሽግግሮች እኩል ሚና የላቸውም በማለት ይገልጻሉ። መሸጋገር (transition) በመጀመሪያ ልጅን ማርገዝ ላይ እና መዋሃድ (incorporation) በመጀመሪያ ጋብቻ ጊዜ ይጎላል

## 2.1.2.1. መለየት (separation)

አንድ ስው ከነበረበት ማንነት፣ አስተሳሰብ፣ ማሕበራዊ ደረጃና ሚና ወደ ሌላ ማንነት (የሆነነት) ሲቀየር የሚፈጠሩ ለውጦች አሉ። መለየት የምንለውም ከነበረው ሁለንተናዊ ውህደት የሚፈጽመው ፍች ነው። በሕይወት ዘመን ዑደት ስርዓት ጊዜ መለየቶች ተደጋግመው ይመጣሉ። ሰው ሲወለድ ከናቱ ማህጸን ይለያል፣ ሲያገባ ከብቸኝነት ይለያል፣ ሲሞት ከህይወት ይለያል።

## 2.1.2.2. መሸጋገር (transition or liminality)

መሸጋገር መለየትን ተከትሎ የሚመጣ ምዕራፍ ነው። ይህ ደረጃ ከነበሩበት ማንነት ተለይተው ወደ አዲሱ ማንነት ሳይቀላቀሉ ያለ አጉል ወቅት ነው። በሁለት የተደራጀ ማሕበራዊ ቡድን መካከል ያለ ክፍት ቦታ በመሆን ለማሕበረሰቡም ሆነ ለግለሰቡ በግልጽ የማይታወቅ ነገር ግን አስቸጋሪ ወቀት ነው። ይህ ደረጃ ካንዱ ቡድን ተነጥለው ወደ ሌላ በመቀላቀልና በአዲሱ ቡድን ተቀባይነት በማግኘት የሚና ድርሻቸው ያልተለዩበትበት ነው (Bell, 1997:95)።

### 2.1.2.3. **መዋሃድ** (Re incorporation)

ከስያሜው እንደምንረዳው መዋሃድ ከአንድ ቡድን ወይም ማንነት ጋር የሚደረግን ውሕደት ያሳያል። ይህ ምዕራፍ በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ከበራዎች ሥርዓት ላይ በግልጽም ሆነ ትዕምርታዊ በሆነ መልኩ የምናገኘው ነው። ሰዎች በአለባበሳቸው፣ በሚመገቡት ምግብ ወይም በሚከውኑት ተግባር ከአንዱ ማሕበራዊ ደረጃ ተነጥለው ፤የሽግግር ጊዜአቸውን አጠናቀው ከአዲስ ማንነት ጋር ውሕደት ይፈጽማሉ። ሰዎች በከበራው ወቅት ውሕደትን ሲፈጽሙ የተቀላቀሉትን ቡድን ህግና ደንብ አክብረው ባሕላዊ ሥርዓቱን ማስቀጠል እንዲችሉ ይሆናል።

### 2.1.3. **የአውድ ተኮር ጥናት መሰረቶች**

አንድን ፎክሎራዊ ቅንጣት ስለምንነቱ፣ ስለተግባሩና የክዋኔ ሂደቱና ስርዓቱ ለመናገር የሚከወንበትን ማሕበራዊና ባሕላዊ አውድ ማወቅ ይኖርብናል። የአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ክዋኔን ምንነት ለመረዳት የሚከወንበትን አጠቃላይ ገጽታ ወይም ማሕበራዊ አውድ መረዳት ወሳኝኝ ነው። ስለ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ጥሩ ትንታኔ ለመስጠት የሚቀርብበትን ባሕላዊ፣ ማሕበራዊና ሁኔታዊ አውድ ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው። ተመሳሳይ ጉዳይ ተደጋግሞ ቢከወን ወይም በተለያዩ ሰዎች ቢከወን አንድ አይነት ፍች ማግኘት ስለማይቻል የሚቀርብበትን አውድ መሰረት ያደረገ ትንተና ማካሄድ ያስፈልጋል (Ben Amos,1993:210):: እኒህ ሰው አያይዘውም “Context in context” በሚለው ጽሑፋቸው Bascomን በመጥቀስ የአንድን ፎክሎር ተግባር ስንገልጽ የሚከወንበትን ማሕበራዊ አውድ ካላገናዘብን የማይቻል መሆኑን አስፍረዋል(BenAmos,1993:209)። ይህ ጥናትም የጉምዝ ማህበረሰብ የሚፈጽማቸውን ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃወች ሥርዓትን ማሕበራዊ፤መዋቅራዊ ፋይዳ የሚመለከት ስለሆነ ጥናቱ አውድን መሰረት አድርጓል።

(Bauman, 1983:367) አንድ ፎክሎራዊ ጉድይ በሚከወንበት አውድ ውስጥ ሲጠና መመሪያ ሊሆኑ የሚገቡ ወይም የጥናታችን መታገኒያ ልናድረጋቸው የሚሹ በማለት ስድስት ነጥቦችን ዘርዝረዋል።

1. **ፍቻዊ አውድ**፡-ይህ የአውድ አይነት በዋናነት የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። ማሕበረሰቡ ስለሚከውናቸው ልምዶችና እውቀቶች ምን

ግንዛቤ እንዳለው፣ እንዴት እንደሚረዱት የየትኛውን የሕይወት ገጽታ እንደሚያሳዩ እና ለመከወን ምን እንዳነሳሳቸው ለመገንዘብ የሚያስችል ነው።

2. **ተቋማዊ አውድ፡**-ሁለተኛው የአውድ ተኮር ጥናት መታገኒያ ሲሆን ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ሲሆን ጉዳዩ የሚከወንበት ተቋም ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ ወይስ ሓይማኖታዊ መሆኑን ከመመርመር ባሻገር ምን አይነት ተቋማዊ ፋይዳ ያበረክታል የሚለውን ይመለከታል።

3.**የተግባር ሂደት አውድ**፡-አውዳዊ ጥናት ስናካሂድ የሚታይ ሌላው ጉዳይ ሲሆን ትኩረቱም የሚጠናው ጉዳይ ከሌላው የፎክሎር ቅርጽ ጋር እንዴት ይዛመዳል የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። የሚጠናውን ጉዳይ ከሌላው ቅርጽ ጋር ለመለየት ማሕበረሰቡ የሚጠቀምበት ስያሜ ምን እንደሆነ የሚታይበት ነው።

4.**ማሕበራዊ መሰረት**፡-ይህ ንኡስ ክፍል ለአውድ ተኮር ጥናት መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የሚጠናው ጉዳይ የሚከወነው በየትኛው የማሕበረሰብ ክፍል እንደሆነ? የትኛውን ማሕበራዊ ደረጃ እንደሚያሳይ? በክዋኔው የሌላው ማሕበረሰብ ተሳትፎ ምን እንደሆነ በመረዳት የተሻለ አውደዊ ትንታኔ ለመስጠት ያስችላል።

5.**ግለሰባዊ አውድ**፡-በዋናነት የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከግለሰብ ኑሮ፣ ሃሳብና ስሜት ጋር እንዴት ይሄዳል? የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። በመሆኑም የግለሰብ ስሜትን የመግለጽ ሀቅማቸውንና ፎክሎራዊ ጉዳዩ ለግለሰቦች የሚሰጠውን ግምት መመርመር ያስችላል።

6.**ሁኔታዊ አውድ፡**-ፎክሎራዊ ቅርጹ የሚከወነው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። ይህ የአውድ አይነት ጉዳዩ ለምን በዚያ አጋጣሚ እንደተከወነና በዚያ ሁኔታ ምን ትርጉም እንዳለው የሚያሳይ ነው።

እነዚህን ስድስት ነጥቦች (Ben Amos,1993:216) በሁለት ያጠቃልሏቸዋል። "ባሕላዊ አውድ" እና "ሁኔታዊ አውድ" በማለት። ባሕላዊ አውድ የሚባለው ሌሎችን የአውድ አይነቶች የሚያቅፍ ሲሆን የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚቀርብበት ሰፊ ገጽታ ነው። ክዋኔው የሚውክላቸው ነገሮች፣ የሚከወነው ጉዳይ፣ የሚቀርብበት ማህበራዊ ደንብ፣ የተሳታፊዎች የእምነት ሥርዓት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና የንግግር ስልት፣ የከዋኞቹ እውቀትና የሥነምግባር ህጎችን ያካትታል። ሁኔታዊ አውድ ደግሞ የሚከወነው ጉዳይ የሚቀርብበትን ማሕበራዊ ሁኔታ ይመለከታል። ብዙ ጊዜም ቃላዊ ከሆኑ ክዋኔዎች ጋር ይገናኛል። ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችም በነዚህ አውዶች መሰረት የተሰበሰቡ ናቸው።

## 2.1.4. የተግባራዊ መዋቅራዊ ንድፈ ሃሳብ ምንነት

ሁሉም ፎክሎራዊ ጉዳይ እንደሚከወንበት ማሕበራዊና ባሕላዊ አውድ ለሚከውነው ማሕበረሰብ የሚኖረው ጠቀሜታ አለ፡፡ የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ትኩረትም አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ በሚከወንበት ማሕበረሰብ ውስጥ ለቡድኑ አባላት የሚኖረው ፋይዳ ወይም ተግባር ላይ ነው፡፡ አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ለመተንተን በማሕበረሰቡ ውስጥ ያለውን ተግባር ማወቅ ቀዳሚ ጉዳይ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም የፎክሎር ተመራማሪው የፎክሎሩን ምንነት ብቻ ከማየት በተጨማሪ ለማሕበረሰቡ ምን እንደሆነ፣ ምን አይነት ትርጉም እና ፋይዳ እንዳለው መገንዘብ ይኖርበታል (Sims and Stephens,2005:175)፡፡ ፎክሎር እንደ ፎክሎሩ አይነት እና እንደ ሚከወንበት አውድ የተለየ ተግባር አለው፡፡ ፈቃደ የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ አቀንቀኝ የሆኑት ፎክሎረኛ Bascomን በመጥቀስ ፎክሎር ሁሉንም ዘውጎች ሊያማክሉ የሚችሉ አራት ዋናዋና ተግባራት እንዳሉት ይጠቅሳሉ፡፡ ይሀውም የማስተማር፣ የማምለጥ (ማምለጭ)፣ የመጠበቅ ወይም የመቆጣጠር እና የማረጋገጥ (የማጽደቅ) ናቸው (ፈቃደ፣ 1991:16-20)፡፡

ይህ ጥናትም የጉምዝ ብሔረሰብ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን አስመልክቶ የሚከውኗቸው ሥርዓቶች ለማሕበረሰቡ ከሚኖራቸው ፋይዳ አንጻር የሚመለከት ይሆናል፡፡ በአንድ ማሕበረስብ ውስጥ ያለ ቁሳዊም ሆን መንፈሳዊ ፎክሎር ለፈጠረው እና ለሚጠቀምበት ማሕበረሰብ የሚሰጠው አገልግሎት አለ፡፡ ይህን አገልግሎትም በማሕበረስቡ ውስጥ ለግለሰቦች የሚኖረው አገልግሎት እና በግለሰቦች ለተዋቀረው ማሕበራዊ መዋቅር የሚኖረው ፋይዳ በሚል ይከፈላል (Barnard,2004:61)፡፡በአጠቃላይ የስነሰብ ተመራማሪው Malinowski የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ማአከላዊ ጉዳይ ስውና ማሕበረስብ መሆኑን ይገልጻሉ (Malinowski ,1939:938)፡፡

መዋቅራዊ ተግባራዊ ንድፈሃሳብ መስረታዊ ትኩረቱ ባሕላዊ ሥርዓቱና ክንዋኔው ለግለሰቦች ከሚኖረው ፋይዳ በበለጠ ማሕበራዊ መዋቅሩን ከማስጠበቅ አንጻርና በዚህ ሂደት ስዎች በማሕበራዊ ተቋማት ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ ትኩረቱ ያደርጋል (Malinowski, 1939:953) ለዚህ ጥናትም በዋናነት የምጠቀመው መዋቅራዊ ተግባራዊ ንድፈሃሳብን ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ኅሳዊ አደርጃጀት ያለው የጉምዝ ብሕረሰብ ማንነቱን አስጠብቆ ለማስቀጠል የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃ ሥርዓቶች የሚኖራቸውን ተግባር መመርመር ስለሚያስችል ነው፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር የኔ ጥናት ከሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይና ከሚጠናው ብሔረሰብ ጋር በተገናኘ የተሰሩ ስራዎች ይዳሰሳሉ፡፡ ለዚህም በአማርኛ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ የሚቀራረቡ ናቸው ያልኳቸውን የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ዲግሪ የጥናት ወረቀቶች መርምሪያለሁ፡፡ በተጨማሪም ከዚህ ጥናት ጋር የሚቀራረቡ በሌሎች የትምህርት ክፍሎች የተሰሩ የመመረቂያ ጽሑፎችንና በተለያዩ መጽሐፍት፣ ጋዜጦች እና ሌሎች ጽሑፎች ላይ ያገኘኋቸውን ስራዎች ተመልክቻለሁ፡፡ የተዳሰሱ ጥናቶች ከቅርብ ወደ ኋላ በታተሙበት ጊዜ ቀርበዋል፡፡

### 2.2.1. በአማርኛ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተደረጉ ጥናቶች

በመጀመሪያ የምዳስሰው ስራዬ እንዳለው በ(2005) ዓ.ም "የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ" በሚል ርዕሰ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያካሄደችውን ጥናት ይሆናል፡፡ በጥናቱ የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሃዘን ሥርዓቶች ተቃኝተዋል፡፡ ይህ ጥናት አውዳዊ የትንተና ዘዴን ተከትሎ የተሰበሰቡና የተተነተኑ መረጃዎች በገላጭ መንገድ ቀርበውበታል፡፡ የጥናቱ ዓላማ ሥርዓቶቹን መግለጽ እና መተርጎም ነው፡፡ ስራዬ በመረጃ ትንተና ክፍልዋ ላይ በከበራዎች ያሉ ጉዳዮችን በተናጠል ትርጉም ለመስጠት ሞክራለች፡፡ ነገር ግን የሁሉንም ልማዳዊ ሥርዓቶች የጋራ ትዓምርት በማውጣት በነዚህ የጋራ (የሚደጋገሙ) ጉዳዮች አማካይነት የሰዎችን የሕይወት ፍልስፍና ለማየት አልገፋችም፣ ያደረገችው ጥረትም የለም፡፡ የእኔ ጥናት ግን ይህን ክፍተት ለመሞላት ሞክሯል፡፡ ከኔ ጥናት ጋርም በርዕሰ ጉዳይ የተመሳሰለ ቢመስልም የሚለይባቸው መንገዶች አሉት፡፡ ከነዚህም ውስጥ በዋናነት በጥናቱ አቀራረብ፣ በማነሳቸው ነጥቦች፣ መረጃዬን ለመሰብሰብና ለመተንተን በምጠቀማቸው ንድፈ ሃሳቦች እና በሚጠናው ማሕበረሰብ ቋንቋና ባሕል የኔ ጥናት ፈፅሞ የተለየ ነው፡፡

ሁለተኛነት የምመለከተው ድርብወርቅ ብፁ በ(2003) ዓ.ም "የጉምዝ ማሕበረሰብ ባሕላዊ ህክምና (የጋፍያ) ሥርዓት እና ማሕበራዊ ፋይዳ" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የሰራችውን ስራ ይሆናል፡፡ ይህ ስራ በብሔረሰቡ ባሕላዊ ህክምና ሥርዓት እና የመድሃኒት ቅመማ ሄደት እንዲሁም በሥርዓቱ ማሕበራዊ ፋይዳ ላይ ያተኩራል፡፡ እነዚህ ሁለት

ጥናቶች በሚጠናው ማሕበረሰብ እና ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ቢመሳሰሉም በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ በዓላማ፣ በንድፈ ሃሳብ አጠቃቀም እና በአጠናን ሄደት ይለያያሉ።

ደስታ አማረ በ(2002) ዓ.ም "በቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በአል አከባበር ፎክሎራዊ ገጽታ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪዋ ማሟያነት ያደረገችው ጥናት ሌላው ዳሰሳ ያደረኩበት ስራ ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ የቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ሥርዓቶችን ምንነት፣አፈጻጸማቸውን እና አከዋወናቸውን መመዝገብና ትንታኔ መስጠት ነው። የጥናቱ አቀራረብ ገለጻዊ ትንተና ሲሆን መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ምልከታና ቃለመጠይቅ ተጠቅማለች። በስም ስያሜ ሂደቱ ያሉ ፎክሎራዊ ጉዳዩችን ማለትም ስነ ቃልና ቁሳዊ ባሕል እንዲሁም የክዋኔ ሂደቱን ተመልክታለች። የአጥኝዋ ትኩረት በማሕበረሰቡ ውስጥ ካሉት የሕይወት ዑደት ደረጃዎች የመጀመሪያ ልጅ ስም ስያሜ ላይ ያተኩራል የኔ ጥናት ግን በጉምዝ ማሕበረሰብ ዋና ዋና የሆኑትን ሥርዓቶች ስለሚመለከት የማሕበረሰቡን የሕይወት አተያይ ለመረዳት ያስችላል፡፧

ተሾመ ሙሉጌታ በ(1996) ዓ.ም "በቢንሻንጉል ጉምዝ ድባጢ ወረዳ የለቅሶ ሥነ ሥርአት" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ሌላው ዳሰሳ የተደረገበት ስራ ነው። የዚህን ስራ ዓላማ በግልጽ ለመረዳት ቢከብድም በለቅሶ ሥርአቱ ያለን ስነቃል መግለጽ የሚል ነው። መረጃ መሰብሰብን በተመለከተ የምልከታ እና የቃለ መጠይቅ ዘዴን እንደተጠቀመ ቢገልጽም መስክ በነበረው ቆይታ ግን የሞተ ሰው ባለመኖሩ መመልከት አለመቻሉን ጠቅሷል። ከእኔ ጥናት ጋርም ባጠናን ሂደቱም ሆነ በዓላማ የተለያዩ ናቸው። ሙሉጌታ የልቅሶ ሥርዓቱን ብቻ የሚመለከት ሲሆን ስነቃል ከክዋኔው እና ልማዳዊ ሥርዓቶች በበለጠ ትኩረት ሰጥቶ የቃኘው ጉዳይ ነው። በተጨማሪ የኔ ስራ በማንዱራ ወረዳ የሚሰራ መሆኑ እና ውልደት፣ ለአቅመ አዳም እና አቅመ ሄዋን መድረስ፣ ጋብቻ እና ሞትን በሙሉ የሚዳስስ መሆኑ ከሙሉጌታ የሚለይበት ነው።

## 2.2.2. ከትምህርት ክፍሉ ውጭ የተደረጉ ጥናቶችና ሌሎች ጽሑፎች

Merone Zeleke በ(2005) እ.ኤ.አ "The Socio Economic Role And Status Of Gumuz Women" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የ"Social Anthropology"ትምህርት ክፍል

የሁለተኛ ዲግሪዋን ለማግኘት ጥናት አካሂዳለች፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማም የጉምዝ ብሔረሰብ ሴቶች በማምረት ሂደት፣ በኢኮኖሚያዊ ጉዳይ እና በአጠቃላይ ማሕበራዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ድርሻ ማሳየት ነው፡፡ በጥናቱም በብሔረሰቡ ውስጥ ሴት ልጅ ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊ ድርሻ እና ሚና እንዳላት ለማሳየት ተሞክሮበታል፡፡ አጥኚዋ የብሔረሰቡን የተለያዩ ባሕላዊ ክንዋኔዎች ለማሳየት ሞክራለች፡፡ ነገር ግን ሁሉም ባሕላዊ ክንዋኔዎች የተቃኙት ሴት ልጅ በማሕበረሰቡ ካላት ድርሻ አንጻር ነው፡፡ ይህ ጥናት በሚጠናው ብሔረሰብ ከኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ከመመሳሰሉ በበለጠ ግን ልዩነቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ልዩነት በጥናቱ ዓላማና በሚያነሱት ርእሰ ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ልዩነት ያጠናን ሂደቱ እና አደረጃጀቱ ነው፡፡ በመጨረሻ አጥኚዋ በሴት ልጅ ማሕበራዊ ድርሻ ላይ ማተኮሯ የሰበሰበቻቸውን መረጃዎች ከማሕበረሰቡ አስተሳሰብ አንጻር እንዳትተነትነው ያደረጋት ይመስለኛል፡፡

Aklilu Yilmaበ(2002) እ.ኤ.አ ለ14ተኛው የኢትዮጵያ ጥናት "Some Observation On Gumuz Dialects". በሚል ርዕስ ያቀረቡት ፅሑፍ ስለ ጉምዝ ብሔረሰብ የቋንቋ ሥነምዕላድ ቅኝት የተካሄደበት ነው፡፡ በዚህ ስራ ስለ ሕዝቡ በገለፁበት ክፍል ብሔረሰቡ በክልሉ ካሉ19 ወረዳዎች በ14ቱ እንደሚገኙ፣ እንዲሁም ከክልሉ ውጭ በሌሎች ቦታዎች ሰፍረው እንደሚኖሩ ገልፀዋል፡፡ ብሔረሰቡ በናይሎ ሰሓራ የዘር ግንድ ስር እንደሚገኝም ጠቅሰዋል፡፡ በአጠቃላይ ስራው ግን በቋንቋው ሥነምዕላድ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከኔ ጥናት ጋርም በርእሰ ጉዳይ ይለያያሉ፡፡

Wold-selassie Abatte. እኚህ ተመራማሪ በ(2002) እ.ኤ.አ በጀርመን ሀገር የዶክትሬት ዲግሪቸውን ለማሟላት "Gumuz And Highland Resettlers Differing Stratageis of Livelihood And Ethnic Relation In Metakel North Western Ethiopia" በሚል ርእስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በመንግስት እና በራሳቸው የሰፈሩ ሕዝቦች ከነባሩ የጉምዝ ሕዝብ ጋር ያላቸውን መስተጋብር እና የነባሩ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ፣መተዳደሪያ ስራ፣ የሃብት አጠቃቀም እንዲሁም የማሕበራዊና ባሕላዊ ተቋማት ምን እንደሚመስሉ ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የብሔረሰቡን ባሕላዊና ማሕበራዊ ገጽታ በማሳየት ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የማንነት ልዩነት እንዴት እንደሚፈጥሩ፤ የሚፈጠሩትን ግጭቶች ለመፍታት እንዴት እንደሚጠቀሙበት ያሳያል፡፡ ይህ ጥናት በሚጠናው ብሔረሰብ ከኔ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም

በጥናቱ ስፋት፣ በርዕሰ ጉዳይ እና በጥናቱ ዓላማ ልዩነት አለው፡፡ በተጨማሪም በWold-selassie ስራ የብሄረሰቡ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓት ጉዳዩ አይደለም

Abbink, Jon. “Gumuz Ethnography” በሚል ርዕሰ በ *Encyclopedia Ethiopia* ያሰፈሩት ጹሑፍ የቃኘሁት ሌላው ስራ ነው፡፡ እኒህ ሰው በአጭር ገፅ ስለብሔረሰቡ ስያሜ አሰፋፈር፣ ቋንቋ እና ባሕል ገልጸዋል፡፡ ከአጉራባች ሀገራት፣ ክልሎች እና ሕዝቦች ጋር ያላቸውን የባሕል፣ የንግድ እና የእምነት መስተጋብርም አስፍረዋል፡፡ ሕዝቡ በጎሳ የተከፋፈለ መሆኑን እና የጋብቻ ሁኔታውም ከጎሳቸው ውጭ እንዲሆን ባሕሉ እንደሚያስገድዳቸው አስፍረዋል፡፡ ይህ ስራ በጉምዝ ብሔረሰብ ላይ የሚያተኩር መሆኑ ከኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ጥናቱ የብሔረሰቡ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓት ላይ ያተኮረ አለመሆኑ ከኔ ጥናት ሚለይበት ነጥብ ነው፡፡

Abeya Iffa በ(1995) እ.ኤ.አ “Adaptation, Culture and Changing Enviroment the Case Of Gumuz Of Diddessa Valley” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የ “Social Anthropology” ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚሆን ጥናት አቅርቧል፡፡ ይህ ስራ በከማሺ ዞን በሚገኙ ጉምዞች ላይ ያተኮረ ሲሆን ከመልክአ ምድር ሆኔታ ጋር እራሳቸውን ለማላመድ ባሕላቸውን እና ባሕላዊ ተቋማትን እንዴት እየተጠቀሙባቸው እንደሆነ ቃኝቷል፡፡ ተመራማሪው አካባቢውን በመላመድ ሂደት ላይ ጠቃሚ የሆኑ ባሕላዊ ተቋማትን ሲያሳይ ስለ ብሔረሰቡ አደረጃጀት አብራርቷል፡፡ ቢሆንም አካባቢና የአከባቢውን አይር ንብረት የመላመድ ሂደታቸው ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ በጥናቱ ዓላማም ሆነ ባደረጃጀቱ ከእኔ ስራ ጋር ልዩነት አለው፡፡

Aster Zewde በ(1991) እ.ኤ.አ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሥነ ልሳን ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዲግሪዋን ለማሟላት “Gumuz Verb morphology” በሚል ርእስ ጥናት አካሂዳለች፡፡ ዓላማውም የብሔረሰቡን ቋንቋ ሥነ ምእላድ ዘርዝሮ ማሳየት ነው፡፡ በጥናቱ ዳራ ላይ ስለብሔረሰቡ የተለያዩ ጸሃፍት የጻፏቸውን ስራዎች በመዳሰስ የብሔረሰቡን ማንነትና የሚኖሩባቸውን አካባቢዎች ለማሳየት ሞክራለች፡፡ በሚጠናው ብሔረሰብ ከኔ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም በርእሰ ጉዳይ ይለያያሉ፡፡

Taddese Tamerat በ(1982) እ.ኤ.አ በኢትዮጵያ ታሪክ እና ኢትኖግራፊ ጥናት ላይ በተደረገው ዓለማቀፍ ሲምፖዚየም "Early Trends Of Feudal Super imposion On Gumuz Society In Western Gojjam" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ ጥናቱ በመተከል ጐጃም በሚገኙት የብሔረሰቡ አባላት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በአካባቢው የነበሩ የፊውዳል ገዢዎች በብሔረሰቡ ላይ ያደርሱት የነበሩትን የአገዛዝ ችግር ያሳየ ቢሆንም ስራው ከአጐራባች ህዝቦች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሰፊው አትቷል፡፡ የአገው ባላባቶች እስከ ሱዳን ጠረፍ ድረስ ያስተዳድሩና ያስገብሯቸው እንደነበረም ገልፀዋል፡፡ ዓላማቸው የፊውዳል አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ያደረሰውን ተጽእኖ መግለፅ ቢሆንም ብሔረሰቡ ለራሱ ያለውን አመለካከትም ገልፀዋል፡፡ ማሕበረሰቡም እራሱን ጉምዝ ካልሆኑ ሰዎች ጋር የጥንት አያታቸው መንትያ እንደነበሩ ይገልጻሉ በማለት አስፍረዋል፡፡ ይህ ጥናት የብሔረሰቡን የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ስርዓት ትኩረት አለማድረጉ ከኔ ጥናት ጋር የሚለየበት አብይ ጉዳይ ነው፡፡

ባጠቃላይ ቅኝት ካደረኩባቸው ስራዎች ክፍተት እና ጥንካሬ የተማርኳቸው ጉዳዮች ቢኖሩም ከስራዎቹ የኔ ጥናት የሚለይበት ነጥብ አለ፡፡ ይህም የአጠናን ሂደቱ ሲሆን የብሔረሰቡን አመለካከት እና የሕይወት አተያይ በሚከውኗቸው ልማዳዊ ሥርዓቶች መሰረት ትንተና የሚሰጥበት መሆኑ ነው ፡፡

## 3. የማንዱራ ወረዳ የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት ከሚከወኑባቸው ዐውዶች አንፃር

በጉምዝ ብሔረሰብ መወለድን፣ ለአቅመ ሄዋን እና ለአቅመ አዳም መድረስን፣ ጋብቻን፣ ሞትን እና ተስካርን ምክንያት በማድግ የሚፈጸሙ ሥርዓቶች መለየት፣ ሽግግር እና አዲስ ማንነት ማግኘት በመባል የሚታወቁትን ደረጃዎች ያልፋሉ፡፡

### 3.1. የውልደት ሥርዓት (ምፐቋ)

ውልደት አንድ ሰው ከሚያልፍባቸው ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ውስጥ የመጀመሪያው ነው፡፡ የጉምዝ ብሔረሰብን የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስንመለከት የመጀመሪያው የውልደት ሥርዓቱ ነው፡፡ በዚህ በውልደት ሥርዓቱም ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎችን እናያለን፡፡ ቅድመ ውልደት ፣ የውልደት ወቅትን እና ድህረ ውልደት፡፡ እነዚህን ክፍሎች ሥርዓቱ የሚያልፍባቸው ደረጃዎች ማለትም መለየት፣ ሽግግር እና አዲስ ማንነት ማግኘት ብለን በቅደም ተከተል ልንመድባቸው እንችላለን፡፡

**ቅድመ ውልደት**

የጉምዝ ህፃን በእናቱ ማህፀን ተረግዞ ከመወለዱ በፊት እናት እና አባቱ ትዳር ከመሰረቱበት ጊዜ ጀምሮ ለደህንነቱ ጥንቃቄ ይደረግለታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ወላድ እናት የአማቶቿን ቤት ምግብ አለመብላት አንዱ ጥንቃቄ ነው፡፡ አሁን አሁን እየቀረ ቢመጣም በባሕሉ ጤናማ ልጆች አትወልድም ተብሎ ስለሚታመን እናት በአማቶቿ ቤት ስትኖር ልጆች ወልዳ እስክትጨርስ የአማቶቿን ምግብ አትበላም፡፡ በገነተ ማርያም ያገኘኋት መረጃ አቀባዪ ኤቤዎ ስለዚህ ጉዳይ ያስረዳችኝን እነደሚከተለው ተርጉሜ አቀርባለሁ፡፡

> ሴት ልጅ በአማቶቿ ቤት ስትኖር የምትወልዳቸው ልጆች ጤነኛ እንዲሆኑ ወልዳ እስክታቆም ድረስ የምትመገበው ምግብ በሚሰጣቸው ጉጆ የምታዘጋጀውን ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በምትወልዳቸው ልጆች እና በራስዋ ችግር ይፈጠራል፡፡ የምትውልዳቸው ልጆች አካል ጉዳተኛ ይሆናሉ (ቃለ መጠይቅ፣ 6/6/2007)፡፡

መረጃ አቀባዬ ከዚህ ጋር አያይዛም እሷም በዚህ መልክ አልፋ ከሁለት አመታት በፊት መውለድ ማቆሟን ስታረጋግጥ ብቻ የአማቶቿን ምግብ መብላት እንደጀመረች ገልፃልኛለች፡፡ ሌላው በቅድመ ወሊድ ስርዓት የሚጠቀሰው የምግብ ምርጫ ነው፡፡ ነፍሰ ጡር ሴት በዋናነት ከማትመገባቸው ነገሮች ውስጥ እንቁላል እና የዶሮ ስጋ ይጠቀሳሉ፡፡ ከነዚህ የዶሮ ተዋፅኦዎች በተጨማሪ በጊዜያዊነት በዕርግዝና ጊዜ የአልኮል መጠጦች እንዳትጠጣ ይመከራል፡፡ እነዚህ

ምግብና መጠጦች የሚከለከሉት በባሕሉ መሰረት በሚወለዱ ህጻናት ላይ የጤና ችግር ያደርሳሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

በእርግዝና ወቅት የሚደረጉ ጥንቃቄዎች ወይም ቅድመ ወሊድ ሥርዓቶች ፅንሱ እየገፋ ሲሄድ እየጠበቀ ይመጣል፡፡ እናት ፅንሱ እየገፋ በመጣ ጊዜ በተቻለ መጠን እቤት ውስጥ ወይም በእህል ማሳ ውስጥ እንዳትወልድ ጥንቃቄ ታደርጋለች፡፡ መጨረሻ የምጥ ሰአቷ ሲደርስ ከቤት ውጭ ወዳለ ጫካ ጥላ ያለው ዛፍ ስር ትሄዳለች፡፡ በብዛት በስራ ቦታ እያለች ምጧ ስለሚመጣ በአቅራቢያዋ ወዳለ ጫካ ትገባለች፡፡ የእርግዝና ጊዜ የህጻኑ ቅድመ ወልደት የእናቲቱ የእርግዝና ወይም የመለየት ወቅት ነው፡፡ ከሌላው ማህበረሰብ ነፈሰጡር በመሆንዋ ትለያለች፡፡

## የወሊድ ወቅት ሥርዓት

የቅድመ ወሊድ ጊዜዋን ያጠናቀቀች ነፍሰ ጡር ሴት በወሊድ ጊዜ የምትጠቀምባቸውን ምላጭ፣ ክር እና በጉምዘኛ "ምጨ" የሚባለውን እንደ ሞዴስ የምትጠቀምበትን ከንጨት ቅርፊት የሚሰራ ነገር ታዘጋጃለች፡፡ ነፍሰ ጡር ሴት ምጧ እንደመጣ ስታረጋግጥ ያለማንም አጋዥነት በአቅራቢያዋ ወዳለ ጫካ ትሄዳለች በጫካ ውስጥ ያለማንም እረዳትነት ትገላገላለች፡፡ በአቅራቢያዎ ይመለከቷት የነበሩ የጎረቤት ሴቶች ካሉ ህፃኑ መወለዱን ሲያለቀስ ካረጋገጡ በኂላ ሄደው ሊያመጧት ይችላሉ፡፡ ሰው ከሌለም ብቻዋን ትመጣለች፡፡ በመጨረሻም ስትወልድ የተጠቀመችበት የሰኔል ምንጣፍ፣ ምላጭና ሌሎች እቃዎችን እዛው ጫካው ላይ ትታ ወደ መንደሯ ወዲያው ትመለሳለች፡፡

የወሊድ ስርዓቱን የተመለከትኩት ዳቡህ በሚባለው ቀበሌ ሲሆን በዚህ ቦታ በአንድ መንደር ውስጥ አንድ በባሕላዊ መንገድ እና አንድ "በዘመናዊ" ወይም የጤና ባለሞያዎች በሚሉት መንገድ የወለዱ አራሶችን አግኝቻለሁ፡፡ ወደ መንደሩ የሄድኩት እሮብ ቀን በ11/6/2007 ነበር፡፡ የመጀመሪያዋ ኤካውክ የምትባል የ19 ዓመት ወጣት ናት፡፡ ይህች እናት የተገላገለችው በባሕሉ መሰረት በአቅራቢያዋ ባለ ጫካ ውስጥ ነው፡፡ ወደ ሰፈራቸው ስደርስ በግቢው ውስጥ ባለ ትልቅ ዛፍ ስር ተቀምጣ ነበር፡፡ አራሷ እናት ለመመገቢያ የሚሆናት "ፋጋ" የተሰኘ መመገቢያ እቃ፣ የውሃ መጠጫ ኩባያ እና የውሃ መያዣ 3 ሊትር ጉማ ከውሃ ጋር በአጠገቧ ተቀምጦላታል፡፡ እሷም በነዚህ እቃዎች ተከባ ልጇን ታቅፋ ተቀምጣለች፡፡

ኤካውክየምትኖረው ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ከሆኑት ኤልኝታና ባለቤቷ ሳሉ ግቢ ሲሆን ቅርበታቸውም ምራታቸው ናት፡፡ እኔ ወደ ቦታው የደረስኩት የውልደት ድባቡ ሳይቀዘቅዝ በአራተኛው ቀን ነበር፡፡



በባህላዊ መንገድ የወለደች የጉምዝ ሴት



በዘመናዊ መንገድ የወለደች የጉምዝ ሴት

ከአራት ቀን በፊት 10 ሰአት አካባቢ ከስራ ቆይታ ስትመለስ ምጥ ይይዛታል፡፡ ምጡ እውነተኛ መሆኑን አብረዋት ያሉ ሰዎች ሲያረጋግጡ በአካባቢው ወዳለ ጫካ እንድትገባ ያደርጓታል፡፡ የባለቤቷ እናት በቅርብ ርቀት እየተከታተለቻት ነበር፡፡ በመጨረሻም ወንድ ልጅ ትገላገላለች፡፡ በሰላም መውለዷን ስታረጋግጥ እናት ምራቷን ይዛ ወደ መንደሯ ትመለሳለች፡፡ ይህ ሰአት ለእናቲቱም ሆነ ለህጻኑ የሽግግር ወቅት ልንለው እንችላለን ፡፡ እናቲቱ ልጇን በእቅፏ ይዛ እናት ለመሆን ህጻኑም በአካል ወደ ማሕበረሰቡ ለመቀላቀል የሚያልፉበት የአዲስ ሕይወት እርከን ነው፡፡ ወደ ግቢ ከገቡ በኋላ ያለውን ሁኔታ ኢልኝታ በተግባር እያሳየች ነበር የገለፀችልኝ፡፡



ሴቶች ውጭ የሚወልዱበት የራሱ ምክንያት እንዳለው የብሔረሰቡ አባል የሆኑት ኤቤዋ ይናገርሉ፡፡

> የመጀመሪው ምክንያት ከእናቲቱ የሚፈሰው ደም ቤት ከፈሰሰ ቤቱ ይረክሳል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የቤት ውስጥ አምላክ (ሙሳ) ስለሚቆጣ እናቲቱም ሆነ የሚወለደው ህጻን እንዲሁም የቤተሰቡ አባላት ጤና ያጣሉ፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የሚወለደው ህጻን ወንድ ከሆነ እቤት ውስጥ ከተወለደ ፈሪ ይሆናል ጫካ ወይም ከቤት ውጭ ከተወለደ ግን ጀግና፣ አዳኝ እና ጦረኛ ይሆናል፡፡ (ኤቤዋ፣ቃለመጠይቅ፣20/6/2006)

በጉምዞች ዘንድ አዳኝነትና ጀግንነት ከወንድ ልጅ የሚጠበቁ ግለሰባዊ ሚናዎች ናቸው፡፡ ለወንድ ልጅ የሚሰጠው ማሕበራዊ ተልእኮ የሚጀምረው ከሚወለድበት ቦታ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ውጭ መውለድ የምትወልደዋ ሴት ጥንካሬ የሚመሰከርበት ነው፡፡ ለዚህ አጋጣሚ ባቅራቢያዋ ሌሎች ሴቶች ቢኖሩም ለማገዝ ጥረት አያደርጉም፡፡

## ድህረ ውልደት

በጉምዝ ባሕል መሰረት ወላድ እናት ዝም ብላ ወደ ቤት አትገባም፡፡ በረንዳ ላይ ተቀምጣ ጫጩት ዶሮ ይፈለግና በእናትና ልጅ ራስ ላይ ተዙሮ አንገቱ ይቆረጣል፡፡ ጫጩቱ ከተቆረጠ በኋላ ቆዳው ተገፎ በልጁ የቀኝ እጅ ይታሰራል፡፡ ይህን የሚያድርጉት ህጻኑም ሆነ እናቲቱ ከመጥፎ መንፈስ እንዲጠበቁ ለማድረግ ነው፡፡ በመቀጠልም እናቲቱ ፀጉሯን ሙሉ ለሙሉ ትላጫለች፡፡

ከዋናው ቤት ጎን የተሰራችው ጐጆ ውስጥ በቅርቀሀ (የበረሃ ሽመል) የተሰራች ምንጣፍ ላይ ከላዩ የሰኔል ምንጣፍ ተደርቦበት ይነጠፍላታል። ከመኝታዋ በተጨማሪም እሳት ይነድበታል። የግል መመገቢያ እቃዎችም ይገቡላታል። ይህ ጐጆ ማደሪያዋ ነው። ቀን ላይ ግቢ ውስጥ ያለ ዛፍ ስር ተቀምጣ ነው ምትውለው። ከቀሪው የቤት ውስጥ ስራ ጋር በተያያዘ መረጃ ሰጪዬ የሚከተለውን ብለውኛል።

> በዚህ ጊዜ ቤተሰቡን የምታስተዳድር ሴት ከሆነች ባለቤቷ ሁለተኛ ሚስት ካለው ሁለተኛዋ ሚስት የቤቱን ሰራ ትሸፍናለች። ከሌለው ግን የጐረቤት ሰዎች እሷን ከማረስ ጋር ጨምረው የቤቱን ስራ ሙሉ በሙሉ ይሸፍናሉ። (ኢልኝታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 11/6/2007)

የድህረ ወሊድ ያለው ሥርዓት የሚጠናቀቀው የልጁ እትብት ሲደርቅ ነው። የህፃኑ እትብት ሲደርቅ እናቲቱ ንፅህናዋን አውጻ ወደ ማሕበረሰቡ ትቀላቀላለች። በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ምዕራፍም ይህ ጊዜ አዲስ ማንነት ወይም ማሕበራዊ ደረጃ የምትይዝበት ነው። በዚህ ጊዜ የሚከናወኑ ሥርዓቶችን ስንመለከት ምግብና መጠጥ ይዘጋጃል። “ክያ” የተሰኘው ባሕላዊ የቦርዲ መጠጥ ተዘጋጅቶ ፍየል ወይም ዶሮ ይታረዳል። እናቲቱን እየመጡ ይጠይቋት የነበሩ ጐረቤቶች ይጠራሉ። ህፃኑ በዚህ ዕለት ሲወለድ ይዞት የወጣው ፀጉር ሙሉ ለሙሉ ይላጫል። እናቲቱ ወንዝ ወርዳ ገላዋን ትታጠባለች፣ ጸጉሯንም ትላጫለች። የፀጉር አላጫጩ ከሌላ ጊዜው የተለየ ነው። መሀል አናቷን በአንድ መስመር እስከ መሀል ጭንቅላቷ ድረስ ትላጫለች። በአራስነት ጊዜዋ ትጠቀምባቸው የነበሩ ቁሳቁሶች እናት እና ልጅ ነጽተው ወደ እቤት ሲገቡ እረክሰዋል ተብለው ስለሚታመን ተቃጥለው ይቀበራሉ።

በልጁና በእናትየው በኩል ያለው ዝግጅት ካለቀ በኋላ የሓገር ሽማግሌዎች ተጠርተው የምርቃን ሥነ ሥርአት ይካሄዳል። ከምርቃን በኋላ የሚታረደው ታርዶ ምግብ መጠጡ ይቀርባል። በዚህ ቀን ልጁ ወደ ማሕበረሰቡ የሚቀላቀልበት ነው። እናቲቱም በአዲስ ማንነት (እናትነትን) እናት ሆና ወደ ማህበረሰቡ በይፋ የምትቀላቀልበት ይሆናል። በዚህ ቀን የሚፈፀመው ሌላው ጉዳይ የስም ማውጣት ሥርኣት ነው። በጉምዝ ብሔረሰብ የህፃን ልጅ ስም አውጣጥ በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ ሊመሰረት ይችላል። ህፃኑ በተወለደበት ቀን በመጣ በእንግዳ ስም ሊሰየም ይችላል። በተወለደበት ቦታም ይሰየማል። ድንገት መንገድ ላይ ከተወለደ “ቻንጅሃ” መንገድ ይባላል። ለምሳሌ መስክ በቆየሁበት ወቅት ቻይናዎች መንገድ በመስራት ላይ ነበሩ። በዛ ምንገድ አካባቢ የተውለዱ ልጆች “ቻይና” በሚል እየተሰየሙ እንደሆነ አስተውያለሁ። ሌላው

በተወለደበት ቀንም ሊጠራ ይችላል፡፡ የቀኑ ስያሜ የህፃኑ መጠሪያ ይሆናለ፡፡ በጨረቃ፣ በክዋክብት ወይም በፀሓይ ከተወለደም በነዚህ ነገሮች ይሰየማል፡፡ ነገር ግን በተመሳሳይ ሁኔታ የተወለዱ ሴት እና ወንድ ቢኖሩ በስያሜያቸው ላይ የተወሰነ ልዩነት ይኖራል፡፡ ለሴትዋ በስሟ ላይ "ኤ" ትጨመራለች "ኤሃጻ" እንደማለት፡፡ ለወንዱ "ዎ" ይጨመራል "ዎሃጻ" እንደማለት፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚሰጠው ስያሜ ተከናውኖ የስም ማውጣት ሥርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡

ከነዚህ ሥርኣቶች በኂላ እናቲቱ ወደ ዕለትከዕለተ ስራዋ ትመለስና ማህበረሰቡን ትቀላቀላለች፡፡ ልጁ ነፍስ አውቆ በስሙ ሲጠራ እናት ስሟ ተቀይሮ በመጀመሪያ ልጇ ስም ትጠራለች፡፡ "እይው ዳላ" "የእከሌ እናት" እንደማለት ነው፡፡

በዳቡህ ቀበሌ በእነ ኤሌኝታ እና ሳሉ ሰፈር ከኤካውክ ሁለት መቶ ሜትር በማይበልጥ እርቀት ላይ ከወለደች አንድ ቀን የሆናትን እናት አገኘሁ፡፡ ባለቤቷ ፈንቻማለዳ ሲባል የፖሊስ አባል ነው፡፡ እሷ ደግሞ ፍቺለንብቻ ስትባል የ19 አመት የ6ተኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡ እነዚህ ጥንዶች ከተጋቡ ሁለት ዐመታቸው ነው፡፡ የሚኖሩትም ብቻቸውን ጠባብ በሆነች ጐጆ ቤት ውስጥ ነው፡፡

ወደ ሰፈራቸው ስደርስ ከምሽቱ 12:30 አካባቢ ነበር፡፡ ከመስክ እረዳቴ ጋር በመሆን ወደ ቤታቸው ስናቀና አቶ ፋንቻ ማለደ እናቲቱን በመንከባከብ ስራ ላይ ተጠምዷል፡፡ ሰላምታ ሰጥተነው ባለቤቱ በሰላም ስለወለደች የእንኳን ደስ አለህ ስሜታችንን ገልፀን ወደ ቤት ውስጥ ዘለቅን፡፡ እቤት ውስጥ እናት እና ልጅ ብቻ ተቀምጠዋል፡፡ የቤቷን ድባብ ስንቃኝ ጸጥ ያለች ነገር ግን በአንጻሩ ዘመናዊ የሚባሉ የመመገቢያ ቁሳቁስ የሚታይባት ነች፡፡ ፍቺ የመጀመሪያዋ ወሊድ ሲሆን ህፃኗም ሴት ናት፡፡ እናቲቱ ነፍሰጡር በነበረችበት ጊዜ የህክምና ክትትል ታደርግ ነበር፡፡ ህፃኗን የተገላገለችውም በጤና ተቋም ነው፡፡ ከወሊድ በኂላ ለህፃኗም ሆነ ለእናቲቱ ምንም አይነት ባሕላዊ ስርዓት አልተካሄደም፡፡ የወለደችውም ከአካባቢው ባሕል ውጭ በህክምና ተቋም ነው፡፡ ጫጩት ታርዶ በህፃኗ እና በእናትየው እራስ ላይ አልዞረም፤ በህጻኗ ቀኝ እጅ ላይም የጫጩት ቆዳ አልታሰረም፡፡

በአንድ ሰፈር ሁለት መቶ ሜትር ባልሞላ እርቀት ውስጥ ባሕላዊ እና "ዘመናዊ" (ባሕላዊ ያልሆነ) ስርዓት ሲፈጸም መታየቱ ለአካባቢው ሊከብድ እንደሚችል ይገመታል፡፡ በዚህ ጉዳይ

ላይ ፍቺ እና ባለቤቷ እንደነገሩኝ እና እኔም እንደተመለከትኩት ከሆነ በባህሉ መሰረት ባለመውለዷ በማሕበረሰቡ የመገለል ነገር ገጥሟቸዋል። እያረሷት ያሉት የሰፈሩ ሴቶች ሳይሆኑ ባሏ ነው። እዛ በቆየሁበት ጊዜ ለመጠየቅ የሚመጣ አንድም ሰው አላየሁም። እንደውም ውጭ ባለመወለዷ ፈሪ እና ጠንካራ ያልሆነች ሴት እንደሆነች እንደሚያስቡ ገልፃልኛለች (ቃለመጠይቅ፣ 11/6/2007)። እቤታቸው የማይገቡትም ረክሷል ብለው ስለሚያምኑ ነው። በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ እነዚህ ሰዎችን ፈፅመው ከባሕሉ አፈንግጠዋል ማለት አንችልም። ይህን ለማለት የሚያስደፍሩ ሁኔታዎችም አሉ። የህፃኗን ስም ማን እንዳሏት በምጠይቅበት ጊዜ ስም የሚወጣላት እትብቷ ደርቆ ሲወድቅ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል። ከዚህ የምንረዳው ሙሉ ለሙሉ ባሕላዊ ሥርዓቱን እንዳልተውት ነው።

## 3.2. የመጀመሪያ የወር አበባ እና የወንድ ልጅ ግርዛት

በጉምዝ ብሔረሰብ ህፃናት ከተወለዱ በኋላ ወደ ማሕበረሰቡ በተለያዩ ሥርዓቶች ይቀላቀላሉ። ማህበራዊ ሰውነትን ያገኛሉ። ይህ ሽግግር አንድም ተፈጥሮአዊ ነው በሌላ መልኩማሕበረሰቡ በሚመራበት ባሕላዊ ስርዓት እየተመራ ማሕበረሰቡ የሚያከናውነው ነው። የብሔረሰቡ አባላት የህፃንነት ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ህጻናትን ወደ ወጣትነት የሚቀላቀሉባቸውም የተለያዩ ሥርኣቶች አሏቸው። ለሴት ልጃገረዶች እና ለወንድ ልጅ የሚከናወኑ ሥርዓቶችን ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን።

### 3.2.1.የመጀመሪያ የወር አበባ ሥርዓት (ግዲድስ ግኽዣ)

ሴት ልጅ የህፃንነት ዘመኗን ጨርሳ ለአቅመ ሄዋን መድረሷን የምታረጋግጠው ተፈጥሮአዊ በሆነው የወር አበባ ክስተት ነው። ይህ ክስተት ግን ከክስተትነቱ ባሻገር ለጉምዝ ብሄረሰብ የራሱ የሆነ መልእክት አለው። አንዲት ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባዋ ሲመጣ በግልፅነት ከቤት ውስጥ ለአንድ ሰው ትናገራለች። ያየችው የእውነት የወር አበባ መሆኑን ታላቅ እህቷ ወይም እናቷ ካረጋገጠችላት በኋላ ቤተሰቡ በሙሉ ያውቃል። ለዚህ ተግባር በየቤቱ በር ወይም ጓሮ የሚሰሩ ትንንሽ ጉጆዎች ስለሚኖሩ እዛ ቤት ውስጥ እንድትገባ ይደረጋል። የሚያስፈልጓትን ቁሳቁሶች እንደ መጠጫና መመገቢያ የመሳሰሉትን ያስገቡላታል።

ይህን የሰሙ የሰፈሩ ልጃገረዶች ተሰብስበው ልጅቱ ያለችበት ጉጆ ድረስ በመምጣት ያጫውቷታል። በዚህ ወቅት መጥፎ መንፈስ ይተናኮላታል ተብሎ ስለሚታመን ልጂቱ ብቻዋን መሆን የለባትም። ከቤተሰብ ተለይታ በጎጆዋ የምትቆየውም የወር አበባው እስኪያልቅ ከ5-6

ቀን፤ ካለቀ በኋላ ለ5 ቀን ሲሆን በአጠቃላይ 10 ቀን ድረስ ልትቆይ ትችላለች፡፡ ማታ ማታ ሁሉም የሰፈሩ ልጃገረዶች ተሰብስበው ያጫውቷታል፤ ሴቶቹ አብረዋትም ያድራሉ፡፡ የቆይታቸውን ጊዜ መረጃ ሰጪዬ እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡

> በዚህ ጊዜ እሷም ሆነች ጓደኞቿ በነዚህ ቀናት በጨሌ የሚሰራ “ሚንዛ” የተባለ የአንገት፣ የእጅ እና የፀጉር (የራስ ጌጥ) ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም ለወር አበባ ጊዜ የሚሆን “ምጭ” የተባለ ከዛፍ ቅርፊት የሚሰራ ለወር አበባ ጊዜ የሚያገለግል ነገር ይሰራሉ፡፡ ይህች ሴት በነዚህ ቀናት ዋናው ቤት እና የእህል ማሳ አትገባም፡፡ እንዲሁም የአደን መሳሪያ አትነካም፡፡ የመመገቢያ ቁሳቁሶቿም የተለዩ ስለሆኑ የሌሎችን እቃ አትነካም፡፡ (ኤቤዋ፣ቃለ መጠይቅ፣ 20/6/2007)

ይህን ወቅት ወይም ያለፉትን 10 ቀናት መለየት የምንለው የሽግግር ደረጃ ነው ማለት እንችላለን፡፡ በዚህ ሁኔታ የወር አበባዋን ከጨረሰች በኋላ ተጨማሪ አምስት ቀናትን ትጠብቅና በ10 ወይም 11ኛ ቀን የመጨረሻው ስርአት ይፈፀማል፡፡ ይህ ስርአትም ከመለየት ቀጥሎ የሚመጣው የመሸጋገር ወቅት ነው ማለት እንችላለን፡፡ ይህ ሥርዓት “ክይ ግኽዣ” ይባላል፡፡ እዚህ ላይ የምንረዳው የሚደረገውን ሥርዓት ከሌሎች የተለየ ስያሜ የሚሰጠው በአውዱ ውስጥ ባለው አገልግሎት ነው፡፡ አውዳዊ ትርጓሜ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ለዚህ ሥርዓት በቅድሚያ እንደ ቤተሰቦቿ አቅም ዶሮ ወይም ፍየል ለእርድ ይዘጋጃል፡፡ “ክያ” የተባለው ባሕላዊ መጠጥም ይቀርባል፡፡ በልጅቱ በኩል ጓደኛቿ እየዘፈኑ ወደ ወንዝ ወስደው ገላዋን አጥበው ይመልሷታል፡፡ ፀጉሯንም አራስ እናት በመጨረሻው የአራስነት ቀን ሥርዓት እንደምትላጨው መሀሏን ክፍት አድርገው ይላጯታል፡፡ ይህ ቀን ልጅቱ ለአቅመ ሄዋን መድረሷ ለአካባቢው ማሕበረሰብ የሚበሰርበትም ጭምር ነው፡፡ ለልጂቱ ምግብ እያዘጋጁ ያቅርቡላት የነበሩ ቤተሰቦቿ እና የሰፈሩ ልጃገረዶች እንዲሁም የሃገር ሽማግሌዎች ተጠርተው በምግብ መጠጡ ይታደማሉ፡፡ ተበልቶ ተጠጥቶ ካለቀ በኋላ ሽማግሌዎች በቀጣይነት ስለሚመጡ የሕይወት ምዕራፎች ማለትም ስለ ትዳር ሕይወቷ ወደፊት ስለሚኖሯት ልጆች መልካም ምኞታቸውን በምርቃን ይገልጻሉ፡፡ ከምርቃኖቹም ውስጥ የተወሰኑትን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

| በአማርኛ | በጉምዘኛ |
|---|---|
| ጥሩ የሆነ ባል ይግጠምሽ፤<br>ሰነፍ ያልሆነ ስራ የሚችል፡ | ካውት ጉደንቋ ላውይ ምግህማ፤<br>ምግህማ ኢትግንዝዋ አግህ አንጉ፡፡ |
| ይሄ ደም የጤና ይሁንልን፤<br>መንግስት ሃገር የሚሆነውን<br>የሚያስወልድ ይሁን፡፡ | ምህ ግኽዣላግህ ሙሳ ፤<br>ካውት ምድ መንግስታ ምሣላ ፡፡ |

ከዚህ ምርቃን የምንረዳው ሴት ልጅ የመጀመሪያ የወርአበባ በምታይበት ጊዜ የሚፈጸመው ሥርዓት ልጂቱ ከምታድርገው የደረጃ እና የዕድሜ ሽግግር በተጨማሪ ሌላ ማሕበራዊ ጉዳይ እንዳለ ነው፡፡ ይህም መልካም ቤተሰብ እና ማሕበረሰብ ከመመስረት በተጨማሪ የሃገርመሪ የሚሆን ልጅ እንዲወለድ ያለን ምኞት ያመለክታል፡፡

የሃገር ሽማግሌዎች ምርቃቱን ሲጨርሱ ልጃገረዶች ጭፈራ ይጀምራሉ፡፡ ጭፈራው ካለፉት ቀናት የደመቀ ይሆናል፡፡ በዚህ እለት ወጣት ወንዶች ካሉ ልጃገረዶቹ አመድ በጥብጠው እየተራጩ ያባርሯቸዋል፡፡ ወንዶቹ ላለመረጨት የሚያደርጉት ትግል ለጨዋታው ድምቀት ይሰጠዋል፡፡

እኔ ይህን ሥርዓት የተመለከትኩት በዳቡህ የነ ኢችሁስ ሰፈር ሲሆን ባለጉዳይዋም ኤሃጻ ትባላለች፡፡ ዕድሜዋ 13 ሲሆን የሥርዓቱ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ነበር የደረስኩት፡፡ ሥርዓቱ ከስራ ሲመለሱ ስለሆነ መሽቶ ነበር፡፡ ይህን ሥርዓት ለማክበር የተሰበሰቡትም በግቢው ውስጥ ባለ ትልቅ ዛፍ ስር ነው፡፡  ህጻናት እሳት እያነደዱ ሲቦርቁ ልጃገረዶች ኢሃጻን ጨምሮ ተሰብስበው የተለያየ ይዘት ያላቸውን ዘፈኖች ያዜማሉ፡፡ በዜማውም ይጨፍራሉ፡፡ በዜማው ከሚያነሷቸው ጉዳዮች መካከል ወንድ ልጅ ጀግና፣ ደምመላሽ፣ አዳኝ መሆን እንዳለበት የሚያነሳሱ አሉበት፡፡ ከልጃገረዶቹ ውስጥ ኢሃጻ በአንገትዋ እና በራስዋ ላይ ባጠለቀቻቸው ጌጣጌጦች ብዛት ትለያለች፡፡



የጉምዞች የመጀመሪያ የወር አበባ ስርአት ጭፈራ (ስርአቱ የሚከበርላት ልጃገረድ (ኤሃፃ))

በሌላ በኩል የሃገር ሽማግሌዎችና የመንደሩ ሰዎችም ባሕላዊ አረቄ እየጠጡ ይጫወታሉ፡፡ከሽማግሌዎች ውስጥ በየነአብደው የተባሉ መረጃ አቀባየን ስለዚህ ሥርዓት አነጋግሪያቸው ነበር፡፡

> ይህ ቀን ከቤተሰብ አልፎ ለዘር ሓረጉም መቀጠል ወሳኝ ስለሆነ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ ምክንያቱም ሴት ልጅ ለአቅመ ሄዋን ስትደርስ የህፃንነት ጊዜዋን ጨርሳ አዋቂ የምትሆንበት ነው፡፡ ዘር ለማስቀጠልም አንድ ደረጃ ትቀርባለች፡፡ በዛ ላይ በለውጥ ሌላ ሴት ለቤተሰቡ የሚመጣበትም ነው፡፡ ከዚህ በኂላ ደህና ዘር አይቶ ጥሩ ሰው መርጦ መዳር የሚቀጥለው ተግባር ነው፡፡(ቃለ መጠይቅ፣ 12/06/2007)

## 3.2.2. የወንድ ልጅ ግርዛት (ሽፓ)

የወንድ ልጅ ግርዛት ሥርዓት ከሴት ልጅ የመጀመሪያ የወር አበባ ሥርዓት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የመመሳሰሉ ምክንያትም ከልጅነት ወደ አዋቂነት በመሸጋገር ሚናቸው የሚለይበት ስለሆነ ነው፡፡ስለ ግርዛት ስናነሳ ማንሳት ያለብን በጉምዝ ብሔረሰብ የወንድ ልጅ እንጅ የሴት ልጅ ግርዛት የማይታዎቅ መሆኑን ነው፡፡ በማንዱራ አካባቢ ያሉ ጉምዞች የወንድ ልጅ ግርዛቱን የሚፈፅሙት በጋራ ነው፡፡ በአንድ ሰፈር ውስጥ ዕድሜያቸው ከ8-12 የሚደርሱ ልጆች በጋራ ሆነው ይገረዛሉ፡፡ መንደሩ ውስጥ ልጆቻቸው በዚህ ዕድሜ ያሉ ቤተሰቦች በመነጋገር ቀኑን ይወስናሉ፡፡ ግርዛቱ የሚከናወነውም ከዋናው ቤት ውጭ ስለሆነ ለሥርዓቱ ማስፈፀሚያ ዳስ ይሰራል፡፡

ልጆቹ ፀጉራቸውን ሙሉ በሙሉ ይላጫሉ፡፡ በመቀጠልም ወንዝ ወርደው ሁሉም ገላቸውን ይታጠባሉ፡፡ ከዚህ በኂላ ለሚቀጥለው ደረጃ ዝግጁ ናቸው ማለት ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት ላይ ገራዥ ሰው በባሕላዊ መንገድ የሰለጠነ ሓገረሰባዊ ሀኪም ነው፡፡ በድሮ ጊዜ በእንጨት ስንጥር የሚገርዙ ሲሆን አሁን አሁን ግን በምላጭ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከግርዛት በፊት ብዙ ጊዜ ህፃናት ሱሪ አይለብሱም፡፡ ልጆቹ ከላይ ብቻ ለብሰው ወደ ዳሱ ይገባሉ፡፡ ዳሱ ውስጥ አንድ ጉድጓድ ይቆፈራል፡፡ እያንዳንዱ ህፃን በየተራ ከጉድጓድ ጫፍ ይቀመጣል፡፡ የህፃኑን አይን የሚሸፈን እንድ ሰው ተመርጦ ይይዛል፡፡

ህፃናቱ ከተገረዙ በኂላ የተጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች እና ደም የነካው ጨርቅ በአንድ ላይ ተሰብስቦ የተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ይገባና ይቀበራል፡፡ ህፃናቱ ቁስላቸው እስኪደርቅ ድረስ ጎጆ ውስጥ ይቀመጣሉ፡፡ በዚህ ቆይታቸው ልጃገረዶች እና ወጣት ወንዶች በፍፁም

እንዲያይዋቸው አይፈለግም። ሌሎች ሰዎችም እንዳያይዋቸው አይፈቀድም ከሰው ይገለላሉ። በዚህ ሥርዓት በሰፈሩ በህብረት መገረዝ የሚያስችል የሰው ቁጥር ከሌለ አንድ ሰው ብቻውን መገረዝ ይችላል። ህፃናቱ ከየቤታቸው ምግብ እየተወሰደላቸው ይመገባሉ። "ይህ በጋራ መገረዛቸውም ልጆቹን የዕድሜ ልክ ጓደኛሞች ያደርጋቸዋል" (ብርሌ ካቺ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 27/05/2007)::

በአማካኝ የሁሉም የተገረዙ ልጆች ቁስል በሚደርቅበት ጊዜ ልጆቹን ወደ ማሕበረሰቡ የመቀላቀያ ስርዓት ይፈፀማል። ምግብ እና መጠጥ ይዘጋጃል። እንደ ቤተሰቦቻቸው የኢኮኖሚ ሁኔታ ዶሮ ወይም ፍየል ይታረዳል። የአካባቢው ሽማግሌዎች እና ገራዡ ሰው ይጠራሉ። ልጆቹ ይመረቃሉ በመቀጠልም ምግብ መጠጥ ይቀርባል። ምርቃኑ ከሚይዛቸው ሃሳቦች ውስጥ ጎበዝና ጀግና እንዲሆኑ፣ ጥሩ አዳኝ እና ደምመላሽ እንዲሆኑ እንዲሁም ማሕበረሰቡን እና አካባቢያቸውን ከጠላት የሚጠብቁ እንዲሆኑ የሚገልጹ ይገኙበታል። ልጆቹ ይጠቀሙባቸው የነበሩ ቁሳቁሶች አልባሳት እና የተላጩት ፀጉር ጉድጓድ ውስጥ ይቀበራል።

ወንድ ልጆች ከተገረዙ በኋላ ሙሉ ወንድ መሆን ስለሚችሉ በማሕበረሰቡ ልማድ መሰረት የሚና ለውጥ ይኖራቸዋል፤ በአዲሱ ማንነት የሚጠበቅባቸው ማሕበራዊ ሚና አለ። ከነዚህ ሚናዎች ውስጥ እራቅ ወዳለ ቦታ ለአደን መውጣት አንዱ ነው። ከዚህ በፊት እራቅ ወዳለ ቦታ አደን መሄድ ከህጻናት የሚጠበቅ ተግባር አልነበረም።

## 3.3. የጋብቻ እና የሰርግ ሥርዓት

በጉምዝ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥርዓት ቤተሰብ ከመመስረት በላይ ትርጉም ያለው ጉዳይ ነው። በብሔረሰቡ ጋብቻ የሚፈፀመው በሁለት የተለያዩ ጎሳዎች መካከል ነው። በአንድ ጎሳ ውስጥ የሚፈፀም ጋብቻ ፈፅሞ የተከለከለ ነው። ጋብቻው የሚካሄደውም በአምስት አይነት መንገድ ነው። በዝርዝር እያንዳንዳቸውን እንመለከታለን።

### 3.3.1. የለውጥ ጋብቻ (ማንጅልማ)

ይህ የጋብቻ አይነት "ማንጅልማ" በመባል ይታወቃል። ጋብቻው አንድ ወንድ ማግባት ሲፈልግ ለሚያገባት ሴት ምትክ ከራሱ ወገን እህት ወይም የዘመድ ልጅ የሚሰጥበት ነው። ይህ አይነቱ ጋብቻ በማንዱራ ወረዳ አካባቢ በስፋት የሚፈፀም የጋብቻ አይነት ነው። አሁን አሁን

በመንግስት እየተከለከለ ስለመጣ በግልፅ ሥርዓት መፈጸሙ እየቀረ መምጣቷሉ፡፡ እኔም በአካባቢው በቆየሁበት ጊዜ ከዚህ በፊት ወቅቱ የሰርግ ሰአት ቢሆንም በይፋ ያገኘሁት ግን አንድም ሰርግ የለም፡፡ ነገር ግን በድብቅ ከሚጋቡት መካከል ዳፍሌ ቀበሌ ያገኘኋቸው ጥንዶችና ቤተሰቦቻቸው ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ ተጋቢዎችም ሆኑ ቤተሰቦቻቸው የጋብቻ ሥርዓቱን የምፈልግበትን ምክንያት ባስረዳቸውም ፎቶ ማንሳት እና ድምፃቸውን መቅረፅ እንደማልችል አስቀድመው ገልፀው በፅሑፍ ላይም ስማቸውን እንዳልጠቅስ አስጠንቅቀውኛል፡፡ ጋብቻው የተፈፀመውም በማታ ነበር፡፡ እኔም በመመልከት እና በመስማት ብቻ ሥርዓቱን መከታተል ችያለሁ፡፡ የለውጥ ጋብቻ የሚፈጽሙት ደቅ ከሚባል ቦታ ከመጡ ሰዎች ጋር ሲሆን በመጀመሪያው ቀን ከደቅ የመጡት የዳፌሊዋን ሴት ሙሽራ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ የዳፌሊዎቹ ወንድ ሙሽራ ከሴትዋ ሙሽራ ጋር በመሄድ በነጋታው ማታ ለውጥዋን ይዞ ይመጣል፡፡

ይህ የጋብቻ አይነት በራሱ በሁለት መንገድ ይካሄዳል፡፡ የመጀመሪያው በሁለቱ ተጋቢዎች ፍላጐት የሚፈፀም ነው፡፡ ሁለቱ ጥንዶች በተለያዩ አጋጣሚዎች ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ገበያ እና የተስካር ቦታዎች ቀዳሚዎቹ ናቸው፡፡ ወጣቶች በገበያ ቦታ በሄዱበት አጋጣሚ መጠጥ ቤት ወይም መንገድ ላይ ይነጋገራሉ፡፡ መጠጥ ቤት ከሆነ አረቂ እየተገባበዙ የሚመጣው መቀራረብ ብዙ ጊዜ ወደ ትዳር የማምራት አጋጣሚ አለው፡፡ በነዚህ አጋጣሚዎች የተገናኙት ወጣቶች የቤተሰብ ሁኔታቸውን ይጠናናሉ፡፡ ከምንም በላይ ግን የተለያዩ ጎሳ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ ይህ የወጣቶች ቀድሞ መነጋገርና መግባባት በሌሎች የጋብቻ አይነቶችም ሊታይ የሚችል ነው፡፡

ልጅ ከልጅቱ ጋር ከተስማማ በኋላ ለቤተሰቦቹ ያሳውቃል፡፡ ቤተሰቦቹ ቤተሰብና ዘሯን ከመረጡ ሽማግሌ ለመላክ ይወስናሉ፡፡ አባትና በአካባቢው ያሉ ሽማግሌዎች በጋራ ሆነው የልጅቱን ቤተሰብ ለመጠየቅ ይሄዳሉ፡፡ መንገድ ሲያስቡ የሚያዩት ህልም እና መንገድ ላይ የሚገጥማቸው ምልኪ ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ በብሔረሰቡ እምነት መሰረት መንገድ ላይ መጥፎ የሚባሉ እንደ ሚዳቋ፣ ቀበሮ እና በብሔረሰቡ “ዳዎ” የምትባል ወፍ ከጮኸች መጥፎ አጋጣሚ ነው፡፡ በተቃራኒው መንገዳቸው ላይ ለቅሶ ከገጠማቸው ወይም ሃዘን፤ ዝንጀሮ ከገጠማቸው መልካም አጋጣሚ ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ ከወንድ ቤት የሚላኩት ሽማግሌዎች ሴት ቤት

ሲደርሱ ምግብና መጠጥ ከተሰጣቸው በኋላ ለምን እንደመጡ ይጠየቃሉ፡፡ ለጋብቻ ጥያቄ እንደመጡ ከተረዱ ወደ እነሱ ለመምጣት ሲያስቡ ያዩትን ህልም እና በመንገድ ላይ የገጠማቸውን ነገር ሁሉ ይጠይቋቸዋል፡፡ ሽማግሌዎቹም ምንም ሳይደብቁ ይናገራሉ፡፡ በጋራ ሁነውም በብሔረሰቡ እምነት መሰረት ትርጉም ላይ ይደርሳሉ፡፡

በመቀጠልም የሴት ቤተሰቦች ስለ ልጁ ሁኔታ ይጠይቃሉ፡፡ በቅድሚያም የሚጠይቁት ልጁ ስራ ወዳድና ሰው አክባሪ ስለመሆኑ ይሆናል፡፡ የወንድ ወገኖችም ምንም ሳይደብቁ ሰነፍ ከሆነም ሰነፍነው ብለው ይናገራሉ፡፡ የሴት ቤተሰቦችም በስንፍናው ስለማይሰማሙ የወንድ ሽማግሌዎች በልተውና ጠጥተው ወደ መጡበት እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ዳቡህ ያገኘኋቸው መረጃ ሰጪዬ አቶ ምናለ አለነ እንደገለፁልኝ ከሆነ "ውሸት በጉምዝ ብሔረሰብ ፈፅሞ የተጠላ ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ለልጁ ሚስት ሊያመጣ የሄደ አባትም ቢሆን የልጁን ድክመት በግልፅ ይናገራል" (ቃለ መጠይቅ፣ 20/06/2007)፡፡

የሴት ቤተሰቦች ከወንድ ቤት ለጥያቄ ከመጡት ሰዎች ጋር ከተስማሙ በተራቸው ለልጃቸው ለውጥ የሚሰጧቸውን ልጅ ይጠይቃሉ፡፡ የሴት ወገኖች የልጃቸውን ለውጥ የሚያዩበትን ቀን በዛው እለት ይወስናሉ፡፡ በለውጥ የምትመጣዋ ልጃቸውን የምትመጥን መሆኗን ካረጋገጡ በኋላ ተነጋግረው ለሰርጉ ቀን ይቆርጣሉ፡፡ በለውጥ የምትመጣው ልጅ ለመጀመሪያዋ ተጠያቂ ወንድም ካላት ለወንድሟ ወይም ለአባቷ ሚስት ትሆናለች፡፡ ለሰርጉ እለት በሁለቱም ቤት ዝግጅት ይኖራል፡፡ ቦርዲ ይዘጋጃል፡፡ ምግብም ይቀርባል፡፡ የአካባቢው ሰው እየበላ እየጠጣ ይጨፈራል፡፡ የሙሽራዋም እህት፣ የወንድም ሚስት እና የሰፈር ሴቶች ተሰባስበው ሙሽራዋን ያሰማምራሉ፡፡ በዚህ ቀን ሙሽራዋ በሀዘን እና በልቅሶ ትጠመዳለች፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ኤቤዋ የተባሉት የብሔረሰቡ አባል ሲናገሩ፡-

> ጋብቻው የሚፈፀመው በሁለት የተለያዩ ጎሳዎች መሃከል ስለሆነ በአካባቢ እራቅ ወዳለ ቦታ ነው የምትሄደው፡፡ ዘመድ ሙቶ ለልቅሶ ካልሆነ በስተቀር ወደ ትውልድ ሰፈርዋ የመመለስ አጋጣሚ አይኖራትም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በህፃንነት ዕድሜያቸው የሚዳሩ መሆኑ እንዲባቡና እንዲያለቅሱ ያደርጋቸዋል (ቃለ መጠይቅ፣ 20/06/2007) ፡፡

በብሔረሰቡ ባሕል በለውጥ የምታገባ ሴት ጥሎሽ የላትም፡፡ ሴቶቹ ሙሽራዋን "ዳውያ" በተባለ ከአፈር በሚሰራ ባሕላዊ ቀለም እና የጉሎ ቅባት እንዲሁም ከጨሌ በሚሰራ ጌጥ ያስውቧታል፡፡

በመቀጠልም የአባቷን ወይም የአጎቷን ኮት ለብሳ ትወጣለች። የሀገር ሽማግሌዎች፣ እናት እና አባት እንዲሁም ጎረቤቶቿ ተሰብስበው ልጅቱን ይመክሯታል። ያስጠነቅቋታል። እናትዋ የሴት ሥርዓት ምን መምሰል እንዳለበት እና እንደሄደች የአማቶቿን ምግብ መብላት እንደሌለባት ትመክራታለች። የሀገር ሽማግሌዎች በበኩላቸው ዘራቸውን እንዳታሰድብ፣ ሥርዓት እንዲኖራት፣ በስራዋ ታታሪ እንድትሆን  እና አማቶቿን እንድታከብር ይመክሯታል። ከዚህ የምርቃንና የምክር ጊዜ በኋላ ሙሽራው እስኪመጣ ድረስ ሙሽሪት እንዳትሸሽ የአጐቷ ልጅ አዝሎ ይጠባበቃል።

የወንድ ሙሽሮች ሙሽሪት ቤት ሲደርሱ ምግብና መጠጥ ከተሰጣቸው በኋላ ከሰፈሩ ሴቶች ሙሽሪትን ለመንጠቅ ትግል ይጀምራሉ። በመንደሩ ጐልበት አላት ተብላ የምትታመን ሴት ሙሽሪትን በእጅና እግሯ ቆልፋ ታዝላታለች። በጣም ስለሚቆላለፉ መለየት ያስቸግራል። ከፍተኛ ትግልም ይደረጋል። በዚህ ትግል ውስጥ ማሸነፍ ከቻለ ብቻ ነው ሙሽራው መውሰድ የሚችለው። የሙሽሪት ቤተ ዘመዶች ከሙሽራው  ወገን ጋር የሚታገሉበትን ምክንያት ሙሽራው ታግሎ አሸንፎ ከወሰዳት ወደ ቤተሰቦቿ አታስብም ልቧ ይቆርጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

የሴት አጃቢዎች ሙሽሪት ወንዱ ቤት እስክትደርሰ ድረስ ተከትለዋት ይሄዳሉ። በጉዞ ላይ እድል ቀንቷቸው ሙሽሪትን ከነጠቁ ይዘዋት ይመለሳሉ። ያ ካልሆነ ግን ሙሽራው ቤት ገብተው ይስተናገዳሉ። እነዚህ ሴቶች ሙሽሪት ልጃገረድ ከሆነች ከወንድ ቤት ተሸልመው ለቤተሰቦቿ መልካሙን ዜና አብሳሪ ይሆናሉ። በአንድ አንድ ቦታ እና ጊዜ ልጃገረድ መሆኗን ለማብሰር ሌላ መንገድ ይጠቀማሉ። ከወንዱ ቤት የሄደ አንድ ሰው በሙሽሪት ወላጆች ቤት ባለቤቶች ሳያዩት ጥኂት በመሄድ በቶፍ ( በጭቃ የተሰራ ሳህን መሰል ባህላዊ እቃ) የተበጠበጠ አመድ ምሰሶ ሰር ያስቀምጣል። በዚህም ቤተሰቦቿ የልጃቸውን ንጽህና እንዲያውቁ ያድርጋል።

አጃቢዎቹ ሴቶች በርበሬ፣ ቦርዲ፣ ጨው፣ ሽንኩርት፣ ጅንጅብል እና ፍየል ተሸልመው ሲመለሱ በለውጥ ወደ ሴቷ ቤት የሄደችውን ልጃገረድ ተከትለው የሄዱ ሴቶችም በዚሁ መልክ ሲመለሱ መንገድ ላይ ይገናኛሉ። የአንዱ ወገን ፍየል ካነሰ ያስመልሳሉ፣ አይቀበሉም። ከተስማሙ ከተገናኙበት ጫካ ፍየሎችን አርደው ጠብሰው ይበሉና ይለያያሉ። የፍየሎችን ቆዳ ተልተለው ሁሉም በእግራቸው ያስራሉ። ፋይዳውም ለቤተሰቦቻቸው የልጃቸውን ልጃገረድ

መሆን እና ፍየል እንደተሸለሙ የሚያሳዩበት ነው፡፡ ከፍየሉ ቆዳ በተጨማሪ ከወንድ ቤት እስከ ሴቷ ቤት ድረስ በየመንገዱ እርጥብ ቅጠል አየበጠሱ በመጣል የልጃቸውን ልጃገረድ መሆን ያበስራሉ፡፡ እርጥቡ ቅጠል የመልካም ብስራት ምልክት ነው፡፡

በጉምዞች ዘንድ ሴት ልጅ ክብረ ንፅህናዋን ጠብቃ መገኘት የግድ ነው፡፡ ድንግል አለመሆንዋን ደብቃ የተዳረች ሴት ከፍተኛ የሆነ ግርፋት ይደርስባታል፡፡ የሙሽራው ቤተሰቦች ከግርፋት በኂላ ወደ ቤተሰቦቿ ይመልሷታል፡፡ አሁን አሁን እየቀረ ቢመጣም ልጅቱ ድንግልናዋን የወሰደውን ሰው ከተናገረች ጠቡ እስከመገዳዳል ድረስ ይደርሳል፡፡ በሽማግሌ ከተያዘ እና ከተስማሙ ደፋሪው ለሙሽራው የከብት ካሳ ይከፍላል፡፡ ካልተስማሙም ድንግልናዋን የወሰደው ሰው እንዲያገባት ይደረጋል፡፡ ሙሽሪት ወደ ባልዋ ቤተሰቦች ከሄደች በኂላ አንድ ሳምንት የመፈተኛ ጊዜ ይኖራታል፡፡ ይህ ጊዜ በአማቶቿ ቤት ሞያዋን አስመስክራ በይፋ የልጅ ሚስት የምትሆንበት ጊዜ ነው፡፡ ፈተናው የሚሆነው በማሕበረሰቡ ልማድ መሰረት ባሕላዊ መጠጥ እና አዋዜ በማዘጋጀት ነው፡፡ ያዘጋጀችውን የሰፈሩ ሽማግሌዎችና የመንደሩ ሰዎች በመሰባሰብ እየቀመሱ ደረጃ ይሰጡታል፡፡ ጥሩ ባለሞያ መሆንዋ ከተመሰከረ በይፋ ተነግሮ የልጃቸው ሚስት መሆንዋ ይታወቃል፡፡ አንድ ሳምንቱ የፈተና ጊዜ የሽግግር ወቅት ነው ማለት እንችላለን፡፡ ከነጠላነት ወደ ጥንድነት የምትሸጋገርበት፡፡ ሙሽሪት ለባልዋ የመጀመሪያ ሚስት ከሆነች ከዚህ ሥርዓት በኂላ በባልዋ ሚስትነት ትጠራለች፡፡ “ኢፎ ዳላ” የከሌ ሚስት እንደማለት ነው፡፡

በለውጥ ጋብቻ የሙሽራው ቤተሰቦች የሚሰጧት ልጅ ከሌላቸው ከዘመድ እስከ ዘር ሀረግ(ጎሳው) ድረስ ይፈለጋል፡፡ በተጨማሪም ሁለቱ ሽማግሌዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከተስማሙ ወልደው ለልጅቱ ቤተሰቦች መለወጫ ለመክፈል ይስማሙና ይጋባሉ፡፡ ልጅቱ ወልዳ የራስዋን ምትክ ሳትከፍል ከሞተች ወንዱ ከየትም አምጥቶ ሌላ ሴት ለቤተሰቦቿ ይከፈላል፡፡

የለውጥ ጋብቻ በማንዱራ ወረዳ ዙሪያ ያሉ የብሔረሰቡ አባላት በስፋት የሚጠቀሙበት የጋብቻ አይነት ነው፡፡ ይህ የሆነበትን ምክንያት የብሔረሰቡ አባልና የሀገር ሽማግሌ የሆኑት መረጃ ሰጪ አቶ ዎኬጋንድር አስረድተውኛል፡፡ እንደሳቸው አገላለፅ በዚህ አካባቢ ብዙ ጊዜ የእርስ በርስ ግጭት ይፈጠራል፡፡ ይህ የእርስ በርስ ግጭት በጣም የከረረ የሚያደርገው በሁለቱ የተጣሉ ጉሳዎች መሀከል ጋብቻ ያለመኖሩ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከእርቅ በኂላ በጋብቻ ለመተሳሰር ወስነው ሊነሱ ይችላሉ፡፡ በሌላ መልኩም ነፍስ የተጠፋፉ አካላት ነፍስ ያጠፋው

ወገን ለተጐጂው ወገን ልጁን፣ እህቱን ወይም የአጐቱን ልጅ በመስጠት እርቁን የእውነት ጠቡንም የማይደገም ያደርጉታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአካባቢዋ እርቃ የምትሄደው ልጃቸው በባሏ ወገን ጉዳት እንዳይደርስባት ከዚያ ቤተሰብ ሌላ ሴት ያመጣሉ፡፡ የባል ወገኖችም እህታቸውን ወይም ልጃቸውን ስለሚሰጡ ሚስቶቻቸውን በአግባቡ ይይዛሉ (ዋኪ ጋንድር፣ቃለ መጠይቅ 7/06/2007)፡፡ ኤቤዎ የተባለችው መረጃ ሰጪዬ እንደጠቀሱልኝ የለውጥ ጋብቻ ገፅታ የሆነ ሌላ ጉዳይ አንስተውልኛል፡፡

> ሴት ልጅ ካገባች በኋላ ባሏ ባይመቻትም የወንድሚ ትዳር እንዳይፈርስ ችላ ታሳልፋለች፡፡ ምክንያቱም እሷ ጥላ ብትሄድ የወንድሚ ሚስት ወይም በሷ ምትክ የተሰጠችው ሴት ትዳሯን ጥላ ወደ ቤተሰቦቿ ትመለሳለች፡፡ ነገር ግን እንደዚህ አይነት መፋረስ እንዳይፈጠር ሴትዋ ችግሯን ችላ ትኖራለች (ቃለ መጠይቅ 20/6/2007)፡፡

## 3.3.2. የጠለፋ ጋብቻ (ማንጉዣ)

የጠለፋ ጋብቻ በአካባቢው ከለውጥ ጋብቻ በመቀጠል የሚፈፀም የጋብቻ አይነት ነው፡፡ ይህ የጋብቻ አይነት በሁለት መንገድ ሊፈፀም ይችላል፡፡ ቤተሰቦቻቸው ሳያውቁ በተጋቢዎች ስምምነት ወይንም ሴቷ ሳትስማማ በወንዱ አስገዳጅነት ሊሆን ይችላል፡፡

በስምምነት የሚፈፀመው ጠለፋ ሁለቱ ተጋቢዎች ተዋደውና ተስማምተው ነገር ግን የሴቷ ቤተሰቦች ሳያውቁና ሳይስማሙ የሚፈፀም የጠለፋ አይነት ነው፡፡ በአብዛኛው ተጋቢዎች ስምምነታቸውን የሚያረጋግጡት በተስካር ሥርዓት ባለ ጭፈራ[3] ላይ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ከተለያዩ ቦታዎች በርካታ ሰዎች ከተለያዩ ጎሳዎች ስለሚመጡ የመተያየትና አብሮ የመጨፈር አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፡፡ በተስካር ቦታ በአዲስ ከሚተዋወቁ ወጣቶች በተጨማሪ ልቡ ከጅሏት ለውጥ የሚሰጣትን እህት ወይም ዘመድ በማጣት ወይም ጥሎሽ መስጠት አቅቶት የቀረችበትን ሴት ሊጠልፍ ይችላል፡፡ እንደተስካር ሁሉ በገበያ ቦታዎች ከግብይት በኋላ አረቄና ሻይ (ፀልኛ) በሚጠጡባቸው ቦታዎች ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ መጠጥ ቤቶች በብዛት እንደዚህ አይነት ስምምነቶች የሚፈፀሙባቸው ናቸው፡፡ ወንዱ ሴቷን ሲጋብዛት ይውልና አባብሎ ወይም አሳምኖ ደብቆ ይዟት ይሄዳል፡፡ ያለሷ ስምምነት ከሆነ ግን ከገበያ ወደ ቤቷ ስትመለስ ከጓደኞቹ ጋር ጫካ ውስጥ ተደብቆ በመያዝ ይጠፋል፡፡

---

[3]በእድሜ የገፉ ሰዎች ሲሞቱ እና ተስካራቸው ሲወጣ ስርአቱ በጭፈራ የታጀበ ነው፡፡ በ3.4 ላይ ተብራርቷል፡፡

በሁለቱም መንገድ ጠለፋው ቢፈፀም በመካከል ሽማግሌ ካልገባ ለመገዳደል የሚደርስ ጠብ ሊጣሉ ይችላሉ፡፡ ልጁ ከጠለፋት በኋላ በቤተሰቦቹ ቤት አይቀመጥም፡፡ ተደብቆ በተለያዩ ቦታዎች (የዘመድ ቤት) በመዘዋዋር ይሰነብታል፡፡ ምክንያቱም ሽማግሌ በመሀከላቸው ገብቶ እርቅ እስካልወረደ ድረስ የሴቷ ቤተሰቦች አደጋ ሊያደርሱበት ስለሚችሉ ጥንቃቄ ማድረግ ስላለበት ነው፡፡

የወንድ ቤተሰቦች ሽማግሌዎችን ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ይልካሉ፡፡ በባሕሉ መሰረት ሴት ልጅ ላይ ጉዳት ማድረስ ክልክል ስለሆነ ለሽምግልና የሚላኩት ሴቶች ናቸው፡፡ ሽማግሌዎችም ልጃቸው ያለችው እነሱ ጋር እንደሆነ እና ምንም ችግር እንዳልደረሰባት ያሳውቃሉ፡፡ ሴት ከመሆናቸው በተጨማሪም ለእርቅ የተላኩ ሽማግሌዎች ላይ ምንም አይነት ችግር ማድረስ የተወገዘ ነው፡፡ በማንዱራ አካባቢ ከጠለፋ በኋላ ብዙውን ጊዜ ለተጠለፈችው ሴት ለውጥ ሌላ ልጅ በመስጠት እርቅ ይወርዳል፡፡ ጠላፊው የደረሰች እህት ከሌለችው እንኳን የዘመድ ልጅ ተፈልጐ ይሰጣል፡፡ ጠቡ (ችግሩ) የወንዱ ዘር (ጎሳ) ስለሆነ ከጎሳው በሙሉ ተፈልጎ ቢጠፋ እንኳን ዕድሜዋ ለጋብቻ ያልደረሰች (የወር አበባ ያላየች) ልጅ ትሰጣለች፡፡ የተላኩት ሴት ሽማግሌዎች የልጅቱን ደህንነት ከገለፁ በኋላ እርቅ የሚፈፀምበትን መንገድ ይፈልጋሉ፡፡ በለውጥ ከሆነ በለውጥ ካልሆነም በጥሎሽ ካሳ ከፍለው ለመታረቅ ይነጋገራሉ፡፡ በዚህ መልክ ሰላም ከወረደ በኋላ ተጋቢዎቹም ተረጋግተው ትዳራቸውን ይፈፅማሉ፡፡ በተጋቤዎቹ ቤተዘመዶቹም መሃከል እርቅ ይወርዳል፡፡

በማንዱራ ወረዳ የሚፈፀመው ሌላው የጠለፋ አይነት ባገባች ሴት ላይ የሚፈፀም ነው፡፡ አንድ ሴት ካገባችና ከወለደች በኋላ ልትጠለፍ ትችላለች፡፡ ይህኛው ጠለፋ በብዛት በሁለቱ ስምምነት ነው፡፡ የሚያደርሰው አደጋም በዛው ልክ የከፋ ነው፡፡ ባል እህቱን ሰጥቶ ወይም ብዙ ብር አውጥቶ ስላገባት ካዲሱ ጠላፊ ጋር የከረረ ጠብ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህም በሽማግሌ ተይዞ ጠላፊው ምትክ ሴት ወይም ካሳ ከፍሎ ሊወስዳትና ሊታረቅ ይችላል፡፡ ለመረጃ ማሰባሰብ መስክ በነበርኩበት ጊዜ ከዚህ የጠለፋ አይነት ጋር የተያያዘ የገጠመኝ ጉዳይ ነበር፡፡ የጠለፋ ስምምነቶች ብዙ ጊዜ ወደ አቅራቢያው ከተማ ለገበያ በሚመጡበት ጊዜ ስለሚፈፀሙ ከዚህ በፊት እኔ እዛ ከተማ እኖር በነበርኩበት ጊዜ መሀል ከተማ ላይ “እጠልፋለሁ” “አልጠለፍም” በሚል  ጩኸትና ግርግር ይፈጠር ነበር፡፡ አንድ ቀን አንዲት ሴት ስትጮህ ሰማንና ቤት ውስጥ ስለነበርን “ምን መጣ” በሚል መንፈስ ተሯሩጠን ወጣን፡፡ ልጅቷ የግቢያችንን አጥር

በሁለት እጆቿ ይዛ ትጮሃለች፡፡ ከአራትና አምስት በላይ የሚሆኑ ወጣቶች  መቀነቷን ይዘው ይጐትቷታል፡፡ በዚህ መሀል "ተው" ብንል የሚከለክሉ የሚመስሉት ጓደኞቹ ሌላው ሰው ላይ ያፈጡ ነበር፡፡ እሷም ካንድ አጥር ሲያስለቅቋት ሌላውን አጥር እየያዘች ታለቅሳለች፤ ትጮሀለች፡፡ ሌላው ሰው ይህን ቢመለከትም የተለመደ ክስተት ስለነበር ምንም አይናገርም ነበር፡፡ አሁን ለመረጃ ማሰባሰብ ባካባቢው በነበርኩበት ጊዜ ግን አንድ ቅዳሜ ቀን እረፋድ ላይ ወደ ገበያ ወጥቸ ያጋጠመኝ ክስተት ከዚህ የተለየ ነበር፡፡ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

በማንዱራ ወረዳ ገነተ ማርያም ቀበሌ በብዛት አረቄ የሚጠጡበት እና በረንዳው ላይም የራሳቸውን ቦርዴ ወይም "ክያ" የተሰኘ መጠጥ አምጥተው የሚሸጡበት አረቄና ሻይ ቤት ሄድኩ፡፡ ቤቱ ሙሉ ለሙሉ በብሔረሰቡ አባላት ተሞልቶ ነበር፡፡ ከበረንዳው አረቄ የሚጠጡ ሁለት ሴትና አንድ ወንድ አጠገብ ተቀመጥሁ፡፡ በዚህ ወቅት ተስፋ አድርጌ የነበረው ለጠለፋ የሚስማሙ ወጣት ጥንዶችን ወይም ሴት ለመጥለፍ የሚማከሩ ወጣቶችን ለማግኘት ነበር፡፡ በሹክሹክታ ይነጋገሩ የነበሩት ከሁለቱ ሴቶች አንዷ እና ወንዱ ጨዋታቸው እየደራ ሲሄድ እንደኛዋ ሴት እየተናደደች ሂዳ ነበር፡፡

ሴቶቹ ሁለቱም  ልጅ ይዘዋል፡፡ ባለ ትዳር ናቸው ማለት ነው፡፡ ይንሾካሾኩ የነበሩት ወጣቶች ንግግራቸው እየተሰማኝ ሄደና ሴቲቱ "ጥለፈኝ" (ውሰደኝ) ስትለው ሰማሁ፡፡ ትኩረቴን ሙሉ ለሙሉ ሰጥቼ ሳዳምጣቸው ሁለቱ ሰዎች ከዚህ በፊት ይተዋወቁ ነበር፡፡ አሁን እሷ ባለትዳርና የልጆች እናት ናት፡፡ ከዚህኛው ሰው ጋር ትስማምታ አብረው ለመኖር ቢጀምሩ ልጆቿንም ለባሏ ጥላ እንደምትመጣ ይነጋገራሉ፡፡ አብራት ያለችው ሴት ከሴቲዮዋ ጋር የአንድ ሰፈር ሰዎች ናቸው፡፡ እናም "አይሆንም! ትቼሽ አልሄድም" በማለት ትከራከራለች፡፡ በዚህ መሀል የሻይ ቤቱ ባለቤትና ታስተናግዳቸው የነበረችው ሴት ጣልቃ በመግባት "ባሏ ቢመጣ ምን ልታደርገው ነው? ለውጥ አለህ ወይ"? ብላ ስትጠይቀው "ለውጥማ የለኝም:: አልሰማማ ካለ ግን እመታዋለሁ" ሲል መለሰላት፡፡ "ያማ ከሆነ አንተ እስር ቤት ትገባለህ:: ከሷ ጋርም አብረህ አትኖርም::" ስትለው ሴቷ እንደ መደንገጥ ብላ ንግግሯ ቋጨችው፡፡

ይህን ካየሁ በኂላ በዳቡህ ቀበሌ ከ20 ዓመት በላይ በአንድ ጉምዝ ቤት በመኖርና በአካባቢው የተለያዩ ስራዎችን በመስራት የኖረውን አቶ ምናለ አለነ ስለዚህ አይነቱ ጋብቻ ስጠይቀው እንዲህ ሲል መለሰልኝ፡-

ይህ የጋብቻ አይነት በብሔረሰቡ ዘንድ ያለ ነው፡፡ ነገር ግን ወንድ ባለትዳሯን ሴት አሳምኖም ሆነ አስገድዶ ባሏ ሳያውቅ ከጠለፋት በኋላ በአስቸኳይ ለውጧን (ምትኳን) ወይም ጥሎሽ የከፈለውን ያህል ሃብት ይከፍላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ጠብ ከመፈጠሩ በተጨማሪ ሴትዮዋ ከመጀመሪያ ባሏ የወለደቻቸውን ልጆች ለአባታቸው ትታ ትሄዳለች፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ 20/06/2007)

### 3.2.3. የጥሎሽ ጋብቻ (ቢዣ)

የጥሎሽ ጋብቻ ከስሙም እንደምንረዳው ወንድየው ለሴቷ ቤተሰቦች ጥሎሽ በመስጠት የሚፈፀም የጋብቻ አይነት ነው፡፡ በፊት ይህ የጋብቻ አይነት የሚፈፀመው በለውጥ ጋብቻ ለውጦ ለማግባት የሚሰጣት እህት፣ የዘመድ ልጅ ወይም ልጅ የሌለው ሰው ነው፡፡ አሁን ደግሞ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ያላቸው ሀብታሞች ሀብታቸውን ለማሳወቅ እና ደረጃቸው ከፍ ያለ መሆኑን ለማሳወቅ ከፍተኛ ሀብት አውጥተው በጥሎሽ ያገባሉ፡፡ ልጅ ይድራሉ፡፡ በዚህ የጋብቻ አይነት ወንዱ የፈለጋትን ሴት ቤተሰቦቹ ከተስማሙበት እና የሴቷ ቤተሰቦችም ልጃቸውን በጥሎሽ መዳር የሚፈልጉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ሽማግሌ ይልካሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም የሴቷ ቤተሰቦች የጠየቁትን የሃብት መጠን ለወንዱ ቤተሰቦች ያሳውቃሉ፡፡ የወንድ ቤተሰቦች ከተስማሙበት ሃብቱን አቅርበው ጋብቻው ይፈፀማል፡፡ የገነተ ማርያም መረጃ ሰጪዬ ኤቤዋ እንደገለፁልኝ በብሔረሰቡ ልማድ መሰረት በጥሎሽ ጋብቻ የሚጠየቁና የሚቀርቡ የሃብት አይነትና መጠኖችን በዝርዝር አስረድተውኛል፡፡ “5 ጠበንጃ፣ 15 ከብት፣ 15 ፍየል፣ 5 አሞሌ ጨው፣ ዶሮ፣ አረቄ እና ሰሊጥ ለጥሎሽ የሚቀርቡ ናቸው" (ቃለ መጠይቅ፣ 20/06/20)፡፡

የሴቷ ቤተሰቦችም ሆኑ ሙሽራዋ ከዚህ ጥሎሽ የታረደን ከብትም ሆነ ፍየልና ዶሮ አይበሉም፡፡ “የእርም ስጋ” የምንለው አይነት ሲሆን በጉምዘኛም “ምህ ጉፃ” ይባላል፡፡ በጥሎሽ የተገኘውን ሀብት ንብረት የሴቷ ቤተሰቦች ቶሎ ብለው አያጠፉትም ምክንያቱም ሴትዋ ሳትወልድ ከሞተች ለባል ቤተሰብ መመለስ ስለሚኖርባቸው ነው፡፡ በሌላ መልኩም በጥሎሽ ያገባችው ሴት ወንድሟ ማግባት ቢፈልግ ከፍሎ የሚያገባበት ስለሆነ ነው፡፡ በዚህ የጋብቻ አይነት የተዳረች ሴት ወደ ባሏ ቤተሰብ በሄደች ጥቂት ቀናት ብትታመም ወደ ቤተሰቦቿ ይመልሷታል፡፡ ቤተሰቦቿም አስታመው ለባሏ መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡

### 3.3.4. የውርስ ጋብቻ (ቻምብ ድዋ)

የውርስ ጋብቻ ወንድም፣ አባት ወይም የወንድም ልጅ ሲሞት የሟችን ሚስት ከሀብት እና ልጆቿ ጋር ወንድም፣ አጐት ወይም ልጅ የሚወርስና የሚያገባበት የጋብቻ አይነት ነው፡፡ በብሔረሰቡ ባሕል መሰረት ወራሽ የሟችን ሚስት የሚወርስበት የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው፡፡ ሟች ከሞተ በኋላ የመጀመሪያው ተስካር ይወጣል፡፡ ከዚህ በኋላ ካሉት ወንድሞች ወይም ወንድም ከሌለው ከአጐቶቹ ውስጥ የሟችን ሚስት በውርስ የሚያገባው ሰው ይለያል፡፡ ወንድሞቹ ከተስማሙ እና ሴትየዋም የፈለገችው ሰው ከሆነ ሽማግሌዎች ይቀርቡና ሥርዓቱ ይፈፀማል፡፡ ነገር ግን ወንድሞቹ እርስ በርስ መስማማት ካልቻሉ ሽማግሌዎች ጣልቃ ገብተው ይወስናሉ፡፡

እንደዚህ አይነቱ ሥርዓት ሲፈፀም በሴትየዋ ቤት ምግብና መጠጥ ይዘጋጃል፡፡ የሟች ቤተሰቦች እና የሀገር ሽማግሌዎች ይሰበሰቡና ሥርዓቱን ያስፈፅማሉ፡፡ የተመረጠው ወንድም ከልጆቹ የወንድሙን ልጆች ሳይለይ፣ ያለ አድሎ ሊያሳድግ እና የወንድሙን ስም ሊያስጠራ በሽማግሌዎች እና በቤተሰቡ ፊት ቃል ይገባል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይህ አይነቱ ሥርዓት ሳይፈፀም የሟች ሚስት ከአንድ የባሏ ወንድም ጋር በድብቅ ግንኙነት ልትጀምር ትችላለች፡፡ ነገር ግን በዚህ ግንኙነት ቀሪው ቤተሰብ ካመነበት ሁለቱ ተጋቢዎች ቤተሰቡ ሳያውቅ በደብቅ ለፈጸሙት ተግባር ካሳ ይከፍሉና ይጋባሉ፡፡ እርቁ የሚፈጸመው ከብት ዶሮ እና ፍየል በማቅረብ ነው፡፡

በዚህ የጋብቻ አይነት የሟች ሚስት ካልተስማማች ላትቀበለው ትችላለች፡፡ ነገር ግን የወለደቻቸውን ልጆች እና ሀበት ንብረት ትታ ወደ ቤተሰቦቿ እንድትመለስ ይደረጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ግን በሷ ምትክ ለቤተሰቦቿ የተሰጠችው ልጅ ተመልሳ ትመጣለች፡፡ በዚህ ሁኔታ የወንድሟ ትዳር ሊፈርስ ስለሚችል ሴቶች ባለመስማማት ትተውእንደማይሄዱ ኤቤዋ የተሰኙት መረጃ አቀባይ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ 20/06/2007)

ሴትዮዋ የውርስ ጋብቻውን ተቃውማ በምትሄድበት ጊዜ የወንድሟ ሚስት ባልና ልጆቿን ትታ መምጣት ካልፈለገች ለቤተሰቦቿ ሴት ልጇን ትሰጣለች፡፡ ይህ የመፈጠሩ እድል ግን በጣም የጠበበ ነው፡፡

### 3.3.5. የማደጎ ጋብቻ (ምዳንቋ)

የማደጐ ጋብቻ የሚባለው ዕድሜዋ ለጋብቻ ያልደረሰች ህፃን ልጅ ከወደፊት ባሏ ቤተሰቦች ጋር ሆና ዕድሜዋ እስኪደርስ ድረስ የምታድግበት የጋብቻ አይነት ነው፡፡ በብሔረሰቡ ባሕል መሰረት ሴት ልጅ ዕድሜዋ ለጋብቻ ደርሷል የሚባለው በአባቷ ቤት እያለች የመጀመሪያ የወር አባበዋን ስታይ ነው፡፡ የማደጐ ጋብቻ የሚፈፀምባቸው የተለያዩ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ሁለቱ ጥንዶች እና ቤተሰቦቻቸው ተስማምተው ሲጋቡ የወንዱ ቤተሰብ ምትክ የሚሰጧት የደረሰች ልጅ ከሌለቻቸው ህጻን ልጅ ይሰጣሉ፡፡ የሴቷ ቤተሰቦች ከተስማሙም ህፃኗን ልጅ በመውሰድ አሳድገው የራሳቸው ወገን ለሆነ ሰው፣ ለልጃቸው ወይም ለወንድም ይድሯታል፡፡

በሌላ መልኩ የወንድ ቤተሰቦች ከህጻኗ ቤተሰቦች ጋር ዝምድና እንዲኖራቸው ከፈለጉ ቤተሰቡን ጠይቀው፣ምትክ ሰጥተው ህጻንዋን ይወስዳሉ፡፡ ወስደውም ከልጆቻቸው ወይም ባሏ ከሚሆነው ልጅ ጋር በጋራ አሳድገው ሲያድጉ ይድሯቸዋል፡፡ አንዳንዴም ለማደጐ ጋብቻ የምትሰጠው ልጅ በጠለፋ ጊዜ የምትሰጥ ምትክ ልትሆን ትችላለች፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሁለት ጎሳዎች መካከል ደም መቃባት ሲኖር ሰው የገደለው ወገን ለሞተበት ቤተሰብ ወልዳ ሟቹን ልትተካ የምትችል ሴት ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የደረሰች የሚከፍሏት ሴት ካጡ ህፃን ልጅ በማደጎነት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ባጠቃላይ ግን ዕድሜዋ ያልደረሰችን ልጅ ለወደፊት ባሏ ቤተሰብ በመሰጠት አድጋ የምታገባበት የጋብቻ አይነት ነው፡፡

## 3.4. የሀዘንና የተስካር ሥርዓት

### 3.4.1. የሃዘን ሥርዓት

ሀዘን ብዙ ምዕራፎች ያሉት አንድ ሰው በአካል ከኖረበት ማሕበረሰብ በሞት ሲለይ የሚከሰት ጉዳይ ነው፡፡ የሀዘን ሥርዓት የሚፈፀመው እንደየ ማሕበረሰቡ እምነት፣ ባሕል፣ እሴት እና የሕይወት ፍልስፍና ነው፡፡ በጉምዝ ብሔረሰብ የሚፈፀመው የሀዘን ሥርዓት እንደ ሟቹ ዕድሜ የተለያየ ሲሆን ከዕድሜ በተጨማሪም ሟቹ የሞተበት ምክንያትም ለሀዘን ሥርዓት ወሳኝነት አለው፡፡ በለጋ ዕድሜ ያለ ወጣት (በዕድሜው ያልገፋ) ሰው ሲሞት ሀዘኑ መሪር ልቅሶው የደመቀ ይሆናል፡፡ በዕድሜው የገፋ፣ ያረጀ እና በምድር ላይ ወልዶ ከብዶ ብዙ አመት የኖረ

ሰው ሲሞት ከለቅሶ ይልቅ በጭፈራ እና ዘፈን ይሸኛል፡፡ ይህ ጭፈራ እና ዘፈን የሰው ልጅ በምድር የመጣበትን ዓላማ ወልዶ ከብዶ አጠናቋል ተብሎ ሲታመን የሚሰጥ ሽልማት ሊሆን የችላል፡፡ በተጨማሪም ሰው በምድር ላይ መኖር የሚገባውን ጊዜ ያህል አለመኖሩ እንጂ የሚያሳዝነው ዕድሜውን ተጠቅሞ ለሞተ ሰው ማዘን አይገባም በሚል የሞትን ተፈጥሮአዊ ገጽታነት የመቀበል ምልት ነው፡፡

ሚቹ የሞተው በሰው ተገድሎ ከሆነ የቀብር ሥነ ሥርዓት የሚፈፀመው በሴቶች ነው፡፡ ወንድ ልጅ በዚህ ቀብር ላይ አይገኝም፡፡ አሁን አሁን እየቀረ ቢመጣም በድሮ ጊዜ ወንዶች ደም ለመመለስ ስለሚሄዱ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን ወንድ ልጅ በሰው እጅ የሞተን ሰው ከተመለከተ ፈሪ ይሆናል፤ ጠላት ቢመጣ ደፍሮ ወደ ጦርነት አይገባም ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በሰው እጅ የተገደለን ሰው ደም መመልከት የለበትም ተብሎ ይታመናል፡፡ የሀዘን ሥርዓትንበተመለከተ በመስክ ቆይታየ ጊዜ የተስካር እና የቀብር ሥነ ሥርዓት ተመልክቻለሁ፡፡ የቀብር ሥነ ሥርዓት የተመለከትኩት በቁጥር ሁለት ቀበሌ የባለንባራስ ጕቅ መንደር ነው፡፡

የሀዘን ሥርዓት የሚጀምረው የሟች ነፍስ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሲሆን ሥርዓቱም በብዛት ለሦስት ተከታታይ ቀናት ይቆያል፡፡ የመጀመሪያው ቀን የሞቱ ዜና ከሩቅ እስከ ቅርብ ላሉ ቤተዘመዶች የሚነገርበት ሲሆን ሁለተኛው ቀን ዋናውና የደመቀው ሥርዓት የሚፈፀምበት ነው፡፡ ሦስተኛው ቀን የሩቅ ቤተዘመዶች የሚሸኙበት ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከሦስት ቀን በላይ ሊቆይ ይችላል፡፡ ወደ ሃብታሙሂስ የቀብር ሥርዓት ስሄድ በመንደሩ ጸጥታ እና ከባድ ሃዘን ሰፍኖ ነበር፡፡ ምክንያቱም ሟች በ35 "በለጋ ዕድሜው" ስለሞተ ነው፡፡ የሞቱ ምክንያትም ድንገት ስለሆነ አወዛጋቢ ነበር፡፡ የሟች ወንድም የሆኑት አያና ባሮ እንደገለጹልኝ ከሆነ

> ሟች በፀና ታሞ ሳይውል ሳያድር በድንገት ስለሞተ ምክንያቱን ለማወቅ "ጋፍያ" ወደ ተባለች "አዋቂ" ቤት ሄድን፡፡ ጋፍያዋም ከአሁን በፊት ደመኞቻችን የነበሩ ሰዎች "ግጨሀ" ወይም ድግምት አድርገውበት መሆኑን ገልጻልናለች፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣15/6/2007)፡፡

ይህ አጋጣሚ የሃዘን ድባቡ ላይ የራሱ ተጽኖ ያሳረፈ ይመስላል፡፡ምክንያቱም ከጠላት ወይም ገደለ ከተባለው ጎሳ የሚመጡ ሰዎች ስጋት ሊያድርባቸው ስለሚችል ነው፡፡

በቦታው ሰዎች በጾታ፣ በዕድሜ እና ለሟች ባላቸው ቅርበት ተከፋፍለው በተለያዩ ስራዎች ተጠምደዋል፡፡ የሟችን ቤት ለመለየት በሚያስችል መልኩ በቤቱ ጣራ ላይ የኢትዮጵያ ባንዲራ

ተሰቅሏል፡፡ ባንዲራ በልቅሶ እና ተስካር ቤቶች ሁሉ መስቀል በብሔረሰቡ የተለመደ ነው፡፡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባሕል እንደሆነ ቢገለጽም ብሔረሰቡ ለሠንደቃላማ ያለውን ክብር የሚያሳይ ነው፡፡



የቀብር ጉድጓድ ሲቆፈር

በብሔረሰቡ ባሕል መሰረት ሰው ሲሞት የሚቀበረው በቤቱ ግቢ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ የቀብር ሥርዓትም የተወሰኑ ሰዎች የቀብር ጉድጓድ ይቆፍሩ ነበር፡፡ በቤቱ ጓሮ ጠመንጃ የያዙ ሰዎች ተቀምጠው፤ በሀዘን ስሜት ተውጠው፤አጠቃላይ ሁኔታውን ሲቃኙ ይታይ ነበር፡፡ አስክሬኑ የነበረው በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ሲሆን በር ላይ በስተቀኝ በኩል አንድ ሽማግሌ ከፊት ለፊቱ በእቃ ብር ይዘው ተቀምጠው ነበር፡፡ እቤት ውስጥ ጨኸት እና እሪታ እንዲሁም ከቤቱ ፊት ለፊት የሟች እህት፣ እናት እና የቅርብ ዘመዶች የመረረ ልቅሶ እያለቀሱ ይሰማ እና ይታይ ነበር፡፡ በብሔረሰቡ እንደ ሌሎች ማሕበራዊ አጋጣሚዎች ሁሉ በልቅሶ ሰአትም ከፍተኛ መረዳዳት እና መተጋገዝ መኖሩን የሚያሳዩ ሌሎች ክስተቶችም ነበሩ፡፡ ወጣት ወንዶች የዛፍ ቅጠል በመቁረጥ እና ደረቅ ሳር በመበተን ለሃዘንተኛው ዳስ ይሰራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው ነዋሪዎች ከየቤታቸው እህል እያመጡ በትልልቅ ማዳበሪያ (ኩንታል) ሲሞሉ ይታይ ነበር፡፡

ከሰፈሩ ሰው የሚሰበሰበውን እህል የመንደሩ ሴቶች ተሰብስበው ፈጭተው የሚጠጣ እና የሚበላ ምግብ ያዘጋጁበታል፡፡ እንግዶችንም ይሸኙበታል፡፡ ግብአተ መሬቱ ከመፈፀሙ በፊት የሩቅ ቤተዘመዶች በሙሉ መምጣት አለባቸው፡፡ የሟች ዘመዶች ሲመጡ ከርቀት ጀምረው እየጮሁ ሲሆን እቤት ውስጥ ገብተው የሟችን አስከሬን እየተመለከቱ ይወጡ ነበር፡፡ በዚህ ሰዓት የቅርብ ዘመድ ያልሆኑ ሰዎች ጫማቸውን አውልቀው ነው ቤት የሚገቡት፡፡ ይህ ድርጊት አንድም ሰዎቹ ዘመድ አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ በሌላ መልኩ ለአስክሬኑ ያላቸውን ክብር ያሳያል፡፡ በልቅሶ ሥርዓቱ ላይ አሁን አሁን እየቀረ ቢመጣም ጥይት የመተኮስ ሥርዓት ነበር፡፡ ጥይት የማይተኩስ እና የቅርብ ዘመድ ያልሆነ ሰው በቤቱ በር በተቀመጠው የብር መቀበያ የአቅሙን ያስቀምጣል፡፡

የመቃብር አቆፋፈሩም እንደ ሟቹ ዕድሜ እና ማሕበራዊ ደረጃ ይለያያል፡፡ የሞተው ሰው ህፃን እና ደሀ ከሆነ አንድ ክፍል ያለው መቃብር (ቀጥ ያለ) ይቆፈራል፡፡ የሞተው ሰው በዕድሜ ትልቅ እና ሀብታም ከሆነ የሚቆፈረው መቃብር ሁለት ክፍል ያለው ነው፡፡ ሁለተኛ ክፍል ያለው መቃብር የራሱ የሆነ የአሰራር ሄደት አለው፡፡ አንድ ወጥ ጉድጓድ በሰው ቁመት ተለክቶ ይቆፈራል፡፡ ስፋቱን ሰው እየተኛ ይለካል፡፡ ቁመቱ በቂ ነው ተብሎ ሲታመን ወደ ጐን ሁለተኛው ጉድጓድ ይቆፈራል፡፡ ይህም ሰውን ማስተኛት በሚያስችል መልኩ ሰው እየገባ እየለካ በቂ ነው ተብሎ እስኪታመን ድረስ ይቆፈራል፡፡ የሟቹን አስክሬን በአካባቢው የታወቁ ገናዦች አዲስ አቦጀዴ ቁም ለቁም በመቅደድ ይገንዙታል፡፡ ተገንዞ በሰሌን ተጠቅልሎ በቃሬዛ ተሸክመው ከቤት ሲያወጡት ሁሉም በየስሜቱ ያለቅሳል ይጮሀል፡፡ በሀብታሙ ሂስ ቀብር ላይ የተመለከትኩትም ይህውን ነበር፡፡ አሁን አሁን እየቀነሰ ቢመጣም በመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ሟች በሕይወት እያለ ይጠቀምባቸው የነበሩ እና ያስፈልጉታል ተብለው የሚገመቱ የእርሻ፣ የአደን እና የመመገቢያ መሳሪያዎች ይቀመጡበት ነበር፡፡

የመቃብሩ የውስጠኛው (ሁለተኛ) ክፍል አስክሬኑ ከገባ በኋላ በእንጨት ይረበረብና በጭቃ ይመረጋል፡፡ ከዛም በዋናው ጉድጓድ ላይ አፈር ይሞላል፡፡ የዚህን ሥርዓት በመቅረፅ ድምፅም ሆነ በተንቀሳቃሽ ምስል መቅረፅ አዳጋች ነበር፡፡ ግብአተ መሬቱ ሲፈፀም ሴት ወንዱ ሁሉም ቀብር ቦታ ያለ ሰው በአካባቢው ያገኘውን ድንጋይ በመቃብሩ ላይ ይጥል ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ሀዘን ከቤተሰብ እንዲርቅ እና ይህን ሃዘን የሀዘን ዳርቻ እንዲያደርገው ጥቁር ፍየል ተፈልጐ ይታረድና ደሙ በመቃብሩ እንዲፈስ ይደረጋል፡፡ የሟች ወንድም የሆኑት አያና ባሮ

እንደገለፁልኝ “የእርዱን ስጋ ቤተሰቡ እና የሟች ቅርብ ዘመድ አይበሉትም፡፡ ይህ የሆነበትን ምክንያት ስጋውን ቤተሰብ ከበላ በቤቱ ሞት ይደጋገማል፡፡ ሀዘን አይርቅም ተብሎ ስለሚታመን ነው” (ቃለ መጠይቅ፣ 15/06/2007)::

ሟች ልጅ ያደረሰ ሰው ከሆነ የልጅ ባሎቹ ሁሉም ነጠላ ይገዛሉ፡፡ ሟች ሃብታም ከሆነም ነጠላው በገንዘብ ይገዛል፡፡ የተገዛው ነጠላ ጥለቱ ተቀዶ በመቃብሩ ውስጥ ይጨመራል፡፡ የቀረው ጥለት በቤቱ ጣሪያ ላይ ይደረጋል፡፡ ጥለቱ ከበዛ ሟች ሀብታም ነበር ተብሎ ይታመናል፡፡ በቀብሩ ቀን የሟች ወንድሞች እና የአጎት ልጆች ወገባቸው ላይ ጨርቅ ነገር በማሰር ከሌሎች ተለይተው ይታወቃሉ፡፡



የሟች ወንድም ወገቡን በጨርቅ ታጥቆ

የቀብር ሥርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የመንደሩ ሰዎች በሰበሰቡት እህል የተሰራው ምግብና መጠጥ ይቀርባል፡፡ በተሰበሰበው ብርም ቡና ይፈላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሁለተኛው ቀን ያልፋል፡፡ በሦስተኛው ቀን የሟች ቤተሰቦች ፀጉራቸውን ይላጫሉ፡፡ በቀብሩ ያልተገኙ ሰዎች ይደርሳሉ፡፡ ዋናው የቀብር ሥርዓት የሚጠናቀቅበት ቀንም ስለሆነ የመጀመሪያው ተስካር የሚፈፅምበትን ቀን ወስነው ቤተዘመዱ ይበተናል፡፡

በዕድሜው የገፋ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የሚፈፀመው ሥርዓት ከሌሎች የተለየ ነው ሲሉ ምናለ አለነ ይገልጻሉ፡፡ በቤት በመንደሩ ዕድሜው የገፋ ሰው ካለ የመቃብር ጉድጓድ ተቆፍሮ ይጠብቀዋል፡፡ በተጠበቀው ጊዜ ያ ሰው ካልሞተ የተቆፈረው ጉድጓድ ይሞላል (ቃለ መጠያቅ፣ 20/06/2007)፡፡ ይህ ልማድ የሰው ልጅ በዕድሜ ከገፋ በስነልቦና (በሃሳብ) ከማሕበረሰቡ እየተለየ እንደሆነ የሚያሳይ ይመስላል፡፡ ነፍስ ከስጋ ስትወጣ የሽግግር ሰአት ነው ማለት እንችላለን፡፡ ከሞተ በኋላ በሌላ ማንነት፤ በሙት መንፈስነት ከማሕበረሰቡ ጋር ይኖራል፡፡

የዕድሜ ባለፀጋ የሆነ ሰው ሲሞት ከእንጨት የተሰራ "ቱራ" የሚባል የሙዚቃ መሳሪያ እና ከቅርቀሃ የተሰራ "እምቢልታ" የተሰኘው የሙዚቃ መሳሪያ እየተነፋ ይጨፈራል፡፡ የአካባቢው ህዝብ ወደ ለቅሶው እንዲሰበሰብ በብሔረሰቡ "እንዲንጋ" የሚባለው ትልቅ ከበሮ ይመታል፡፡ አሁን አሁን ከጸጥታ አንፃር እየተከለከለ ቢመጣም ጥይት እየተተኮሰ ልጁ ወይም ወንድሙ ይፎክር ነበር፡፡ ይህን የከበሮ እና የጥይት ድምፅ የሰሙ የአካባቢው ነዋሪዎች ወደ ሀዘኑ ቤት ይሰበሰባሉ፡፡

ለቀብሩ ቀን ከቅርብ እስከ እሩቅ ያሉ ዘመዶች ይላክባቸዋል፡፡ ዘመድ ወዳጅ እንዲሁም ጐረቤት ተሰብስበው በዜማና በጭፈራ ሟችን ያሞግሳሉ፡፡ ሟች በሕይወት የሰራቸውን ተግባራት በመዘርዘር እና በመጥቀስ ታሪኩን ያወሳሉ፡፡ ሟች ጠንካራ ገበሬ ከነበረ በግብርናው የነበረውን ታታሪነት ጠንካራነት፣ የታወቀ አዳኝ ከሆነ ጀግንነቱን፣ በማሕበረሰቡ ውስጥ አዛኝ እና እሩህሩህ ከነበረም ደግነቱ በዜማው ይወሳል፡፡ የአካባቢው ሰው መተጋገዝ እና በየስራ ድርሻው መሰማራት በዕድሜ ያልገፋ ሰው ሲሞት እንደሚፈፀመው ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚህ የአዛውንቶች የቀብር ሥርዓት በርካታ ሰዎች  ይገኙበታል፡፡ የመቃብር አቆፋፈሩም ቦታው የተመቸና ንፅህና ያለው መሆን እንዳለበት በቡድን ውይይት ወቅት ተረድቻለሁ፡፡ ምክንያቱም የሟች መንፈስ መቆሸሽ እና መጉስቆል ስለሌለበት እና ከቀሪው ቤተሰብ ጋር ይኖራል፤ ምህረት ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ (የቡድን ውይይት፣7/06/2007)፡፡ ከቀብር በኋላ የሚታረደው እርድም በርከት ይላል፡፡ በመቃብሩ ላይ ደም ለማፍሰስ የታረደውን ጥቁር ፍየል ቤተሰብ የሆነ ሰው አይበላውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚፈፀመውን እርድ ግን ሁሉም ሰው በጋራ ይመገባል፡፡

### 3.4.2. የተስካር ሥርዓት

የተስካር ሥርዓት ሰው በአካል ከማሕበረሰቡ ተለይቶ ከሞተ በኋላ በመንፈስ ከማሕበረሰቡ ጋር መሆኑን የሚያመላክት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ውስጥም የመጨረሻው የሽግግር ሥርዓት ነው፡፡ ተስካር በጉምዝ ብሔረሰብ በድምቀት ከሚከበሩ ሥርዓቶች ውስጥ ቀዳሚው ሲሆን "ክይ ምሽ" ተብሎ ይጠራል፡፡ በብሔረሰቡ ባሕል መሠረት ለአንድ ሰው ከአንድ ጊዜ እስከ ሦስት ጊዜ ተስካር ሊወጣለት ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ተስካር ሰውዬው በሞተበት ቀን አቅራቢያ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛው ቤተዘመድ ወስኖ ሁሉም ተረዳድቶ በአመቱ ወይም በሁለት አመቱ በሰፊው የሚፈፀም ይሆናል፡፡ በተጨማሪም

ሁለተኛውን ተስካር አባት ብቻውን በዋናነት ያዘጋጀው ከሆነ በሌላ ቀን ልጆች ብቻ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ እነዚህ በዋናነነት በሁሉም ሰው ዘንድ የሚፈፀሙ ሲሆን በልዩ ሁኔታ የሚዘጋጁም አሉ ሲሉ በቡድን ውይይት ወቅት እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡፡

> የሞተው ሰው ለቤተሰቦቹ በተደጋጋሚ በህልም ከታየ ነፍሱ ተጠምታ ስለሆነ ተስካር ይወጣለታል፡፡ ሰዎች ከሞቱ ብዙ አመት ከሆናቸው በኋላም ቢሆን በቤተሰቡ ጤና ማጣት ከመጣ፣ ከብት፣ ፍየልና ሌሎች እንስሳት እየሞቱ ካስቸገሩ አዝርቱ አልበረክት ካለ የሟች መንፈስ ተቀይሟል ስለዚህ ዘመድ ወዳጅ ተጋግዞ ቤተሰቡ ተስካር ያወጣል ያካልሆነ ቤተሰቡ ጤና ያጣል ሰውም ሊሞት ይችላል፡፡ (ሃጽ አሊጋስ፣ የቡድን ውይት ፣ኤሲሳ፣14/06/07)

በኤሲሳ ጐጥ የወጣው የዣኒፀሀይ ተስካርም የዚሁ አይነት ነው፡፡ ሴትየዋ አንድ ልጅ አላት፡፡ ይህ ልጅ እናቱ ከሞተች ከ10 ዓመት በኋላ በኢኮኖሚ የጠነከረ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ልጆቹ ጤና እያጡ ሲያስቸግሩት በአቅራቢያው ወዳለች “ጋፍያ” ሄዶ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጊዜ የእናቱን ተስካር ስላላወጣ ልጆቹ እንደሚታመሙና አሁንም ይህን ማድረግ ካልቻለ ለሱም አደጋ እንዳለው ይነገረዋል፡፡ በመጨረሻ ከዘመድ ወዳጅ ጋር ተማክሮ ተስካሩን ለማዘጋጀት ችሏል (ቃለ መጠይቅ 14/06/2007)፡፡ በብሔረሰቡ እራሱን የቻለ የተስካር ወቅት ያላቸው ሲሆን እህል ተሰብስቦ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ያለው የጥር እና የየካቲት ወር ተመራጭ እና የተለመደም ነው፡፡ እነዚህ ወራት የተመረጡበት ምክንያትም በአማካይ የግብርና ስራ የሚቀንስበት ስለሆነ መሆኑን በቡድን ወይይት ጊዜ ተረድቻለሁ፡፡ (ጅግዳ፣ 7/06/2007)

እንደ ለቅሶ እና ቀብር ሥርዓቱ ሁሉ የተስካር ሥርዓቱም እንደ ሞተው ሰው ዕድሜ፣ ማሕበራዊ ደረጃ እና ሀብት ይወሰናል (ይለያያል)፡፡ የሞተው ሰው በስራ ላይ ያለ ዕድሜውም ያልገፋ ከሆነ በተስካሩ ላይ አይዘፈንም፡፡ ካለመዘፈኑ ጋር ተያይዞ የፍተሻእና ዋስ መጥራት ሥርዓቱ ይቀንሳል፡፡ የሞተው ሰው በዕድሜው የገፋ፣ በማሕበረሰቡ ከበሬታ የነበረው ጀግና እና ሀብታም ከነበረ ተስካሩ እጅግ የደመቀና ከፍተኛ የሆነ ሰው የሚታደምበት ይሆናል፡፡ በመስክ ቆይታዬ ሁለት ተስካሮች ላይ ተገኝቼ ሥርዓቱን ተመልክቻለሁ፡፡ የመጀመሪያው ተስካር ሟች ዕድሜዋ የገፋ እና በርካታ ልጆችን እንዲሁም የልጅ ልጆችን ያፈራች ስለነበረች በደመቀ መልኩ የተከበረ ሲሆን ሁለተኛዋ ሟች በወጣትነት ዕድሜዋ ስለሆነ የሞተችው የተስካር ሥርዓቱ ከጭፈራ ይልቅ የሀዘን ድባብ ያጠላበት ነበር፡፡ ሥርዓቱ ለወንድም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁለቱንም ሥርዓቶች በዝርዝር እንመልከት፡፡

የተስካር ስራ የሚጀመረው ከሚፈፀምበት ቀን አንድ ወር ቀደም ብሎ ነው፡፡ ሥርዓቱን ለመፈፀም ቤተሰብ ከ4-6 ከብት፣ 10 ፍየል እና ዶሮዎች እንዲሁም እስከ 10 ኩንታል የቦርዲ እና የዳቦ እህል ያዘጋጃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዕለቱ ዘመድ ወዳጅ እንደ አቅሙ ከብትም ሆነ ፍየል ሊያቀርብ ይችላሉ፡፡ የተስካሩ ስራ በይፋ የሚጀመረው “ግህሻ” በሚባለው ሥርዓት ነው፡፡ ይህ ሥርዓት በራሱ ሦስት ቀን ሊወስድ ይችላል፡፡ በዚህ ቀን በመንደሩ ያሉ ሴቶች በሙሉ ወፍጪቸውን ይዘው ወደተስካሩ ቤት ይመጣሉ፡፡ ለሥርዓቱ የሚሆነው እህል በሙሉ ይቀርብና ይፈጫል፡፡ ስራው የሚፈፀመውም በጭፈራ እና በዘፈን ታጅቦ ነው፡፡

ባህላዊ የአረቄ መጠጥ ይቀርባል፣ እየጠጡ እየዘፈኑ ሲፊጩ አድረው ካላለቀም ይውሉበታል፡፡ ግማሾቹ ውሃ በመቅዳት ዱቄቱን በወፍራሙ ይደብቱታል፡፡ በሦስተኛው ቀን ጠዋት የወፍጮ ማንሻ እርድ ይፈፅማል፡፡ ፍየል ከታረደና ደም ከፈሰሰ በኋላ ሁሉም ሴቶች ያመጡትን ወፍጮ አንስተው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ ከዚህ ዝግጅት በኋላ በአካባቢው ላሉ ሁሉም ጎሳዎች ጥሪ ይተላለፋል፡፡



የተስካር እድምተኞች በየመጡበት ጎጥ ተቀምጠው፡፡

ጀግዳ በነበረው ተስካር ላይ ዘጠኝ ያህል ጎሳዎች የተገኙ ሲሆን ተስካሩን የሚያጡት “ዲጉሳ” የተባለው ጎሳ አባል የሆነው ግርሙ ባንዱሀ ናቸው፡፡ አቶ ግርሙ “ሰዎችን እስከ ባንቡክ ድረስ በእግሬ በመሄድ ጥሪ አስተላልፌለሁ” ሲሉ ገልጸውልኛል (ቃለ መጠይቅ 8/06/2007)፡፡ ባምቡክ ማለት በግምት ከጀግዳ 70 ኬሎ ሜትር ይርቃል፡፡ በዚህ መልክ የተጠሩ ሰዎች በተስካሩ የመጀመሪያ ቀን ይመጣሉ፡፡ ሴቶች ለቦርዲ የሚሆን ድፍድፍ መሳይ “ጉቋ” እና አረቄ ይዘው

ይመጣሉ። አንዳንዶቹም በርዲውን እራሱን ያመጣሉ። የመንደሩ ሰዎች አስተናጋጅ ነው የሚሆኑት። በቤቱ ዙሪያ ሰፊ ዳስ ይጣላል። ቅጠልም ይነጠፍበታል።

እንግዶች በየአቅጣጫው ህፃን ትልቅ፣ ሴት ወንድ ሳይል ተሰልፈው ወደ ሰፈሩ አቅራቢያ ሲደርሱ ይቆማሉ። ከባለ ተስካሮቹ ወገን እንግዳ ተቀባዩ ቡድን አቀባበል አደርጎ እስኪያስገባቸውም ይጠብቃሉ። እንግዶች ወደ ተስካሩ ከመቀላቀላቸው በፊት ሁሉም ሰው ይፈተሻል። ፍተሻው የጦር መሳሪያ መያዝ አለመያዛቸውን ሲሆን ስለት፣ ጥይት እና ጉራዴ ካለ ይዞ መግባት የተከለከለ ነው። ያየዙትን ዱላም ለእንግዳ ተቀባዩ ያስረክባሉ። በተስካሩ ላይ መጠጥና ጭፈራ ስላለ እረብሻ እንዳያስነሱ ሁሉም ቡድን ዋስ ይጠራሉ። ገንዘብም ያስይዛሉ። አንድ ቡድን ጠብ ቢያስነሳ ዋሱ የሚጠየቅ ሲሆን ዋስ የሚሆነውም ሰው ከመጡበት አካባቢ ተሰሚነት ያለው መሆን አለበት። በቡድን ውይይቱ ላይ እንደተረዳሁት የጠበቀ ፍተሻ እና ዋስ መጥራት ያስፈለገው የበርካታ ጎሳ አባላት ስለሚመጡ ደመኛሞች ከጠላታቸው ጋር ይገናኛሉ። መጠጥ ሲበዛ በጭፈራ ጊዜ ሊጣሉና ደም ሊፋሰሱ ስለሚችሉ ይህን ለመከላከል መሆኑን ተረድቻለሁ። (ቡድን ውይይት 8/06/2007)

ከፍተሻው በኋላ በሰልፍ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ይሄዱና ይቀመጣሉ። ሁሉም በየራሱ መቀመጫ ተለይቶ ይቀመጣል። በተስካሩ ወቅት የቤቱን ሁኔታ የተመለከትን እንደሆን በቤቱ ጣሪያ ላይ የኢትዮጵያ ባንዲራ ይሰቀላል። አንዳንድ ቦታ ላይ የተመለከትኩት መሀሉ ላይ ምንም ነገር የሌለበት አረንጓደ ቢጫና ቀይ ቀለም ብቻ ያለው ባንዲራ ነው።
የሟች ልብስም በጣሪያው ይሰጣል። በቤቱ በር ላይ በስተግራ ከጭቃ በተሰራ ድስት መሳይ እቃ ("ቶፋ") ድፍድፍ ይቀመጣል። ድፍድፉ የተሰራው የቅርብ ዘመድ ሁሉ ባመጣው እህል ሲሆን በውሀ ያልተበጠበጠ ነው። ከድፍድፉ ጎን የውሃ መጠጫ ከቅል በሚሰራ ሰሃን መሰል እቃ ("ፋጋ") የሚቀመጥ ሲሆን በደፍድፉ ላይ እርጥብ የግራር ቅጠል ይቀመጣል። በቡድን ውይይት እንዲህ ሲባል ተገልጿል።

> በአጠቃላይ እነዚህ እቃዎች "ምፅሁሳ" ተብለው ይጠራሉ። የመቀመጣቸውም ምክንያት ድፍድፉ የሟች መንፈስ እንዲቋደሰው የተቀመጠ ሲሆን ፋጋው በህይወት እያለች ትጠጣበት የነበረ መሆኑን እና አሁንም ከድፍድፉ ቀንሶ እንዲጠጣበት የታሰበ ነው። የግራር ቅጠል ክረምት ከበጋ የማይደርቅ ቅጠል በመሆኑ እና እሾህማ መሆኑ ተስካሩ

ምንም ችግር ሳይገጥመው በሰላም እንዲጠናቀቅ ያደርጋል የሚል እምነት አለ (ብርሌ፣ የቡድን ውይይት፣ ጀግዳ፣ 8/06/2007)፡፡

ይህ ቅጠል በብሔረሰቡ የእርቅ ሥርዓት ሲፈፀምም የሚጠቀሙበት ሲሆን አመቱን ሙሉ ስለማይደርቅ ለዚህ ሥርዓት የተመረጠ እንደሆን ይነገራል፡፡ ይህን የ"ምፅ ሁስ" ትርጓሜ አንዳንዶቹ ባሕል ስለሆነ ነው ብቻ ብለው ይመልሳሉ፡፡

ከበሩ በስተቀኝ በኩል ዘንግ የያዘ ሽማግሌ ሰው ሰዎች የሚሰጡትን ገንዘብ በእቃ ይቀባላል፡፡ በዚሁ አቅጣጫ 20 ሜትር በሚሆን እርቀት ላይ የሟች መቃብር ንፅህናው ተጠብቆ ይታያል፡፡





የቀብር ቦታ

ምፅ ሁሳ

ከመቃብሩ ጐን ለእርድ የተዘጋጁ አምስት ከብቶች ታስረዋል፡፡ በቤቱ በር ከፊት ለፊት ባለው ሜዳማ ቦታ ከ5-6 ሜትር እርዝመት ያለው አንድ ትልቅ እንጨት ተተክሏል፡፡ በእንጨቱ ጫፍ በአካባቢው የሚበቅሉ አዝርዕቶች ዋናዎቹ ዘንጋዳ እና ማሽላ ከነእንጨታቸው አንድ አንድ ዘላላ እና የኢትዮጵያ ባንዲራ ታስሮበታል፡፡ በዚህ እንጨት ዙሪያ ሁሉም ጎሳዎች ተራ በተራ ክብ ሰርተው የሚጨፍሩበት እና የሚፎክሩበት ይሆናል፡፡ የእህል ዘሩ በረጅም እንጨት ለምን እንደተሰቀለ አንድ የሀገር ሽማግሌ አቶ ምኬ ጋርድርየሚባሉ ጠይቄ ነበር፡፡ እሳቸው

እንደመለሱልኝ “የሚች ዘር እንደ እህል ዘር ሁሉ ይረባል፣ ይራባል የሚለውን እና የሃገርን ክብር ለማሳየት ነው” (ቃለ መጠይቅ 8/06/2007)፡፡



በተስካር ቤት የሚተከል የእህል ዘር እና ባንዲራ

በተስካሩ ዋዜማ ወቅት እድምተኞቱ ከሰአት በኋላ ጀምሮ እስከ ለሊቱ አስራአንድ ሰአት ድረስ በጭፈራ ያሳልፋሉ፡፡ ጉምዞች የጭፈራ ማድመቂያ እና የሰውን የዘፈን ሞራል የሚቀሰቅሱ የተለያዩ ባሕላዊ መሳሪያዎች አሏቸው፡፡ “ቱራ”፣ “አንዲጋን”፣ “ግንጣል” እና ጡሩንባ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በጭፈራው ላይ መህል ገብቶ የሚያቀነቅነው ሰው ጭራ ይዞ ያውለበልባል፡፡ አስጨፋሪ የምትባለው በግሯ ላይ “አንጫቋ” አስራ፣ በእጇ አለንጋ እና ቅጠል ይዛ መህል ላይ ትጨፍራለች፡፡ ከሌሎች የተለዬ ውዝዋዜም የምታሳይ ሲሆን ለፍከራ እና ለጭፈራው እንዲነቃቁ ታደርጋለች፡፡ የፈዘዘ ካለም በያዘችው ጨንገር (አለንጋ) ልትማታ ትችላለች፡፡ በዚህ ጊዜ እዛው ከሚፈጠር አጋጣሚ አንስቶ ከአመታት በፊት ጎሳው ደም ለመመለስ ያደረገውን ተጋድሎ ጭምር ይገጠምለታል፡፡



አስጨፋሪ

ገዳይ ካለም በስሙ ይወደሳል፡፡ ገዳይ ስንል የአንበሳና የነበር ብቻ ላይሆን ይችላል ሰውን (ጠላቱን) የገደለም ይዘመርለታል፡፡ ይወደሳል፡፡ ተራው የደረሰው ጎሳ ደመኛው ካለ የዛን ጎሳ እያጣጣለ የራሱን ጎሳ ከፍ ያለ መሆንና ጀግንነት እያወሳ ይጨፍራል፡፡ ሌላኛው ጎሳም እንዲሁ በተራው ይፎክራል፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ በተስካሩ ቦታ ግን ምንም አይነት ደም መፋሰስ እንዳይኖር በገቡት ቃል እና በጠሩት ዋስ መሰረት ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ በጭፈራው ወቅት ጎረምሶችና ኮረዳዎች በጋራ የሚያደርጉት የፊት ለፊት ጭፈራ ሌላው ትእይንት ነው፡፡ ይህ ቦታ ለወጣቶች ዋነኛ የመተጫጫ ቦታ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከተስካር በኋላ ጠለፋ ስለሚኖር በሳምንቱ ለሽምግልና በየሰፈሩ የሚቀመጡበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡

በሁለተኛው ቀን ሽማግሌዎች ከመረቁ በኋላ የቀረቡት ከብቶች ይታረዳሉ፡፡ ስጋውም በቡድን በቡድን በተወካዮቻቸው መሰረት ይከፋፈላል፡፡ ህፃን ትልቅ ሳይል ለሁሉም እኩል እንዲዳረስም ይደረጋል፡፡ በመጨረሻ ቀን ከስአት ባንዲራው ወርዶ ይታጠብና በክብር ለባለቤቱ ይመለሳል፡፡ በዋናው ቤት በር ላይ የነበረው የቦርዴ ድፍድፍ ሥርዓቱ በሰላም መጠናቀቁን ሲያረጋግጡ በሟች መቃብር ላይ ይደፋል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎችም ለተስካሩ የመጣውን ሰው መርቀው በሰላም ወደየ ሀገራቸው እንዲገቡ አስጠንቅቀው ይሸኟቸዋል፡፡

ሁለተኛው የተስካር አይነት በዕደሜያቸው ላልገፉ ሰዎች የሚከናወን ሲሆን እንደ መጀመሪያው ጭፈራ አይኖረውም፡፡ ከጭፈራውና ከፉከራው በተጨማሪ ፍተሻና ዋስ መጥራትም የለም፡፡ በአሲሳ ጉጥ የተመለከትኩት የኻንያፀሀይ ተስካርም የዚህ አይነት ነበር፡፡

ሁለተኛ ባየሁት ተስካር ላይ ጭፈራም ሆነ ፍተሻ የለም፡፡ ሁሉም ሰው በየምድብ ቦታው ተቀምጦ ይዞ የመጣውን መጠጥ እና ምግብ ይመገባል ይጠጣል፡፡ ፀጥታ እና የሀዘን ስሜቱም ከፍ ያለ ይመስላል፡፡ ከብሔረሰቡ አባል ውጭ ማንኛውም ሰው ወደ ቦታው በተናጠል ሲገባ በመጀመሪያ እጅ እንዲያስታጥብ የተመደበው አስታጣቢ ያስታጥበዋል፡፡ ይህም ለእንግዳ ሰው የሚሰጠውን ክብር ያሳያል፡፡ በመቀጠልም የብሔረሰቡ ተወዳጅ መጠጥ ቦርዲ ይሰጠዋል፡፡ ሌላው ሥርዓቱ ደረጃ በደረጃ ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ አግኚቼዋለሁ፡፡ ባጠቃላይ የተስካር ሥርዓት የሞቱ ሰዎች መንፈስ በአካል ካለው ጋር አብሮ መሆኑን ማሳያ እንዲሁም ከሙት መንፈስ ጋር እርቅ ማውረጃ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

# 4.ትንታኔ

## 4.1.በሥርዓቶቹ የሚከወኑ ልማዳዊ ድርጊቶችና ትዕምርትነታቸው

ከበራዎች ላይ ስለሚኖሩ ትእምርታዊ ጉዳዮች እና አጠቃላይ ሥርዓቱ Sims and Stephensን ሲገልጹ "የማሕበረሰቡ አስተሳሰብ አውዳዊ በሆነ መልኩ ትእምርታዊ በሆኑ ጉዳዮች ይፋ የሚወጣበት ነው" ይላሉ (Sims and Stephens ,2005:95)፡፡

ከበራዎች ላይ የሚከወኑ ልማዳዊ ክዋኔዎች በማሕበረሰቡ ወይም በቡድኑ ውስጥ ያለን ሃሳብ ወይም እምነት የሚወክሉ ናቸው፡፡ በስርዓቱ ላይ በግልፅም ሆነ በትርጉም ለሚታዩ ጉዳዮች የተለያየ ትርጉም ሊሰጧቸው ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አጠቃላይ አውዱን እና በአውዱ ውስጥ የሚከወኑ ሌሎች ልማዳዊ ሥርዓቶችን በማገናዘብ የጉዳዩን ፍቺ ማግኘት ይቻላል፡፡ በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ወቅት የሚያከናውኗቸው ሥርዓቶችም የራሳቸው ትዕምርት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ስም ማውጣት የህጻኑን ማህበራዊ ተቀባይነት ማረጋገጥ ማስቻል ነው፡፡ ከጫጩት የተገፈፈን ቆዳ በእጅ ላይ ማሰር ልጁን ከእርኩስ መንፈስ(ከመጥፎ ነገር) መጠበቅ እንዲቻል ማድረግ ነው፡፡

በከበራዎች የሚታዩ፣ በተደጋጋሚ ግዘፍ ነስተው የሚቀርቡ ጉዳዮችን በመፈክርና በመተርጎም ሥርዓቱን የሚያከናውነውን ማሕበረሰብ የሕይወት አተያይ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ የኑሮ ፍልስፍናቸውንም መገንዘብ ያስችላል፡፡ የጉምዝ ብሔረሰብ በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር የሚያከናውናቸው ሥርዓቶችን በማየትና በመመርመር የብሔረሰቡን የሕይወት ፍልስፍና ባሕላዊ እሴት ማወቅ ይቻላል፡፡ ለዚህ ጥናት በተመለከትኳቸው ዋናዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃ ሥርዓቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚመጡና የብሔረሰቡን የሕይወት ፍልስፍና ያሳያሉ ብዬ ያመንኩባቸውን ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1. መፅዳት እና መቆሸሽ

መቆሸሽና መፅዳት ሥርዓቶቹ የሚታዩ የአንድ ጉዳይ ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡ መቆሸሽ የምንለው ሀሳብ ሰዎች ከዘወትራዊ እንቅስቃሴ ውጭ ሲሆኑና በማሕበረሰቡ ያቆሸሻል (ያረክሳል) በሚባልበት ሁኔታ ሲገኙ ነው፡፡ የጉምዝ ብሔረሰብ ላይ ቆሽሿል በሚሉበት ሰአት ያለ ሰው በሌላው ማሕበረሰብ ላይሆን ይችላል፡፡ ማሕበረሰቡ መቆሸሽ ነው ብሎ የሚያምንባቸው አጋጣሚዎች እና ሁኔታዎች ግን ለሴቶች ብቻ የተወሰኑ አይደሉም፡፡ ወንዶችም ለተወሰነ ጊዜ

ቆሽሸዋል ተብለው ይገለላሉ፡፡ ሁሉም የሚቆሽሹበት መንገድ አንድ ነው የሚያሰኙ ጉዳዮችም አሉ፡፡ ሴት ልጅ ትቆሽሻለች ወይም ረክሳለች የምትባለው የመጀመሪያ የወር አበባዋን ስታይ ጀምሮ በየወሩ የወር አበባዋን ስታይና ልጅ በምትወልድበት ጊዜ ነው፡፡

ወንድ ልጅም በተመሳሳይ በሚገረዝበት ጊዜ ስለሚረክስ ወደ ቤት አይገባም ቁስሉ እስኪደርቅ ከጓደኞቹ ጋር በተሰራላቸው ጎጆ ይቀመጣል፡፡ ይህን መርከስና መቆሸሽ ለሁለቱም ፆታዎች ነው የሚያሰኝ ሌላም ጉዳይ አለ፡፡ ህጻን ልጅ  ሲወለድ (ልጁ  ሴትም ሆነ ወንድ) እናቲቱ ፀድታ ወደ ቤት የምትገባው የህፃኑ እምብርት ደርቆ ሲወድቅ ነው፡፡ ስለዚህ ሴትም ሆነ ወንድ ያልደረቀ ቁስል (እምብርት) ሳይደርቅ ወይም ሳይፀዳ እና በባሕሉ መሰረት ተቀባይነት ሳያገኝ ወደ ቤት መግባት ቤቱን ማርከስ ነው ማለት እንችላለን፡፡

በዚህ ብሔረሰብ ረክሷል ተብሎ የታመነ ሰው ሌላ ሰው ከነካና እርሱ በተቀመጠበት ሌላ ሰው ከተቀመጠ ያ ሰው ላይ ችግር ይፈጠራል፤ ይታመማል ተብሎ ይታመናል፡፡ የአንድ ሰው መርከስ ሥርዓቱ እስካልጸዳ ድረስ ለሌላም ሰው ችግር ያመጣል ተብሎ ይታመናል ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የወር አበባ የምታይ ሴት ሌላን ሰው ለመንካት እጇን አመድ መቀባት አለባት ምክንያቱም ሰላምታ የሚለዋወጠው ሰው ይታመማል እከክ ይይዘዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ መርከስና መቆሸሽ ተፈጥሯዊ በሆኑ ክስተቶች የሚመጡ ሁነው ሳለ በሰው ሰራሽ ባሕላዊ ክንዋኔዎች መፅዳት ይመጣል፡፡

ለምሳሌ መውለድና መወለድ፣ የወር አበባ ማየት፣ እንዲሁም የወንድ ልጅ መገረዝ ተፈጥሯዊ ኩደቶች ናቸው፡፡ በነዚህ ጊዜያት የሚመጣው መርከስ ግን ባሕላዊ በሆኑ ክዋኔዎች ይፀዳሉ፡፡ መስዋእት ይሰዋል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች ይመርቃሉ፡፡ በክስተቶቹ የረከሰ ሰውም ወንዝ ወርዶ ይታጠባል፡፡ በሌላ መልኩ አንዳንዶቹ የመቆሸሽ ወቅቶች በሕይወት ዘመን ዑደት ደረጃዎች የመለየት ወቅቶች ናቸው፡፡ የመንጻት ሥርዓት የሚፈጸመውም ግለሰቡ አዲስ ማንነት ይዞ ወደ ማሕበረሰቡ እንዲቀላቀል ነው፡፡

### 4.1.2. መስዋእት ማቅረብ

በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓቶቹ ውስጥ የሚታየው ሌላው ጉዳይ መስዋእት አቀራረብ ነው፡፡ መስዋእቱ የተማጽኖ፣ የምስጋና፣ የስጋት፣ የማጽዳት፣ ወይም የእርቅ ሊሆን ይችላል፡፡ መስዋእት በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓቶች ውስጥ አንድን ሰው ከአንድ ደረጃ ወይም ከነበረበት ወደ አዲሱ ሕህበራዊ እና ግለሰባዊ ደረጃ ለማሸጋገር የሚመጣ ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በብሔረሰቡ ልማድ መሰረት ከእንስሳትም ሆነ ከእጽዋት ለመስዋእትነት የሚመረጡና የማይመረጡ አሉ፡፡ ጉምዞች መጥፎ መንፈስ እንዳይቀርባቸው መጠበቂያ ቅዱሱን መንፈስ ማቅረቢያ ዶሮ ያርዳሉ፡፡ ዶሮ በሽግግር ሥርዓቶቹ በመለየት ላይ ያለች እናት ከነልጇ ከመጥፎ መንፈስ እና ወደፊት ሊገጥማቸው ከሚችል አደጋ ለመከላከል ዶሮ ይዞርባቸውና አንገቱ ይቆረጣል፡፡ በተመሳሳይ በብሔረሰቡ እርቅ ሲፈፀም የሚመረጠው መስዋእት ዶሮ ነው፡፡ በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለውን መጥፎ የጥላቻ መንፈስ ለማራቅ በሁለቱ ሰዎች እራስ ላይ ዶሮው እንዲዞር ይደረግና አንገቱ ይቆረጣል፡፡ የተቆረጡት ዶሮዎች ስለማይበሉ እራቅ ተደርገው ይጣላሉ፡፡ የዶሮ ጫጩት ለመስዋእትነት የሚመረጠው የብሔረሰቡ አባላት ባሕላችን ስለሆነ ነው ቢሉም ለጋ ስለሆነ ነው የተመረጠው ማለት እንችላለን፡፡

መስዋእት ከማቅረብ ጋር የሚነሳው መሰረታዊ ጉዳይ ለመስዋእትነት ከሚመረጠው የእንስሳ፣ የእህልና የምግብ አይነት ባሻገር መስዋት የሚቀርበው ጉዳይ ለጋነት ነው፡፡ ከዶሮ ጫጩት ለመስዋእት የሚመረጥ ሲሆን ከእህልም ጮረቃ (በቆሎ ወይም ግለሰቡ ያመረተው እህል) ተመራጭ ነው፡፡ በባሕሉ ለፈጣሪ በአመት አንድ ጊዜ የሚቀርበው መስዋእት ወይም "ክይ ግድያ"ሰብሎች በጮረቃነት ዘመናቸው ከሚሰጡት ፍሬ የሚዘጋጅ ነው፡፡ በተስካር ሥርዓቱ ለሟች መንፈስ የሚቀርበው መስዋእት "ምዕ ሁሳ" ውሃ ያልነካው አዲስና ትኩስ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ያላረጀ እና ለጋ የሆነ ነገር ለመስዋእትነት ተመራጭ ብቻ ሳይሆን የግድ መሆኑን ነው፡፡ መስዋእቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ እና ፀሎታቸው እንዲሰማ በሰው እጅ ያልተበረዘ ረጅም እድሜ ያልኖረ ንፁህና ለጋ የሆነ ነገር ተመራጭ ነው፡፡

ለጋነት ለሚለው ፅንሰ ሀሳብ ወይም ለትኩስ ሃይል በብሔረሰቡ ዘንድ ያለውን አመለካከት ከሰው ልጅ ጋር በማገናኘት መመልከት እንችላለን፡፡ አንድ ሰው በልጅነቱ ሲሞት ሀዘኑ መራር ይሆናል፡፡ በምድር ላይ ያለውን ዘመን ሲጨርስ ግን ወደ ሌላ ዓለም መሄዱ ግድ ነው ከሚል

ሃሳብ የተነሳ መቃብር ተቆፍሮ ይጠብቀዋል፡፡ በጉምዝ መስዋእት አመራረጥ ዘመኑን የጨረሰ እንስሳ መሞቱ ስለማይቀር መስዋእት ለማቅረብ አይመረጥም፡፡ ምክንያቱም መስዋእቱ ከልብ ፀሎቱም የሚሰምር ሊሆን አይችልም የሚል እምነት ስላለ፡፡ ነገር ግን በልጅነት እድሜ ያለ ሰው እና እንስሳ ለጋነቱ ያሳሳል፡፡ የሰው ልጅም በለጋ እድሜው ሲሞት ያሳዝናል፡፡ በተመሳሳይ መስዋእት የሚቀርብለት አካል ምንም ሀጢያት የሌለበት ትኩስ ነገር ሲቀርብለት ደስ ይለዋል የሚል እምነት አላቸው፡፡

### 4.1.3. ደም

ደም በሥርዓቶቹም ሆነ አጠቃላይ በብሔረሰቡ ሁለት አይነት ፅንሰ ሃሳብ ይይዛል፡፡ አንድም የመርከስ ሌላው የመቀደስ (የመፈወስ)፡፡ ደም የወር አበባ ከምታይ ሴት፣ ከወለደች እናት እና ከተገረዘ ልጅ ወጥቶ በዋናው ቤት በእህል ማሳና የእህል ማስቀመጫ ካረፈ ያረክሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ፈፅሞ የተከለከለ ነገርም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንድ ሰው ቤት ውስጥ እያለ ደም ፈሶት (በጩቤ ተወግቶ ) ቢሞት ያ ቤት ረክሷል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰው ደም የመጣን መቆሸሽ በእንስሳት ደም ሲቀደስ እናያለን፡፡ መጥፎ መንፈስም በእንስሳት ደም ሲባረር ይገጥመናል፡፡ በሽግግርሥርዓቶች ወቅት ተለይተው ከነበሩበት ሁኔታ ወደ አዲሱ ማንነት ሲሸጋገሩ ወደ መቀደስ የሚመጡት የእንስሳትን ደም መስዋእት በማድረግ ነው፡፡ ከእንስሳትም የጫጩት ደም በማፍሰስ፡፡ ሰው በሚሞትበት ጊዜም ከቤተሰቡ የሙት መንፈስ እንዲወጣ እና ሞት እንዳይደጋገም በሞተው ሰው መቃብር ላይ ፍየል ታርዶ ደም ይፈሳል፡፡ መጥፎውን መንፈስ ለማባረር ያገለግላል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ደም ፈውስ፤ መድኃኒት ሆነ ማለት እንችላለን፡፡ ለመቀደስ ደም የተመረጠ ጉዳይ ሁኖ እናገኘዋለን፡፡

### 4.1.4. ዘር መተካት

ማሕበረሰቡ ለዘር መተካትና መዋቅሩን ለማስቀጠል ያለውን አመለካከት በሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓቶች ውስጥ መመልከት እንችላለን፡፡ በብሔረሰቡ ዘርን ማስቀጠል ትልቅ ዋጋ ያለው ጉዳይ ሲሆን ትዕምርታዊ በሆኑ ጉዳዮች ይገለጻል፡፡ ይህ ጉዳይ ከሴት ልጅ ህልውና ጋር የተቆራኘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሴት ልጅ የምታልፍባቸው የሽግግር ሥርዓቶች ላይ ይህን ጉዳይ በግልፅ እናያለን፡፡ ሴት ልጅ ከተወለደች በኋላ ወደ አዋቂነት የምትሸጋገረው የመጀመሪያዋን የወር አበባ ስታይ ነው፡፡ ይህ ደረጃ ልጂቱ ሙሉ ሰው መሆንዋንና ለአቅመ ሄዋን መድረሷን ማሳያ ነው፡፡ የቤተሰቡን ዘር የማስቀጠል ሃላፊነት የምትረከብበት ወቅትም

ነው፡፡ ይህ ስለሆነም ደስታው ከፍ ያለ ነው፡፡ ሥርዓቱ ላይ ሽማግሌዎች ሲመርቁም ዘርሽን ተኪ፣ የተባረከ ልጅ ውለጂ፡፡ በማለት በመቀጠል ስለሚጠበቅባት ማሕበራዊና ባሕላዊ ሃላፊነት ያስገነዝቧታል፡፡ ይህን ደረጃ ቤተሰቦቿ በደስታ ተቀብለው ሥነ ሥርዓቱን ስለሚያስፈፅሙላት ልጅቱ  በግልጽ ስለሁኔታው ትናገራለች፡፡

ዘርን ማስቀጠል መቻል ከምንም ነገር ቀዳሚ መሆኑን የሚያሳዩ ሥርዓቶቹ የሚታዩ ክስተቶችም አሉ፡፡ የመጀመሪያው ሴት ልጅ መውለድ እስከምታቆም ድረስ በወሊድ ጊዜ ችግር እንዳያጋጥማትም ሆነ መሀን እንዳትሆን የአማቶቿን ምግብ አትበላም፡፡ ሁለተኛው እንቁላልና የዶሮ ስጋም እንዲሁ የምትከለከላቸው ምግቦች ናቸው፡፡ በወንድ ልጅ ሞቶ ምክንያት ደም የተቃቡ ሰዎች ለሟች ወገን ዘር የምታስቀጥል እና ምትክ ወንድ ልጅ የምትወልድ ሴት ልጅ ከተሰጠቻቸው ደሙ ይደርቃል፡፡ እርቅ ይወርዳል፡፡ ምክንያቱም የተጎዳው ቤተሰብ በሴቷ አማካኝነት የመከነውን (በሞተው ሰው) ዘር ማስቀጠል ይቻላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

በተጨማሪም ሥርዓት የተጋቡ ባልና ሚስቶች ሴቷ ሳትወልድ ዘር ሳትተካ ብትሞት (ተፈጥሮአዊ ሞት) ቤተሰቦቿ ሌላ ሴት እንዲሰጡ የሚገደዱበት ሁኔታ አለ፡፡ የሞተችው ወልዳ ከሆነ ግን ዘርዋን ተክታለች ተብሎ ይታመናል፡፡ በአጠቃላይ ዘር ማስቀጠል መቻል ከሥርዓቶቹ ሁሉ በብሕረሰቡ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ሴት ልጅ (ካለው ሥርዓተ ጾታዊ ጉዳይ ውጭ) ከፍ ያለ ቦታ አላት ማለት እንችላለን፡

## 4.1.5. ፀጉር መላጨት

አንድ ሰው ከነበረበት ማንነት እና ማሕበራዊ ደረጃ ወደ ሌላው ማሕበራዊ ደረጃ ሲሸጋገር የነበረበትን ማሕበራዊ ማንነት እና እሴት ይጥላል ወይም ያስወግዳል፡፡ የሚቀላቀልበትን ማሕበራዊ ደረጃም በአዲስ ማንነት እና በሌላ ሃላፊነት ይቀበላል፡፡ አሮጌውን ማንነት ማስወገዱን እና አዲሱን ማንነት እና ሃላፊነት መቀበሉንም አሮጌውን ፀጉር በመላጨትና አዲስ ፀጉር በማብቀል ያሳያል፡፡ በጉምዝ ብሔረሰብ የሚፈፀመውም ይህ ሥርዓት ነው፡፡ በሁሉም የሽግግር ሥርዓቶች ሲወለዱ፣ ከህፃንነት ወደ አዋቂነት ሲሸጋገሩ፣ ሲያገቡ እና ሲሞቱ ፀጉር መላጨትን አንዱ ልማዳዊ ድርጊት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

### 4.1.6. መቅበር

ከአንዱ የዕድሜ እና ማሕበራዊ ደረጃ ወደ ሌላው ደረጃ ሲሸጋገሩ ባለፈው ማንነት የነበሩ ያለፈው ማንነት ምልክት ያለባቸው ጉዳዮች እየተቀበሩ ይቀራሉ፡፡ ጉድጓድ የመጨረሻው የሕይወት ምዕራፍ ላይ ሲደረስ የሰው ልጅ ሙሉ አካል (ስጋ) ከነፍስ ተለይቶ መዳረሻ የሚሆነው ቦታ ነው፡፡ ያለፈ ማንነት ምልክቶችን መቅበሩም አዲሱን ማንነት በፍጹም የተቀየረ መንፈስ እና አቋም ለመቀበል ታስቦ ነው፡፡ ልብስ፣ ጸጉር፣ የአካል ክፋይ እና የመገልገያ ቁሳቁሶች ከሚቀበሩት ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## 4.2. የሽግግርሥርዓቶች እናበሥርዓቶቹየሚከወኑልማዶችለማሕበረሰቡ ያላቸውፋይዳ

ማነኛውም የፎክሎር ቅንጣት ለፈጠረው እና ለሚከውነው ማሕበረሰብ የሚኖረው (የሚያበረክተው) ፋይዳ አለ፡፡ በተለይ በከበራ (ritual) የሚከወኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ሁሉንም የፎክሎር ዘውጎች ሊይዙ ስለሚችሉ ለማሕበረሰቡ የሚኖራቸው ፋይዳ የጎላ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አንድ ማሕበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን የሚከውነው ልማዳዊ ክዋኔ በጊዜው ላሉት ሰዎች የሚሰጠው ፋይዳ ሲኖር ተቀብለው ያስቀጥሉታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ማሻሻያ እየተደረገበት ይመጣል፡፡ የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን አስመልክቶ የሚከወኑ ሥርዓቶች በሁሉም ሰው ሕይወት የሚያልፉና የሚኖሩ ናቸው፡፡ በነዚህ ሥርዓቶች ያሉ ልማዳዊ ድርጊቶችም ለማሕበረሰቡ የሚሰጡት ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ (ፋይዳ) አላቸው፡፡ በጉምዝ ብሔረሰብ የሚከናወኑ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃ ሥርዓቶች ከሚከወኑበት አውድ አንፃር ለማሕበረሰቡ ያላቸው ፋይዳ አለ፡፡ በሥርዓቶቹ የሚከወኑት ልማዳዊ ክንዋኔዎችም እንደዚሁ፡፡ ከፋይዳዎቹ ውስጥ ማሕበራዊ ፋይዳውን እና በስሩ ያሉትን መዋቅራዊ እና ግለሰባዊ ፋይዳዎች እንመለከታለን፡፡

### 4.2.1.ማሕበራዊ ፋይዳ

የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት የሚፈፀሙት በቡድን በመሆን ነው፡፡ የማንነት እና ማሕበራዊ ደረጃ ለውጡ የሚመጣው በግለሰቡ ላይ ቢሆንም የሽግግር ሥርዓቱ የሚፈፀመው ግን በማሕበረሰቡ ባሕል እና ፍልስፍና ተቀንብቦ በማሕበረሰቡ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ ከግለሰቡ ባሻገር ለአጠቃላይ ማሕበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም ወይም የሚኖረው ፋይዳ

ላቅ ያለ ነው፡፡ ከነዚህ ፋይዳዎች ውስጥ የማሕበረሰቡን ማሕበራዊ መዋቅር ማስጠበቅ በጉምዝ ማሕበረሰብ ዘንድ በዋናነት የምናገኘው ፋይዳ ይሆናል፡፡

## 4.2.1.1.ማሕበራዊ መዋቅሩን ማስጠበቅ

አንድ ብሔረሰብ በቋንቋው፣ በአለባበሱ፣ በአነጋገሩ፣ በአመጋገቡ፣ በሕይወት ፍልስፍናው፣ በእምነቱ እና በአጠቃላይ ልማዳዊ እንቅስቃሴው ከሌላው የሚለይበት መንገድ አለው፡፡ ከሌላ ተለይቶ እኔ፣ የኔ፣ የኛ የሚልበትም ከሌላው በተለየ በራሱ የሚመለከተው ነው፡፡ ይህ ጉዳይ የማንነት መፈጠሪያ እና የማንነቱ መገለጫ ሆኖም እናገኘዋለን፡፡ ማሕበረሰቡ ባሕልና እሴቱ እንዲሁም ማንነቱ የተመሰረተበትን ልማዳዊ እምነት የሚያስጠብቅበት፣ ለራሱ እንዲመቸው ለዘመናት የቀረፀውን መዋቅር የሚያስቀጥልበት መንገድ አለው፡፡ ማሕበረሰብ በተለያዩ ልማዳዊ ሥርዓቶች የተገነባ ትልቅ መዋቅር ወይም ሥርዓት ነው፡፡ ትልቁ ማሕበራዊ መዋቅር እንዲቀጥል እያንዳንዳቸው ልማዳዊ ሥርዓቶች የየራሳቸው ፋይዳ አላቸው (Barnard,2004:62)፡፡ በጉምዝ ብሔረሰብም የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃ በራሱ እና በሥዓቱ የሚከወኑት ልማዳዊ ሥርዓቶች ማሕበራዊ መዋቅሩን ለማስጠበቅ ይውላሉ፡፡ ማሕበረሰቡ መዋቅሩን ለማስቀጠል የዘረጋቸው ሥርዓቶች ናቸው ማለትም እንችላለን፡፡ እነዚህን ሥርዓቶች እና ልማዳዊ ተግባራት በጥብቅ ልማዳዊ ሂደት ስለሚመሩ በቀላሉ አይፈርሱም፡፡ እያንዳንዳቸውን ሥርዓቶች መዋቅሩን ለማስጠበቅ ያላቸውን ሚና እና ፋይዳ በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

አንድ ህፃን ልጅ ሲወለድ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ቢመጣም ከተወለደ በኋላ የሚቀበለው ማሕበረሰብ ግን እራሱ በቀረፀው መዋቅር ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል፡፡ ያ ካልሆነ ለማሕበረሰቡ ማሕበራዊ መዋቅር ችግር ሊሆን ይችላል ተብሎም ይታመናል፡፡ የተወለደው ህፃንም የተወለደበት ማሕበረሰብ በሰራው ሥርዓት (ልማድ) መሰረት የቡድን አባልነቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህ የሚሆነውም በቡድኑ እምነት እና ልማድ መሰረት ማደግ እንዲችል ነው፡፡ ህፃኑም እየተመለከተ ያደገውን ነገር ሆኖ ያን ልማድ ማስቀጠል ይችላል፡፡ ሁሉም የሽግግር ሥርዓቶች ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ እና ማሕበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ሲሸጋገሩ የሚከወኑ ናቸው፡፡ ስለሆነም ወደ ሚቀላቀሉበት ቡድን ሲገቡ በዚህ ደረጃ ማሕበራዊ ቡድኑ ከነሱ የሚጠብቀው እና እንዳይፈፅሟቸው የሚከለክለው ጉዳይ አለ፡፡ ይህን ጉዳይ በሚፈጽሙት ልማዳዊ ሥርዓት መሰረት እንዲያውቋቸው ይደረጋል፡፡ በማሕበረሰቡ መዋቅራዊ ህግጋት

መሰረት ማሟላት ያለባቸውን አሟልተው ማቆም ያለባቸውን አቁመው፣ እራሳቸውን ዝግጁና ብቁ አድርገው ይቀላቀላሉ፡፡ እነዚህ ዝግጅነቶች የራሱ የሽግግር ሥርዓቱ ፋይዳዎች ናቸው፡፡ ሰዎች በተፈጥሮ የሚያመጧቸው ለውጦች በባሕሉ መሰረት መቃኘት አለባቸው፡፡

በሁሉም ደረጃዎች ማሕበራዊ አወቃቀሩ እና ህግጋቱ ያስቀመጣቸው ግለሰባዊና ቡድናዊ መዋቅሮች አሉ፡፡ እነዚህን መዋቅሮች እና ሥርዓቶች መዋቅሩን ለማስጠበቅ ያለቸውን ፋይዳ በመቀጠል እንመለከታለን፡፡

የብሔረሰቡን የውልደት ሥርዓት ስንመለከት የሚመራበት መዋቅር ለወንድ ልጅ እና ለሴት ልጅ የሚሰጠው ድርሻ አለ፡፡ ይህ ድርሻ የሚሰጠው ከመወለዳቸው ጀምሮ ነው፡፡ "በአካል መወለድ አንድ ጉዳይ ሲሆን ማንነቱ በሚገባ ተለይቶ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት አግኝቶ እንደ አንድ አባል መቆጠር ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው" (Bell,1997:94)፡፡ በብሔረሰቡ ልማድ መሰረት ሴት ልጅ መውለድ ያለባት ከቤት ውጭ ነው፡፡ ምክንያቱም በእምነታቸው መሰረት በቤት ውስጥ የቤት አምላክ (ሙሳ) አለ፡፡ ስለዚህ በወሊድ ጊዜ የሚፈሰው ደም እቤት ውስጥ ከፈሰሰ አምላክን ያስቆጣል፡፡ የእምነት ሥርዓቱንም ይጥሳል፡፡ የእምነት ሥርዓቱና ልማዳዊ የአምልኮ ሥርዓቱ ከተዛባ የማሕበረሰቡን ማሕበራዊ መዋቅር ያዛባል ተብሎ ይታመናል፡፡ በሌላ መልኩ የሚወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ እቤት ውስጥ በሚወለድበት ጊዜ ፈሪ፣ ማሕበረሰቡን ከውጭ ጠላት መጠበቅ የማይችል መሆን ስለሌለበት ጫካ ውስጥ ተወልዶ ጀግና መሆን አለበት የሚል እምነት አለ፡፡ ስለዚህ ውጭ በመወለድ የማሕበረሰቡን እምነት እና አመለካከት ተከትሎ እንዲያድግ እና ጀግና በመሆን ማሕበራዊ ድርሻውን እንዲወጣ መደረግ አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ በቤተሰቡም ሆነ በማሕበረሰቡ ላይ መጥፎ ችግር ይገጥማል ተብሎ ስለሚታመን ልማዱን አጥብቀው ይይዙታል፡፡ ይህ ስጋት በሌላ መልኩ ማሕበራዊ መዋቅሩን ያስጠብቃል፡፡

በብሔረሰቡ ባሕል መሰረት ልጆች ከህፃንነት ወደ አዋቂነት ሲሸጋገሩ የሚከናወኑ የሽግግር ሥርዓቶች አሉ፡፡ በስርአቶቹ ላይም የሚከናወኑ ልማዳዊ ድርጊቶች ልጆቹ ማሕበራዊ መዋቅሩን ጠብቀው እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ወንድ ልጅ የግርዛት ሥርዓቱን ሲያጠናቅቅ የአደን መሳሪያ ይዞ ወንድ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ያከናውናል፡፡ ፀጉሩን በመላጨት የተገረዘባቸው ቁሳቁሶች ጨምሮ ጉድጓድ ውስጥ ይቀብራል፡፡ ልጅነቱንም አብሮ ያራግፋል፡፡ ወደ አዋቂነት ተሸጋገረ ማለት ነው፡፡ አዲስ ማንነት በመላበስ ቤተሰቡን እና ማሕበረሰቡን ከውጭ

ጠላት ይከላከል ዘንድ ሃላፊነት ይረከባል፡፡ ይህ ሥርዓት ወንድ ልጅ በማሕበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ማስረከቢያ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ልጆች የቀደምቶቻቸውን ተግባር ማስቀጠል አይችሉም ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ልጆቹ የሚገረዙት ከዕድሜ አቻቸው ጋር በሕብረት ስለሆነ ጠንካራ እና የዕድሜ ልክ ጓደኝነት ይመሰርቱበታል፡፡

ሴት የመጀመሪያዋን የወር አበባ አይታ ለአቅመ ሄዋን መድረሷን ካረጋገጠች በኋላ በማሕበረሰቡ ባሕል መሰረት ልታሟላቸው የሚገቡ እና መሆን ያለባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በሽግግር ሥርዓቱ ላይ የሀገር ሽማግሌዎች በምክርና በምርቃት እንዲሁም እናቶች በማሳየት ያስተምሯታል፡፡ ይህ ጊዜ ዘር ለማስቀጠል ብቁ መሆኗ የሚረጋገጥበት ስለሆነ ወደ ጋብቻ መቅረቧ የሚታወቅበት ነው፡፡ ስለዚህ ለጋብቻ ተመራጭ እንድትሆን እና የዘር ሀረጓን ስም እንድታስጠብቅ ክብረ ንፅህናዋን መጠበቅ ይኖርባታል፡፡ ሴት ልጅ ማወቅ የሚኖርባትን የእናትና እህቶቿን ሙያ መልመድ አለባት፡፡ ማሟላት ያለባት ሁሉም መስፈርት ወደ ሁለተኛው ደረጃ ስትሸጋገር የሚጠብቃት ስለሆነ በሽግግር ወቅት በጭፈራም ሆነ ትእምርታዊ በሆነ መንገድ እንድታወቅ ይደረጋል፡፡ ይህ ስርዓት ለማሕበረሰቡ ማሕበራዊ መዋቅሩን ማስቀጠያ ዘዴ ነው ማለት እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ይህ ሥርዓት ሴት ልጅ በማሕበረሰቡ ውስጥ ሊኖራት የሚገባን ድርሻ፤ የሚጠበቅባትን ሃላፊነት የማሳወቅ ተግባር አለው፡፡

የጋብቻ ሥርዓቱ ማሕበራዊ መዋቅሩን ከማስጠበቅ አንፃር ከፍ ያለ ድርሻ አለው፡፡ ጋብቻ ዋና ዘርን ማስቀጠያ መንገድ ነው፡፡ ቤተሰብ፣ መንደር እና ብሔረሰብ የምንለው ነገር የሚኖረው ጋብቻ ሲኖር ነው፡፡ የጉምዝ ብሔረሰብም እነዚህ የማሕበራዊ መዋቅር መገለጫ የሆኑ ተቋማትን ለማስጠበቅ እና ማሕበራዊ መዋቅሩን ለማስቀጠል የጋብቻ ሥርዓቱን ይጠቀማል፡፡ አንድ ሰው በቤተሰብ ብሎም በመንደሩ በአጠቃላይ በጎሳው ውስጥ ለትዳር ዝግጁ ሲሆን ( ስትሆን) ጉዳዩ የግለሰብ ሳይሆን የአጠቃላይ የጎሳው ይሆናል፡፡

በብሔረሰቡ ልማድ መሰረት በአንድ ጎሳ ውስጥ ጋብቻ መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡ በአንድ ጎሳ ውስጥ ጋብቻ ቢፈጸም በተጋቢዎቹ ላይ ችግር እንደሚፈጥር የሚታመን ቢሆንም በዋናነት ግን ማሕበራዊ መዋቅሩን ማስቀጠል ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በብዛት ጋብቻው የሚፈፀመው በለውጥ ስለሆነ ወንድ ማግባት ሲፈልግ ከአጠቃላይ ጎሳው ምትክ ሴት ለሌላኛው ጎሳ (የሴት ወገን) መስጠት ይኖርበታል፡፡ የምትመጣዋም ምትክ ሴት ከጎሳው አባላት አንዱን አግብታ

የጎሳውን ዘር ማስቀጠል አለባት፡፡ በጋብቻ ሥርዓቱ አንድ ጎሳ እንደ ቤተሰብ አይነት መዋቅር አለው ማለት የሚያስችል ማሕበራዊ አደረጃጀት እናገኛለን፡፡ በአንድ ጎሳ ውስጥ ጋብቻ ቢፈቀድ ማሕበራዊ መዋቅሩን ይዛባል፡፡ ሴት እህት የሌለው ወንድ ማግባት ሲፈልግ ምትክ የሚሰጠው ከአጠቃላይ ጎሳው ተፈልጎ ነው፡፡ ከዚህ ጕሳ ውስጥ ጋብቻ ቢፈቀድ ግን እህት የሌለው ማግባት ስለማይችል ማሕበራዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል፡፡ አንዳንዴም ጋብቻ በሁለት ጎሳዎች መካከል ጠብ እንዳይፈጠር መከላከያ፣ ጠብ ቢፈጠርም ሰላም ማውረጃ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ የጋብቻ ሥርዓቱ በአጠቃላይ ብሔረሰቡ ላለው ማሕበራዊ አደረጃጀት ከፍተኛ ፋይዳ አለው ማለት እንችላለን፡፡ አንድ በለውጥ ያገባች ሴት ትዳርዋን ጥላ ብትሄድ በሷ ምትክ ለቤተሰቦቿ የተሰጠችው ሴት ውደ ቤተሰቧ ትመለሳለች፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሷ ብቻ ሳይሆን የውንድሟ ወይም የአጎቷ ቤተሰብ ይፈርሳል፡፡ ነገር ግን ይህ እንዳይሆን ትዳሯን ጠብቃ ችግሮችን ችላ ትኖራለች፡፡ ማሕበራዊ ሥርዓቱም በጋብቻተረጋግቶ ይቀጥላል፡፡

በሌላ መንገድ የጋብቻ ሥርዓቱ ማሕበራዊ መዋቅሩን ያስጠብቃል ስንል በብሔረሰቡ ልማድ መሰረት ወደ ባል ቤት የምትመጣው ሴት ናት እንጅ ወንድ ወደ ሴት ቤት አይሄድም፡፡ ሴቴቱ በሄደችበት ማሕበራዊ ቡድን ምንም አይነት ችግር ብትፈጥር በመዋቅሩ ላይ ችግር ወይም ተፅኖ በማያደርስ መልኩ ወደ መጣችበት መንደር እና ቡድን እንድትመለስ ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ የጋብቻ ሥርዓቱ በጕሳ እና በዘር መረጣ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ማሕበራዊ ሥርዓቶችም የተቃኘ ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የእምነት ሥርዓቱና ባህላዊ መዋቅሩ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

## 4.3.1.2.ማሕበራዊ ትስስር መፍጠር

በጉምዝ ባሕል የግል፣ የኔ፣ የቤተሰቤ የሚሉ ቃላት ያልተለመዱ ናቸው፡፡ ማሕበራዊ ትስስራቸው  የጠበቀ ነው፡፡ የሽግግር ሥርዓቶች ይህን ማሕበራዊ ትስስር የማጠናከር እና የመፍጠር ፋይዳ አላቸው፡፡ የግለሰቦች ማሕበራዊ መተሳሰርም በሥርዓቶቹ ላይ ይገለፃል፡፡ አንድም የሽግግር ሥርዓት በግለሰብ ወይም በቤተሰብ ብቻ የማይፈጸም ሲሆን በጎሳ ወይም እንደ ማሕበረሰብ በጋራ ይፈፀማል፡፡ ህፃናትን ከአዋቂዎች፣ አዋቂዎችን ከአዛውንቶች ደሃዎችን ከሀብታሞች ማገናኛ መድረክ ሆኖም ያገለግላል፡፡ በዋናነት ሥርዓቶቹ ማሕበራዊ ትስስር የሚፈጥሩበት መንገድ አለ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ሥርዓቱ የሚፈፀምበት ቤት (አካል) ለሥርዓቶቹ

የሚያወጣውን ወጭ ሁሉም ሰው በመደጋገፍ የሚሸፍነው መሆኑ ነው። የሀዘን ሥርዓቱን ብንመለከት የቀብር ቀን የመንደሩ ሰው ሁሉ እህል አዋጥቶ በሀዘኑ ቤት አዘጋጅቶ ለቀስተኛውን ይሸኛል። በተስካር ሥርዓትም ሁሉም ሰው በሚያስብል መልኩ ወደተስካሩ ቤት ቦርዴ፣ አረቄ እንዲሁም ለዕርድ የሚሆን ከብት ወይም ፍየል ይዞ ይመጣል። ከዚህ በተያያዘ ሌሎች ሥርዓቶችንም ማሕበረሰቡ በጋራ ይፈፅማል።

በሕይወት ዘመን ሽግግር ሥርዓቶች የሚፈጠረው ማሕበራዊ ትስስር በስራ ላይም በማሕበር እንዲሆን ማድረግ ያስችላል ማለት እንችላለን። ታዳጊ ወጣቶችም የግርዛት ሥርዓታቸው የሚፈፀመው በሰፈሩ ከ8-12 አመት ዕድሜ ያላቸው በጋራ በመሆን ነው። እነዚህ ወጣቶች ከሥርዓቱ በኋላ ያላቸው ወዳጅነት የጠበቀ ይሆናል። ለአደንና እና ለሌሎች ተግባራትም በጋራ ይሰለፋሉ።

## 4.2.1.3.ማሕበራዊ ደረጃን ማሳወቅ ማስቻል

ባሕላዊ ሥርዓቶች የቡድኑን ማንነት ከመግለፅ ባሻገር በቡድኑ ወስጥ ያለን ማሕበራዊ ደረጃ ያሳያሉ። የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓቶች በራሳቸው የሰዎችን ማሕበራዊ ደረጃ ማሳወቂያ ማንነታቸውን በይፋ ማስረከቢያ ናቸው። አንድ ሰው ከህፃንነት ወደ ወጣትነት ሲሸጋገር በማሕበረሰቡ ውስጥ ያለው ማሕበራዊ ደረጃ እና ማሕበራዊ ሚና ይለወጣል። ከብቻነት በጋብቻ ወደ ጥንድነት ሲሸጋገርም ባለትዳር ወደ ሚል ማሕበራዊ ደረጃ ይቀላቀላል። ልጅ በሚወለድበት ጊዜም ወደ እናት አባት መሆን ደረጃ ይሸጋገራል። እነዚህ ደረጃዎች በማሕበረሰቡ ልማድ መሠረት በሚፈፀሙ ሥርዓቶች ይፋ ይደረጋሉ። እራሱንም በዚህ ደረጃ ላይ ነኝ ብሎ ያስተዋውቃል።

በሌላ መልኩ ለሽግግር ሥርዓቱ የሚፈፀሙ ስርዓቶች በማሕበረሰቡ ባሕል ውስጥ ግለሰቡ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ማሳያዎች ይሆናሉ። አንድ ሰው ሲወለድ በቤተሰቡ ውስጥ ብቸኛ ወንድ ወይም ብቸኛ ሴት ሆኖ ከተወለደ እንዲሁም ቤተሰቦቹ በኢኮኖሚ የተሻለ ደረጃ ላይ ያሉ ከሆኑ በስርዓቱ ላይ በሚፈፀሙ ክንዋኔዎች ማወቅ ይቻላል። ቤተሰቡ በኢኮኖሚ የተሻለ ከሆነ በሁሉም ሥርዓቶች የሚያቀርበው እርድ ከፍ ያለ ይሆናል። በጋብቻ ሥርዓቱ ላይ አሁን አሁን የጥሎሽ ጋብቻ ገንዘብ ያለው ሰው በረከት ያለ ሀብት ንብረት በመስጠት ልጅን ይድራል። የኢኮኖሚ ደረጃውንም ያሳያል።

በሀዘን ሥርዓቱም ግልፅ በሆነ መንገድም ሆነ በትእምርቶች የሟች ማሕበራዊ ደረጃ ይታይበታል። ሟች የዕድሜ ባለፀጋ መሆኑን፣ በሕይወት ሳለ ጀግና የነበረ መሆኑን በፉከራ እና በጭፈራ ይገለፃል። ሟች ሀብታም እና ብዙ ልጆች ያሉት መሆኑን በቀብሩ ላይ በሚጨመረው ነጠላ እና በቤቱ ጣሪያ ላይ በሚደረገው የነጠላ ጥለት ብዛት ማወቅ ይቻላል። በአጠቃላይ ግን የሽግግር ሥርዓቶቹ እራሳቸውምሆኑ በሥርዓቶቹ የሚፈፀሙ ክንዋኔዎች የግለሰቦችን እና የቡድኑን ማሕበራዊ ደረጃ ያሳያሉ።

## 5.ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓቶች ላይ የተደረገ ጥናት ሲሆን የሚከወንበትን አውድ መሰረት አድርገው የተሰበሰቡ መረጃዎች ጥናቱ በተቀነበበበት ንድፈሃሳብ አማካይነት ተተንትነው እና ተተርጉመው የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝተዋል፡፡ በዚህም መሰረት በብሔረሰቡ አራት ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ሥርዓቶች ያሉ ሲሆን እነሱም ውልደት፣ ከልጅነት ወደ አዋቂነት መሸጋገር፣ ጋብቻ እና ሞት ናቸው፡፡

የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት ላይ የሚከወኑ ልማዳዊ ሥርዓቶች የማሕበረሰቡን አመለካከት የሚያሳዩ መሆናቸው አንዱ የጥናቱ ግኝት ነው፡፡ ሥርዓቶቹ በልማዳዊ ክንዋኔዎች የተሞሉ በመሆናቸው እነዚህ ልማዶች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ስለሆነም ብሔረሰቡ በሕይወት ስለመኖር እና ስለመሞት፣ ከሞት በኋላ ስላለ ሕይወት፣ በጋራ ስለመኖር፣ ዘርን ስለ ማስቀጠል እንዲሁም ስለ መቆሸሽ እና ስለ መንጻት ያለውን አመለካከት መረዳት አስችሏል፡፡

ሌላው ግኝት የሕይወት ዘመን ዑደት የሽግግር ደረጃ ሥርዓቶች መፈጸማቸው ለብሔረሰቡ የሚያበረክቷቸው ፋይዳዎች መኖራቸው ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ማሕበረሰቡ የተገነባበትን መዋቅር ማስጠበቅ ዋናው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባሕላዊ ሥርዓቶቹ የማሕበረሰቡን ማሕበራዊ አንድነት እና መረጋጋት እንደሚያስቀጥሉ እና እንደሚያጠናክሩ እንዲሁም የግለሰቦችን ማሕበራዊ ደረጃ ማሳያ እንደሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ በአባላቱ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ መተጋገዝን መፍጠርም ሌላው ፋይዳ ነው፡፡

የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃ ሥርዓቶች የብሔረሰቡ አባላት ባሕላቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ የሚያደርጉ ዘዴዎች መሆናቸው ሌላው ግኝት ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ጋብቻ የሚፈፀመው በብሔረሰቡ አባላት ውስጥ ሆኖ በማሕበራዊ ደንቡ መሠረት በሁለት የተለያዩ ጐሳዎች መካከል መሆኑ ባሕላቸው ለሌሎች የተጋለጠ እንዳይሆን አድርጐታል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነን የጉምዝ ሴት ከብሔረሰቡ ውጭ የሆነን ሰው ለማግባት ፍቃደኛ አለመሆንዋ ነው፡፡

በመጨረሻ ሁሉም የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃ ሥርዓቶች የቡድን አባላትን ሥነ ልቦናዊ እርካታ የሚጨምሩ ናቸው፡፡ በወሊድ ስርዓቱ እናት ውጭ በመውለዷ ጥንካሬዋን ማስመስከሪያ፤ ልጇ ወንድ ከሆነም ጀግና እንደሚሆን ማመኗ የሚፈጥርላት ሥነ ልቦናዊ እርካታ አለ፡፡ የሞተን ሰው በሕሀሉ መሠረት መቅበር ለቤተሰቦቹ መፅናኛ ሲሆን ሌላው ሰውም የሟችን ቤተሰብ በማፅናናት ከቡድኑ ጋር አንድ መሆኑን በማሳየት ለራሱ የሚፈጥረው እርካታ አለ፡፡ የቤተሰቦቹን ተስካር ያወጣ ሰውም ከሙት መንፈስ ወቀሳ ነፃ እንደሚሆን እና ንብረቱ እና ልጆቹ ጤናማ እንደሚሆኑ ማመኑ የሚፈጥርለት መረጋጋት እና ሥነ ልቦናዊ እርካታ አለ፡፡

# ዋቢጽሑፎች


ስራየ እንዳለው፡፡ “የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓተ ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ከፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሐሳብ አንጻር”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣2005 ዓ.ም፡፡

ተሾመ ሙሉጌታ፡፡ “በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ደባጢ ወረዳ የልቅሶ ሥነሥርዓት” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ 1998 ዓ.ም፡፡

ደስታ አማረ፡፡ “በቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል”፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ ዲግሪ ሟሟያ ጹሑፍ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ድርብወርቅ ብፁ፡፡ “የጉምዝ ማሕበረሰብ ባሕላዊ ህክምና (ጋፍያ) ሥርዓትና ማሕበራዊ ፋይዳ” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ 2003ዓ.ም፡፡

የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት፡፡ *ዝክረ ህዳር፡፡* አሶሳ፣ 2007 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የስነቃል መምሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም

Abdul Samad. “The Gumaz of The Low Lands of Western Gojjam”. In Africa Journal, Italo African Institute, 1995.

Abnik, Jon. “Gumuz Ethnography” In *Encyclopedia Ethiopia*. Uhlight (Ed), Vol.ii, 2005.

Abeya Iffa. “Adaption, Culture and Changing Environment”.Addis Ababa University; Department Of Social Anthropology, MA Thesis, 1998.

Aklilu Yilma. “Some Observation on Gumuz Dialects”.*Proceeding of The 14th International Conference of Ethiopian Studies*, Addis Ababa; Institute of Ethiopian Studies, 2002.

Aster Zewde. “Gumuz Verb Morphology” Addis Ababa University; Department of Linguistics, MA Thesis, 1991.

Aysheshme Melesse. “The Validity of Customary Marriage in Gumuz Society After Abduction And Its Effect on Peace And Order of the Region”. Addis Ababa; Ethiopia Civil Service College, 2000 E.C .

Barnard Alan,. *History And Theory In Anthropology*. United Kingdom; Cambridge University Press, 2004.

Bauman, Richard. “The Field Study of Folklore in Context” In *A Hand Book of American Folklore*. Dorson, Richard (Ed), Bloomington, Indiana University Press, 1983.

Bell,Cathrine . *Ritual Perspectives and Dimension.* New York; Oxford University Press, 1997.

___________. *Ritual Theory, Ritual Practice*. New York; Oxford University Press, 1992.

Ben-Amos, Dan. **“**Context in Context**”.** New York; Western States Folklore Society, Vol. 52, No. 2/4, Theorizing Folklore, 1993.

Bender, M. Lionel.The Eastern edge of the shala; Ethiopian Nilo Sahelians, Proceeding of the fifth International Conference of Ethiopian Studies, Chicago, 1978.

Beneshangul gumuz Population data .2007 Ethiopian census of Population and housing, online data.

Gennep, Arnold Van. *The Rites of Passage*. The University Chicago Press, 1960.

Goldstein, Kenneth. *A Guide For Field Work In Folklore*. Habtboru; Published By Gale Research Company, 1964..

Grimes, Ronald .*Deeply In To The Bone*. Berkeley; University of California Press,1997.

Homans,George. “Anxiety And Ritual: The Theories of Malinowski And Radcliffe-Brown” American Anthropological Association; Blackwell Publishing, 1941.

Jeff, Hill And Peggy, Daniels. *Life Events and Rites of Passage*. United States of America; Omni Graphics Inc, 2008.

Kotharin C.R. *Research Methodology, Methods and Techniques*. New Delhi; New Age International Publishers, 2004**.**

Malinowski ,Bronislaw. “The Group And The Individual In Functional Analysis”. In *American Journal of Sociology*, The University Of Chicago Press,1936.

Malinowski, Bronislaw. *Sex and Repression In Savage Society*. New York; Published in Rutledge, 2003.

Mcgee R. Jon and Warms Richard.*Anthropological Theory*.New York; Texas State, 1955.

Meron Zelke. “The Socio Economic Role and Status of Gumuz Women”.Addis Ababa University; Department of Social Anthropology, MA Thesis, 2005.

Rappaport, A.R. “Ritual” In “Folklore Cultural Performances and Popular Entrainments”. New York; Oxford University Press, 1992.

Ruth, Finnegan. *Oral Traditions and the Verbal Arts***.** London and New York; Rutledge Publishing Company, 1992.

Simis, Martha and Marthine Stephens.. *Living Folklore.* United States of America; Utah University Press, 2005.

Taddesse Tamerat. “Early Trends of Feudal Supper Imposion on Gumuz Society in Western Gojjam”. *Proceedings From The Intentional Symposium on History And Ethiopia Studies*. Addis Ababa; Institute of Ethiopian studies, 1982.

Tekuret for Gumuz People. Situational and Need Assessment Report on Gumuz People, Addis Ababa, 2002.

Tsega Endalew. “Inter-Ethnic Relations on Frontier: Mätakkäl (Ethiopia), 1898- 1991” Wiesbaden, Hmburg, Germany, 2006.

Wold-selassie Abatte. “Gumuz and Highland Resettlers Differing Stratageis of Livelihood and Ethinic Relation in Metkel North Western Ethiopian”. Mϋnster, Götingham University, 2004”

World Vision.Assessment Report of Gender Analysis in Mandura Woreda. Mandura, Gelgel Beles, 2011.

## አባሪ አንድ

ለጥናቱ መረጃ ለማግኘት ቃለመጠይቅ ለተደረገላቸው ሰዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

በብሔረሰቡ የሚፈጸሙ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?

የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርአት ለምን ይፈጸማል?

ከሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርአት ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ተረኮች ካሉ?

በውሊድ ጊዜ የሚፈጸሙ ሥርአቶች ምን ምን ናቸው? የመፈጸማቸው ምክንያትስ ምንድን ነው?

በእርግዝና ጊዜ የሚከለከሉ እና የሚመከሩ (የሚፈቀዱ) ነገሮች ምን ምን ናቸው? ለምን?

ሴቶች ለመውለድ የሚመርጡት ቦታ የት ነው? ለምን?

ህጻኑ ከተወለደ በኋላ የሚፈጸሙ ልምዳዊ ክንዋኔዎች ምን ምን ናቸው? ለምን?

በወሊድ ውቅት ለእናት እና ልጁ ምን ይደረጋል?

በባህላዊ መንገድ ባለመውለዷ በራስዋ እና በልጇ ችግር የገጠማት እናት ካለች ታሪኳን ቢነግሩኝ?

ወላድ እናት ከማህበረሰቡ እና ከእለት እለት ስራዋ ለስንት ቀን ትገለላለች?

ህጻኑ ማህበራዊ እውቅና አግኝቶ ወደ ማህበረሰቡ የሚቀላቀለው ምን ሲሆን ነው?

ለልጃገረዶች የመጀመሪያ የወር አበባ ሥርአት ለምን ይፈጸማል? ምንስ ፋይዳ አለው?

ሥርአቱ የሚፈጸመው ለስንት ቀን ነው?

አብረዋት የሚሆኑት እነማን ናቸው?

ወንድ ልጆች በጋራ የሚገረዙት ለምንድን? ነው ምንስ ፋይዳ አለው?

ባይገረዙ ምን ጉዳት አለው?

የግርዛት ሥርአቱ ለምን ከቤት ውጭ ሆነ?

በብሔረሰቡ ስንት አይነት ጋብቻ አለ? ምን ምን ናቸው?

ለጋብቻ የሚመረጥ ዘር አለ? ሊላ ከግምት ውስጥ የሚገባ ይኖር ይሆን?

አንድ ወንድ ወይም ሴት ለጋብቻ ደርሰዋል የሚባለው መቼ እና ምን ሲሆን ነው?

አጠቃላይ የጋብቻ ሂደቱን ቢገልጹልኝ?

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከጋብቻ በኋላ የሚኖራቸውን ማህበራዊ እና ግለሰባዊ ድርሻ ቢገልጹልኝ?

ሙሽሮች የጫጉላ ጊዜ አላቸው ወይ? ካለ ስንት ቀን? ምን ምን እንዲያደርጉ ይጠበቃል?

የተለያዩ ሰዎች( ህጻናት፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ውንዶች እና አዛውንቶች) ሲሞቱ የቀብር እና የሃዘን ሥርአቱ ይለያያል ወይ? ለምን?

በሃዘን ሥርአቱ ምን ምን ይፈጸማል? ለምን?

ለቅሶው ለስንት ቀን ይቆያል?

የቀብር ቦታው የት ነው?

የሟች ቤተሰቦች ከሌሎች ሰዎች በምን ይለያሉ?

ሟች ከተቀበረ በኋላ ተስካር ለምን ይወጣል? ምንስ ፋይዳ አለው?

በስንተኛው ጊዜ እና ለምን ያህል ጊዜ ይፈጸማል?

እንደሟች ሁኔታ(ህጻንነት፣ ወጣትነት፣ ሴት ወይም ወንድ መሆን፣ ሃብታም ወይም ደሃ መሆን) የተስካር ሥርአቱ ይለያያል ወይ? ለምን?

## አባሪ ሁለት
## የመረጃ ሰጪዎች ዝርዝር
### በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች

| | የመረጃ አቀባይ ስም | ጾታ | እድሜ | የት/ት ደረጃ | ሞያ | ቀበሌ | መረጃ የተሰበበት ቀን | የመረጃ ሰጭነት ደረጃዎች | ብሄር | ምራመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኤካውክ ደርጉ | ሴ | 19 | ያልተማረች | ግብርና | ዳቡህ | 11/062007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 2 | ፍቺ ለንብቻ | ሴ | 19 | ያልተማረች | ግብርና | ዳቡህ | 11/062007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 3 | አያና ባሮ | ወ | 30 | 9ኛ ክፍል | የ/ሰራተኛ | ቁጥር ሁለት | 15/06/2007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 4 | ፋንቻ ማሊደ | ወ | 23 | 10ኛ ክፋል | ፖሊስ | ዳቡህ | 12/06/1007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 5 | አገረ ብዙነህ | ሴ | 18 | 10ኛ ክፍል | ተማሪ | ቁጥር ሁለት | 20/062007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 6 | ደርጉ ሳሉም | ሴ | 30 | ያልተማረች | ግብርና | ቁጥር ሁለት | 15/06/2007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 7 | ቦጌ ብልታ | ሴ | 45 | ያልተማረች | ግብርና | ቁጥር ሁለት | 12/06/2007 | ንኡስ | ጉምዝ | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | መከተ ጉገ | ወ | 37 | ያልተማረ | ግብርና | ቁጥር ሁለት | 12/06/2007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 9 | ምናለ አለነ | ወ | 37 | 10+2 | ነጋዴ | ዳቡህ | 20/06/2007 | ንኡስ | አገው | |
| 10 | ቡዚያ ድቢያ | ወ | 48 | ያልተማረች | ግብርና | ቁጥር ሁለት | 12/06/2007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 11 | ፋንቻ አምሳያ | ወ | 27 | 10+3 | የመንግስት ሰራተኛ | ማንዱራ | 22/06/2007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 12 | ክዊ ጃርት | ወ | 50 | ያልተማረ | ነጋዴ | ገ/ማርያም | 25/06/2007 | ንኡስ | ጉምዝ | |
| 13 | አስረሳች ማና | ሴ | 37 | 4ኛ ክፍል | ነጋዴ | ገ/ማርያም | 25/06/2007 | ንኡስ | አገው | |
| 14 | አብራሃም አይናለም | ወ | 27 | 12+3 | የመንግስት/ሰ | ገ/ማርያም | 24/06/2007 | ንኡስ | አገው | |
| 1 | አቶዋኬ ጋርድር | ወ | 98 | ያልተማረ | ግብርና | ጂግዳ | 8/06/2007 | ቅልፍ | ጉምዝ | |
| 2 | ግርሙ ባንዱህ | ወ | 60 | ያልተማረ | ግብርና | ጂግዳ | 7/06/2007 | ቁልፍ | ጉምዝ | |
| 3 | ኢልኝታ ማካ | ሴ | 50 | ያልተማረች | ግብርና | ዳቡህ | 11/062007 | ቁልፍ | ጉምዝ | |
| 4 | ሰለሞን መኩሪያ | ወ | 58 | ያልተማረ | ግብርና | ዳቡህ | 11/06200 | ቁልፍ | ጉምዝ | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 7 | | | |
| 5 | ኢቢዋ ካዊ | ሴ | 50 | ያልተማረች | ግብርና | ገ/ማሪያም | 20/06/2006 | ቁልፍ | ጉምዝ | |
| 6 | አብጀው ምህያ | ወ | 80 | ያልተማረ | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | ቁልፍ | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 7 | ጥሩነህ ባንዱህ | ወ | 50 | ያልተማረ | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | ቁልፍ | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 8 | ሃጽ አሊጋስ | ወ | 40 | 6 ክፍል | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | ቁልፍ | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |

## በቡድን ወይይት የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች

### የጂግዳ ቡድን

| | የመረጃ አቀባይ ስም | ጾታ | እድሜ | የት/ት ደረጃ | ሞያ | ቀበሌ | መረጃ የተሰበበት ቀን | | ብሄር | ምራመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶዋኬ ጋርድር | ወ | 98 | ያልተማረ | ግብርና | ጂግዳ | 8/06/2007 | | ጉምዝ | |
| 2 | ግርሙ ባንዱህ | ወ | 60 | ያልተማረ | ግብርና | ጂግዳ | 7/06/2007 | | ጉምዝ | |
| 3 | ብርሊ ካቺ | ወ | 55 | ያልተማረ | የባህል መዳኒት | ዳፊሊ | 27/05/2007 | | ጉምዝ | |
| 4 | አግዜ ዋፋ | ሴ | 55 | ያልተማረ | ግብርና | ጂግዳ | 07/062007 | | ጉምዝ | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ሳንቢጥ ኪዳኔ | ወ | 27 | 10ኛ ክፍል | መከላከያ ተመላሽ | ጂግዳ | 07/062007 | | ጉምዝ | |
| 6 | አንድዎ በየነ | ወ | 50 | ያልተማረ | ግብርና | ጂግዳ | 07/062007 | | ጉምዝ | |
| 7 | ድረስ አማረ | ወ | 45 | ያልተማረ | ግብርና | ጂግዳ | 08/06/2007 | | ጉምዝ | |
| | የዳቡህ ቡድን | | | | | | | | | |
| 1 | ኢልኝታ ማካ | ሴ | 50 | ያልተማረች | ግብርና | ዳቡህ | 11/062007 | | ጉምዝ | |
| 2 | ሰለሞን መኩሪያ | ወ | 58 | ያልተማረ | ግብርና | ዳቡህ | 11/062007 | | ጉምዝ | |
| 3 | ላቀው ፋንቻ | ወ | 80 | ያልተማረ | ግብርና | ዳቡህ | 12/06/2007 | | ጉምዝ | |
| 4 | በየነ አብደው | ወ | 70 | ያልተማረ | ግብርና | ዳቡህ | 12/06/2007 | | ጉምዝ | |
| 5 | ውሽና ሁሳ | ሴ | 50 | ያልተማረች | ግብርና | ዳቡህ | 12/06/2007 | | ጉምዝ | |
| 6 | ኢቺ ሁሳ | ሴ | 60 | ያልተማረች | ግብርና | ዳቡህ | 11/062007 | | ጉምዝ | |
| 7 | ኤችል ዋኔ | ሴ | 45 | ያልተማረች | ግብርና | ዳቡህ | 11/06/2007 | | ጉምዝ | |

| **የኤሲሳ ጎጥ ቡድን** | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አብጀው ምህያ | ወ | 80 | ያልተማረ | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 2 | ሃጽ አሊጋስ | ወ | 40 | 6 ክፍል | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 3 | ዘኒ ጅጊ | ወ | 45 | ያልተማረ | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 4 | ጥሩነህ ባንዱህ | ወ | 50 | ያልተማረ | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 5 | ማኪ ብጊ | ወ | 70 | ያልተማረ | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 6 | አቡኔ ሂስ | ሴ | 43 | ያልተማረች | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 7 | አምቡዋ ባሊ | ሴ | 60 | ያልተማረች | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |
| 8 | ኤ እንግዳ | ሴ | 30 | ያልተማረች | ግብርና | ገ/ማሪያም | 14/06/2007 | | ጉምዝ | ኤሲሳ ጎጥ |